# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

81ኛ ዓመት ቁጥር 363 ጳጉሜን 3 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












## የሰላም ቀን በአብሮነት እሴቶች ታጅቦ ይከበራል

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የአብሮነት እሴቶቻችን የዘለቄታ ሰላም ግንባታ ላይ ጉልህ ሚና ያላቸው በመሆኑ የሰላም ቀንን በአንድነትና በፍቅር ታጅበን ማክበር ይኖርብናል ሲሉ የሰላም ሚኒስትር አቶ ብናልፍ አንዷለም ተናገሩ።

ሚኒስትሩ ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደተናገሩት፣ በአሁኑ ወቅት እየታዩ ያሉት የግለኝነትና የጥላቻ አስተሳሰቦች በህዝቦች መካከል የነበረውን የመከባበርና በሰላም አብሮ የመኖር እሴቶችን እያቀጨጨ በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ጉዳት እያደረሰ ነው።

ስለዚህ የሰላም ቀንን ስናከብር ባለፉት ዓመታት የተፈጠሩ መርዛማ አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን በማረም የህዝቡን የአንድነትና የአብሮነት እሴቶች ለመገንባት ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል።

ሁላችንም ሰላምን በራሳችን ውስጥ መፈለግ አለብን እንጂ ከውጭ ለማግኘት መጣር የለብንም ያሉት

የሰላም ቀን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## አገልጋይነት የሁል ጊዜ ተግባራችን ሲሆን ይገባል

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- የአገልጋይነት ቀንን ስናከብር አገልጋይነትን የሁል ጊዜ ተግባራችን እንዲሆን ለማድረግ ቃል በመግባት ሊሆን እንደሚገባ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የለውጥ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አስታወቁ። ኮሚሽኑ ዕለቱን በተለያዩ ሁነት ያከብራል።

በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የለውጥ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ወይዘሮ ንግስት ጌታቸው የአገልጋይነትን ቀን አስመልክተው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአገልጋይነት ቀንን አንድ ጊዜ ብቻ አክብሮ ማለፍ ሳይሆን ዓመቱን ሙሉ ህዝብን ማገልገል ክብር ነው የሚለውን የአገልጋይነት ስሜት መጋራት ይገባል፤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና አገልጋዮች የተሰጣቸውን ህዝብ የማገልገል ተልዕኮ በሚፈለገው ደረጃና ፍጥነት አገልግሎት መስጠት ይኖርባቸዋል።

የአገልጋይነት ቀን ሲከበር የአንድ ቀን ሁነት ብቻ ሆኖ መቀጠል የለበትም ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ቀኑን ለሚዲያ ሽፋን የማዋል ብቻ ሳይሆን አገልግሎት መስጠት ክብር መሆኑን በመረዳት መሆን እንዳለበት



ጠቅሰዋል። ሁሉም ተቋማትና ሲቪል ሰርቫንቱ ሁሉ ጊዜና አቅማቸውን አሟጠው በአክብሮት ማገልገል መቻልን የዕለት በዕለት ዋና ተግባራቸው ሊሆን እንደሚገባ አመልክተዋል።

እንደ ወይዘሮ ንግስት ገለጻ፤ ቀኑ መከበር አለበት ተብሎ እንደ አገር ሲወሰን ዋና ዓላማው ማገልገል ክብር መሆኑን ለማሳየት ነው። በቅንነት ማገልገል እንደ አገር ሊቀጥል የሚገባው እሴታችን ነው የሚል መልዕክትንም ለማስተላለፍ ነው። ዕለቱ በማገልገል ውስጥ ለሌሎች እርከታን ሊያመጣ የሚችል ሥራን ማከናወን እንደሚቻልም ማሳያ ይሆናል።

እለቱን ተቋማት በተለየ መንገድ እንደሚያከብሩት የገለጹት ወይዘሮ ንግስት፤ የግል ተቋማትን ጭምሮ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ዝቅ ብለው የጽዳት ሥራዎችን በመሥራት ጭምር እንደሚያከብሩት ነው የገለጹት። ከዚህ ባሻገር ተቋማት እንደየተልዕኳቸው የእውቅና መስጫ መርሀ ግብሮችንም እንደሚያካሂዱ ጠቁመዋል። ዝቅ ብሎ ማገልገል ክብር መሆኑን ሊያስገነዝብ በሚችል መልኩ ተቋማት መንቀሳቀስ እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል።

"የአገልጋይነት ቀንን ስናስብ ተገልጋይ እንዳለ ማሰብ ያስፈልጋል። አገልጋይነት ዜጎች ያለ ምንም እንግልት የመንግሥትን አገልግሎት በተቀመጠው የአሰራር ሥርዓት መሠረት ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ነው" ብለዋል ወይዘሮ ንግስት።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ከተቋቋመበት ተልዕኮ አንጻር የሚሰጠው አገልግሎቶች

አገልጋይነት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል








## አሸባሪው ሕወሓት በአማራ ህዝብ ላይ ያለው ጥላቻ ከፖለቲካ አደረጃጀቱ ይመነጫል

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት በአማራ ላይ ያለው ጥላቻ ከህዝባዊ ግንኙነት ሳይሆን ከሽብር ቡድኑ የፖለቲካ

አሸባሪው ሕወሓት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ፎቶ ፡- ገባቦ ገብሬ

## የሽብር ቡድኑ በተደጋጋሚ የወረራ ሙከራ ቢያደርግም በሽንፈት እንዲመለስ ተደርጓል

ገጽ 6






## የአቅመ ደካሞችን መንፈስ ያደሱ የበጎነት ሥራዎች

ገጽ 2

# የአቅመ ደካሞችን መንፈስ ያደሱ የበጎነት ሥራዎች

**በኃይሉ አበራ**

የጳጉሜን ቀናት በተለያዩ ስያሜዎች መከበር ከጀመሩ እነሆ ሶስት ዓመታት ተቆጥረዋል። የዘንድሮ የጳጉሜን ቀናትም የበጎ ፈቃድ ቀን፣ የአምራችነት፣ ቀን፣ የሰላም ቀን፣ የአገልጋይነት ቀን እና የአንድነት ቀን በሚል በመከበር ላይ ይገኛሉ።

በዚህም መሰረት በእያንዳንዱ ቀን የተለያዩ ሁነቶች ሲካሄዱ ሰንብተዋል። ከነዚህም መካከል በበጎነት ቀን የተካሄዱት የበጎ ተግባራት ይጠቀሳሉ።

በእለቱ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በርካታ የመንግሥትና የግል ተቋማት እንዲሁም ግለሰቦች የበጎ ተግባራን በማከናወን እለቱን አስበው ውለዋል። ከነዚህም የበጎ ተግባራት መካከል በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ የተካሄደው የበጎ ተግባር መርሐግብር አንዱ ነበር።

በዕለቱ በክፍለከተማው 335 ቤቶች ለአቅመ ደካሞች ተሰጥተዋል። አስር ሺህ ለሚጠጉ ዜጎች የማዕድ ማጋራት መርሐግብር ተከናውኗል። የአቅመ ደካሞች ቤት እድሳት፣ የትምህርት ቤቶች ጽዳት እና ሌሎች የበጎ ሥራዎችም በእለቱ ከተከናወኑ ተግባራት ውስጥ ይጠቀሳሉ።

በአቅመ ደካማ ቤት እድሳት ተደርጎላቸው ርክክብ ከተደረገላቸው መካከል አቶ በቀለ ሆርዶፋ ይገኙበታል። አቶ በቀለ ለአርባ ዓመታት በደሳሳ ቤት ውስጥ እኖር ነበር ያሉ ሲሆን አሁን በተደረገላቸው የመልሶ ግንባታ አዲስ ቤት በመግባታቸው ደስተኛ መሆናቸውን ገልጸዋል።

አቶ በቀለ ለለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ፣ ለወረዳ ስድስት፣ ለመንግሥት እና ለባለሀብቶች ምስጋና አቅርበዋል። ኢትዮጵያ በአራቱም ማዕዘን ሰላሟ የተጠበቃ እና የሚፈታተኗትን አቅም እንዳይኖራቸው፣ አገር ሰላም እንዲሆን አዲሱ ዓመት የአብሮነት የፍቅር ዘመን እንዲሆንም ተመኝተዋል።

በዕለቱ የተገኙት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሂክማ ሀይረዲን፣ ለባለ ሀብት እና ለተለያዩ በጎ ሰዎች ብቻ ይሰጥ የነበረው የበጎነት ሥራ አሁን ግን ትልቁ የመንግሥት ትኩረት ነው ብለዋል።



በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን፣ እናቶችን፣ ሴቶችን፣ ህጻናትን እና አባቶችን የመደገፍ ሥራ እየሰራን ነው ብለዋል።

ወይዘሮ ሂክማ በመርሐ ግብሩ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት የበጎ ተግባር ሥራዎች በአንድ በኩል የመንግሥትን ችግር ባለሀብቱ የሚተባበርበት እና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ዜጎች የሚደገፉበት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት በጎ ሥራውን ለሰሩ አካላት ምስጋና የሚያቀርብበት፣ ተጠቃሚ የህብረተሰብ ክፍሎች ፈጣሪያቸውን የሚያመሰግኑበት ነው።

አባቶች እና እናቶች ለአገር አንድነት እና አብሮነት የበለጸገች ኢትዮጵያን ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ በጸሎታቸው እና ዱአቸው እንዲያግዙም ወይዘሮ ሂክማ አሳስበዋል።

ጳጉሜን አንድ የበጎነት ቀን በአገር አቀፍ ደረጃ በጎ አድራጊዎችን የምናመሰግንበት ቀን መሆኑን አስታውሰው በከተማዋ በሁሉም ክፍለ ከተሞች የሚተገበረው የተለያዩ በጎ ሥራዎች በቀጣይነት ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ጠቁመዋል።

ዜጎችም በየአካባቢያቸው ለሰላም መጠበቅ እንዲሰሩ አቅመ ደካሞች በፀሎታቸው እንዲተጉ አሳስበዋል። መልካም የአዲስ ዓመት በዓልም ለሁሉም እንዲሆን ተመኝተዋል።

በማዕድ ማጋራት ሥራውም በግ፣ ዶሮ፣ እንቁላል፣ ዱቄት፣ ፓስታ እና መኮሮኒ እንዲሁም ዘይት ተሰጥቷል።

የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጥላሁን ሮባ በበኩላቸው በክፍለ ከተማው በተሰሩ ሰው ተኮር ሥራዎች ላይ ሚና ለነበራቸው ባለሀብቶች እና መላው የህብረተሰብ ክፍል ምስጋና አቅርበዋል።

ቤታቸውን ማደስ ያልቻሉ ዝናብ የሚያፈስባቸው ከ100 በላይ አቅመ ደካሞች ቤቶች ፈርሰው ድጋሚ የተገነቡ ናቸው ብለዋል። በጳጉሜን አንድ የበጎነት ቀን በ10ሩም ወረዳ 335 ቤቶች ለአቅመ ደካሞች የተላለፉ ሲሆን በማዕድ ማጋራት ዘጠኝ ሺህ 585 በዝቅተኛ ኑሮ የሚገኙ ዜጎች ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል።

መንግሥት የህዝብን ኑሮ ለማሻሻል በትጋት እየሰራ ባለበት በዚህ ወቅት ለ3ኛ ጊዜ ጦርነት የከፈተው የሽብር ቡድኑ ትኩረታችንን ከልማት እንድናነሳ ለማስተጓጎል በመሆኑ ህዝባችን ከመንግሥት እና ከሀገር መከላከያ ጎን በመሆን ሊቀለብሰው እንደሚገባም አመላክተዋል።

በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በ2014 በሁሉም በጎ ፈቃድ መርሐ ግብር 329 ሺህ በጎ ፈቃደኞች የተሳተፉ ሲሆን 73 ሺህ 335 ዜጎች ማዕድ ማጋራት መቻሉን የክፍለ ከተማው በጎ ፈቃድ ቡድን አስተባባሪ ወይዘሮ አብዮት በቀለ ለአዲስ ዘመን ገልጸዋል። በክረምቱም 224 ሺህ በጎ ፈቃደኞች መሳተፋቸውን ጠቁመዋል።

# የሥጋ ደዌ በሽታን ለመከላከል ቶሎ ወደህክምና መሄድ ብቸኛው መፍትሄ ነው

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ሥጋ ደዌ በቀላሉ በህክምና የሚድን ተላላፊ በሽታ በመሆኑ በበሽታው የተጠቁትን ሰዎችን ቶሎ ወደ ጤና ተቋም በመውሰድ በሽታውን መከላከል እንደሚገባ ተገለጸ።

አለርት ሆስፒታል ሰሞኑን በሥጋ ደዌ በሽታ ዙሪያ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ባካሄደበት ወቅት፣በመድረኩ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረቡት ዶክተር ቅድስት ቦቦሻ እንደገለጹት፤ በሽታው በተለምዶ እንደሚባለው እርግማን የሚይዝና የማይድን ሳይሆን በህክምና በቀላሉ የሚድን ተላላፊ በሽታ በመሆኑ በበሽታው የተጠቁትን ሰዎችን ቶሎ ወደ ጤና ተቋም መውሰድ ያስፈልጋል ።

በሽታው በባክቴሪያ ህዋስ አማካኝነት ከሰው ወደ ሰው እንዲሁም ከእንስሳ ወደ ሰው የሚተላለፍ መሆኑን በጥናት መረጋገጡን የጠቀሱት ዶክተር ቅድስት፣ በሽታው በዋናነት የሚተላለፈው በበሽታው ክፉኛ ከተጠቁት ሰዎች በአፍንጫቸው በኩል ከሚወጡ የባክቴሪያ ክምችት ባላቸው ጠብታዎች አማካኝነት መሆኑን ተናግረዋል።

ምንም እንኳ አንዳንድ አገሮች በሽታው ፈጽሞ አገራቸው እንዳይገባ ማድረግ የቻሉ ቢሆንም እንደ ደቡብ አሜሪካ ባሉ አገሮች የበሽታው ስርጭት አሁንም ከፍተኛ ነው ያሉት ዶክተር ቅድስት፤እንደ አጠቃላይ በዓለም የበሽታው ስርጭት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱን አስገንዝበዋል።

የህመም ስሜት የሌላቸው ነጣ ያሉ ምልክቶች፣ጠጠር ያሉ እባጮች፣የጡንቻዎች መዛልና የነርቮች መተለቅ የሥጋ ደዌ ምልክቶች መሆናቸውን የተናገሩት ባለሙያዋ፣ በሽታው ክትባት ስለሌለው በሽታውን ለመከላከል



ከሁሉም በላይ ንጽህና አጠባበቅ ላይ ተገቢ ትኩረት መስጠት ጠቃሚ መሆኑን መክረዋል።

ለባክቴሪያው ተጋላጭ ከሆኑት ሰዎች መካከል 5 በመቶ ብቻ ምልክት የሚያሳዩ ሲሆን 95 በመቶው የሚሆኑት በሰውነት የመከላከል አቅማቸው ባክቴሪያውን ስለሚያዳክሙት ምልክት ላይታይባቸው ይችላል ያሉት ዶክተር ቅድስት፤በበሽታው ከተጠቁ በኋላ የህመም ምልክቱ ከሁለት ሳምንት እስከ 40 ሊቆይ እንደሚችል አስገንዝበዋል።

በሆስፒታሉ የቆዳና የሥጋ ደዌ ስፔሻሊት የሆኑት ዶክተር ሽመልስ ንጉሴ በበኩላቸው የበሽታው ስርጭት በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች የሚስተዋል ቢሆንም በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ከፍተኛ መሆኑን ገልጸው፣ በህብረተሰቡ መካከል እንደሚወራው በሽታው በመጨባበጥ የሚተላለፍ ስላልሆነ ሥጋ ደዌ ያለበት ሰው ማግለል ተገቢ እንዳልሆነና ከአፍንጫ በሚወጣ ፈሳሽም በሽታው የሚተላለፍም ቢሆን እንኳን ወደ ሌላ ሰው የመተላለፍ እድሉ 5 በመቶ ብቻ መሆኑን ተናግረዋል።

በሽታው ቶሎ ህክምና ካላገኘ ነርቮችን ክፉኛ እንደሚጎዳና ሰውነት እንደሚያደርቅ የተናገሩት ዶክተር ሽመልስ፣ ነገር ግን በጤና ተቋማት የሥጋ ደዌ መድኃኒቶች በነጻ የሚሰጡ መሆናቸውና መድኃኒቶቹን በአግባቡ ከተጠቀሙ መዳንና ሥርጭቱንም መግታት እንደሚቻል ገልጸዋል።

ከሁሉም በላይ ግን ሕብረተሰቡ ሥጋ ደዌ በህክምና የሚድን ተላላፊ በሽታ መሆኑን በመገንዘብ በበሽታው የተጠቁትን ሰዎች ከመደበቅ ይልቅ ቶሎ ወደ ጤና ተቋም ሄደው ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል ።



## “አሸባሪው ሕወሓት የከፈተውን ጦርነት በአንድ እጃችን እየተከላከልን በሌላ እጃችን ልማታችንን እናስቀጥላለን”

አቶ መለሰ አለሙ
- የአዲስ አበባ ብልጽግና ፓርቲ ጽህፈት ቤት ኃላፊ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት ለሦስተኛ ጊዜ የከፈተውን ጦርነት በአንድ እጃችን እየተከላከልን በሌላ እጃችን ደግሞ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በማስፋት ልማታችንን እናስቀጥላለን ሲሉ የአዲስ አበባ ብልጽግና ፓርቲ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ገለጹ። በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የ 60 ቀናት ሰው ተኮር ፕሮጀክቶች ተመርቀዋል።

የአዲስ አበባ ብልጽግና ፓርቲ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ መለሰ አለሙ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የ 60 ቀናት ሰው ተኮር ፕሮጀክቶችን ከትላንትበስቲያ መርቀዋል። በምረቃ ስነ ስርዓቱ ላይም ወቅቱ በኢትዮጵያ አሸባሪው ሕወሓት ለሦስተኛ ጊዜ የከፈተውን ጦርነት በአንድ እጃችን እየተከላከልን በሌላ እጃችን ደግሞ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለማስፋትና ልማታችንን ለማስቀጠል ያለንን ቁርጠኝነት የምናረጋግጥበት ጊዜ ነው ብለዋል።

በሽብር ቡድኑ የተከፈተው ጦርነት በሁሉም ኢትዮጵያውያን ላይ በመሆኑ፤ ሁሉም ጦርነቱን ለመመከትና ለማክሸፍ የተጀመረውን የብልጽግናና የእድገት ጊዜን ወደፊት ማስቀጠል እንዳለበት አቶ መለሰ ተናግረዋል። ከመንግሥት ጎን በመቆም የግንባር ሚናን መወጣት፤ በሌላ መልኩ በደጀን የአካባቢን ሠላም በመጠበቅ የሽብር ቡድኑን እኩይ ተግባር የማክሸፍ ከፍተኛ ኃላፊነት መወጣት እንደሚገባ አመላክተዋል።

ከጦርነቱ በስተጀርባ ያሉ የኢትዮጵያ ጠላቶች አንድ ላይ አብረው የሚሳተፉበት ዋናው ምክንያት ለኢትዮጵያውያን ግልጽ ነው ያሉት አቶ መለሰ፤ “እኛ ከድህነት ወጥተን ወደ ብልጽግና ለመገስገስ ያለን ፍላጎትና በሂደቱ ያገኘናቸው ስኬቶች ምን ያክል ወደ ፊት ሊወስዱ እንደሚችሉ የሚያውቁ፤ ከዚህ ጉዟችን ለማደናቀፍ አልመው እየተንቀሳቀሱ ነው። ከቻሉ አገርን ለማፍረስ ካልሆነም ለማዳከም የሚያደርጉት ጥረት አካል ነው” ብለዋል።

አቶ መለሰ፤ እነዚህን ፈተናዎች እየተቋቋምን በልማት መንገዳችን መቆማችን የግድ የሚል ወሳኝ ምዕራፍ ላይ እንገኛለን በማለት፤ "በአንድ እጃችን አሸባሪው ህወሓት የከፈተብንን ጦርነት እየተከላከልን በሌላኛው እጃችን ደግሞ የጀመርነውን የብልፅግና ጉዞ ወደ ፊት እናስቀጥላለን” ሲሉ ተናግረዋል።

በ60 ቀናት ውስጥ የተሠሩ ፕሮጀክቶች የተጓተቱትን በማጠናቀቅ እንዲሁም አዲስ ፕሮጀክቶችን በመጀመር በህዝቡና በባለሀብቱ በጎ ፈቃደኝነት፣ በአመራሩ ብቃት እና በሰራተኛው ትጋት በአጭር ጊዜ ውስጥ በወጪ ቆጣቢነት በጥራት ከተጠናቀቁት ፕሮጀክቶች አንዱ መሆኑንም አቶ መለሰ አስታውቀዋል።

ፕሮጀክቶቹ በክፍለ ከተማው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙትን የማህበረሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ የሚያደርጉ እንደሆኑ በመግለጽ፤ ተግባሩ "በአንድነት እንደመር" የሚለውን የ2015 አዲስ ዓመት መቀበያ መሪ ቃል የበጐ ፈቃድ አሻራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በመደጋገፍ ኢትዮጵያን ለማበልጸግ የተጀመረ አንዱ ማሳያ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ከትላንትበስቲያ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የተመረቁት የ 60 ቀናት ሰው ተኮር ፕሮጀክቶች በአስቸጋሪ ህይወት ውስጥ የነበሩ 455 አባወራዎችን የቤት ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥም 70 ቤቶች አዲስ የተገነቡ እንዲሁም 385ቱ እድሳት የተደረገላቸው ናቸው። ለአዲሱ ግንባታና እድሳት ሥራም 129 ሚሊዮን ብር ጠቅላላ ወጪ ተደርጐባቸዋል።

ዜና

# የሽብር ቡድኑ ሰርጎገቦችን ለማስገባት የሚያደርገው ጥረት እየከሸፈበት ነው

ጌትነት ተስፋማርያም



ሐራ፡- የሕወሓት ሽብር ቡድን በተለያየ መንገድ ሰርጎገቦችን ወደሐራ ከተማ ለማስገባት የሚያደርገው ጥረት እየከሸፈበት ነው ሲሉ በሰሜን ወሎ ዞን የሐራ ከተማ ምክትል ከንቲባ አቶ ሙሐመድ ሰይድ ገለጹ።

አቶ ሙሐመድ ሰይድ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሽብር ቡድኑ ወረራውን ለማስፋፋት እንዲመቸው ታጣቂዎቹን በተለያየ መንገድ ወደከተማ እንደሚያስገባ ይታወቃል። ይህ ጥረቱ ግን በቅንጅታዊ የጸጥታ ስራ እየከሸፈበት ይገኛል።

በከተማዋና በዙሪያዋ ባሉ አካባቢዎች የጸጥታ ኃይል ተሰማርቶ አስፈላጊውን ጥበቃ እያደረገ ይገኛል ያሉት አቶ መሐመድ፤ በከተማዋ በየጊዜው በሚደረግ ፍተሻና የቁጥጥር ስራ ከ60 በላይ ጸጉረ ልውጦች መያዛቸውን አስታውቀዋል።

ከዚህ ባለፈ እብድ መስለው ሲሰልሉ የነበሩ ሁለት የሕወሓት ሽብር ቡድን አባላት መገኘታቸውን ጠቁመው፤ በቤተክርስቲያንና በከተማ ውስጥ የአዕምሮ በሽተኛ መስለው ሲንቀሳቀሱ እንደነበር አቶ መሐመድ ተናግረዋል።

እብድ መስለው የተገኙትም ሰዎች አስፈላጊው መረጃ ተጣርቶባቸውም ለወራሪው ቡድን መረጃ ሲያቀብሉ እንደነበር ተረጋግጧል ያሉት አቶ ሙሐመድ፤ ግለሰቦቹ ለሚመለከተው የጸጥታ አካል መተላለፋቸውን ገልጸዋል።

በተጨማሪነት አንድ ወንድና አንድ ሴት የሽብር ቡድን አባላትም በከተማ ውስጥ እኩይ አላማቸውን ለማስፈጸም ሲንቀሳቀሱ መያዛቸውን ምክትል ከንቲባው አስታውቀዋል።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ሁለተኛ ወረራውን በአማራና አፋር ክልሎች በፈጸመበት ወቅት በውሸት የአዕምሮ ህመምተኛ የሆኑ ሰላዮቹ ያሰማራ እንደነበር ይታወቃል። ከዚህ ባለፈ በስደተኛ ስም ሰርጎገቦቹን ወደከተማ ያሰማራ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ መሆኑን አቶ ሙሐመድ ገልጸዋል።

እንደ ምክትል ከንቲባው ገለጻ፤ የሽብር ቡድኑ በአማራና አፋር ክልሎች ላይ ወረራ ከፈጸመ በኋላ ጥቃቱን ወደተለያዩ አካባቢዎች ለማስፋፋት ቀድሞ ውዥንብር ፈጣሪዎችን በከተማዎች ውስጥ እንደሚያሰማራ ህብረተሰቡ ተገንዝቧል።

በመሆኑም በእያንዳንዱ መንደርና ገበያ ስፍራዎች ጭምር ለጸጥታ አካላት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በተገቢው ወቅትና አግባብ እያቀበለ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም በአሉባልታና በሃሰተኛ መረጃ የተነሳ የተወሰነው የሐራ ከተማ ነዋሪ ውዥንብር ውስጥ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ላይ በየመዝናኛውና በህብረተሰቡ ዘንድ የሃሰት መረጃ የሚነዙ አካላትን መቆጣጠር የሚያስችል የጸጥታ ስራ በመከናወኑ ውጤት መገኘቱን ጠቁመዋል።

በአሁኑ ጊዜ ሐራ ከተማ በተረጋጋና ሰላማዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ስትሆን የከተማዋ ነዋሪ በተደራጀ ሁኔታ አካባቢውን ከመጠበቅ ባለፈ ለጥምር ጦሩ ድጋፍ እየቀረበ ይገኛል ብለዋል።

አቶ ሙሐመድ እንዳስታወቁት፤ ህብረተሰቡ በየቀኑ ምግብ በማዘጋጀት ግንባር ላይ ለሚገኘው ጥምር ጦር እያቀረበ ይገኛል።

የወልዲያ፣ መርሳና ሐራ ከተሞችም የግንባር ድጋፎች ላይ በቅንጅት እየሰሩ መሆኑንና ከተለያዩ አካባቢዎች የሚቀርበውን ድጋፍ በማስተባበር ደጀንነታቸውን በማሳየት ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ሐራ ከተማ በወልዲያና ጭፍራ ከተሞች መካከል የምትገኝ የሰሜን ወሎ ዞን ከተማ ነች።

# የከተማ አስተዳደሩ ለሀገር መከላከያ ሰራዊት ድጋፍ አደረገ

ፍቃዱ ዴሬሳ




አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሶስተኛ ጊዜ በትህነግ ቡድን የተከፈተውን ጦርነት ምክንያት በማድረግ ለሀገር መከላከያ ሰራዊት የመጀመርያ ዙር የዓይነት ድጋፍ አደረገ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ከከተማ አስተዳደሩ ሁሉም ክፍለ ከተሞች እንዲሁም ከተለያዩ ተቋማት የተሰበሰበውን ድጋፍ ለብሄራዊ ሀብት አሰባሳቢ ኮሚቴ አስረክበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ለሀገር መከላከያ ሰራዊት ህያው የሆነውን ደጀንነቱን የተለያዩ ድጋፍ በማድረግ እያሳየ የቀጠለ መሆኑን ተናግረዋል። የተጀመረው የድጋፍ ማሰባሰብ መርሀ ግብርም የሚቀጥል መሆኑን ወ/ሮ አዳነች አቤቤ በርክክብ ስነስርዓቱ ላይ አስታውቀዋል።

ድጋፉ አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግ ለሀገር መከላከያ ሠራዊት የተደረገ የተለያዩ የምግብ ነክና አልባሳት መሆኑን ተናግረው፣ እንዲህ ባለ ወቅት መከላከያ ሰራዊቱ የሀገርን ክብርና ሉአላዊነት ለማስቀጠል እየተዋደቀ በመገኘቱ ኢትዮጵያውያን ከጎን ሊቆሙለትና ደጀንነታቸውን ሊገልፁለት ይገባል ብለዋል።

ለሁሉም ዜጎች ብሄራዊ ኩራት ለሆነውና ለሕይወቱ ሳይሳሳ ለሀገርና ለሕዝብ ደኅንነት እየተዋደቀ ለሚገኘው ለሀገር መከላከያ ሠራዊት የመዲናዋ ነዋሪዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ድጋፍ ማሰባሰብ መቻላቸውን ከንቲባዋ ተናግረዋል።

የኢፌዲሪ መከላከያ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ወ/ሮ ማርታ ለዊጂ በበኩላቸው ከተማ አስተዳደሩ በአጭር ቀናት ውስጥ ድጋፉን በማሰባሰብ ደጀንነቱን መግለጹ የሚያስመሰግነው መሆኑን ገልጸዋል።

መንግሥት ለሰላም ያሳየውን ከፍተኛ ጥረት ወደኋላ በመግፋት ሽብርተኛው የትህነግ ቡድን ለሶስተኛ ጊዜ ለከፈተው ጦርነት የአማራና የአፋር ክልል ህዝቦች በከፍተኛ ሁኔታ ደጀንነታቸውን እየገለፁ መሆናቸውን አውስተው፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና መላው የመዲናዋን ነዋሪ ለዚህ ተግባር በግንባር ቀደምትነት በመሰለፍ ደጀንነቱን አሳይቷል ብለዋል።

የትራንስፖርት ሚኒስትርና የብሔራዊ ሎጂስቲክስና ገቢ አሰባሰብ ንኡስ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወ/ሮ ዳግማዊት ሞገስ ኮሚቴው የገንዘብ ማሰባሰብ፣ የአይነት ድጋፎች፣ አስፈላጊ የሆኑ ማሽነሪና ተሽከርካሪዎችን ማሰባሰብ ሥራ እንዲሁም የጤና ዘርፍ ላይ የሚሰጡ ድጋፎችን በማስተባበር እየሰራ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

የሀገር መከላከያ ሰራዊት ጦርነቱ ከተጀመረ አንስቶ ከፍተኛ ዋጋ እየከፈለና ሀገርን የደፈረ የባንዳ ኃይል ላይ እርምጃ እየወሰደ በመሆኑ ደጀንነትና አለኝታነትን ማሳየትና በቀዳሚነት ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

የከተማው አስተዳደሩ ከከተማው ህዝብ ያሰባሰበውን 291 ኩንታል በሶ፤ 157 ኩንታል ዳቦ ቆሎ ፤194 በሬዎችና ፤ 532 በጎች እንዲሁም 9949 የቆዳ ሽበጥ በከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ አማካኝነት አስረክቧል።



አቶ ደምለው አልማው

# የኢትዮጵያን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ዜጎች ለአገራቸው ደጀን መሆን ይጠበቅባቸዋል

ሙሳ ሙሐመድ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ቀጣይነት ለማረጋገጥ ሁሉም በውጭ በአገር ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው ደጀን መሆን እንደሚጠበቅባቸው አእላፍ ደጀን ኔትወርክ አስታወቀ።

የአእላፍ ደጀን ኔትወርክ መስራች አቶ ደምለው አልማው በድርጅቱ አንደኛ ዓመት የምስረታ ጉባኤ ላይ በበየነ-መረብ ባደረጉት ንግግር እንደተናገሩት፣ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ቀጣይነት ለማረጋገጥ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ዜጎች ለአገራቸው ሰላም፣ልማትና ዲሞክራሲ የበኩላቸውን ንቁ ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው።

ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ አሰባሳቢነት በሁሉም አገራዊ ጉዳዮች በመሰባሰብ ስለ አገራችን ሰላም፣ልማትና አንድነት መመካከርና መስራት ይኖርብናል ያሉት አቶ ደምለው፤ በኢትዮጵያ የሚስተዋሉ ችግሮችን ከመከሰታቸው በፊትና ከተከሰቱም ወዲያው መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል ብለዋል።

የሰላም ሚኒስቴር አቶ ብናልፍ አንዱዓለም በበኩላቸው ባደረጉት ንግግር፣ ሁላችንም ሰንሰባሰብ በኢትዮጵያ የስበት ኃይልና በሁሉም አገራዊ ጉዳዮች የኢትዮጵያን ቀጣይነት ለማረጋገጥ መሆን አለበት።

በሰሜን የአገሪቱ ክፍል የተካሄደውን ግጭት ተከትሎ ኢትዮጵያን ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ጫናዎች ለመታደግ የዲያስፖራው ያደረጋቸው ንቅናቄዎችና ተሳትፎ ከፍተኛ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ብናልፍ፤በአሁኑ ወቅት በአእላፍ ደጀን ኔትወርክና በዓለም አቀፍ ኒኦ ሶሳይቲ በኩል የተጀመረው ኢትዮጵያውያንን በአንድ ጥላ ስር የመሰባሰብ ሥራ ከጅምሩ ጥሩ ነገሮችን እያሳየን ነው፤አሁንም ይበልጥ ሊሰራበት ይገባል ብለዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን መሰባሰባችን አላማው ኢትዮጵያዊነት ሊሆን ይገባል ሲሉ ሚኒስትሩ፤ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ብናለፍ ገለጻ፣ ምንም ያህል በዜጎች መካከል የአመለካከት፣ የብሔር፣ የባህል፣ የትምህርት ደረጃና የሚኖሩበት አገር የእድገት ደረጃ ቢለያይም እንኳን ሊያሰባስበን የሚችለው ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነው ።

ሁልጊዜም ለመሰባሰብና ለመደራጀት ዋናው አላማና ግብ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንዲፋፉ ሊሆን ይገባል ሲሉ አቶ ብናልፍ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በምንኖርባቸው አገራት ያገኘናቸውን እውቀቶችና ክህሎቶች፣ ተጠቅመን አገራችንን ለማልማት፣ ለማሳደግ፣ ለማበልጸግ፣ ለመለወጥ፣ለማሻገርና ቀጣይነቷን ለማረጋገጥ መሆን መቻል አለበት ብለዋል።

"የሰላም መጥፎና የጦርነት ጥሩ የለውም" ያሉት ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ ሁሌም ሰላም እንድትሆን በያለንበት አገር በኢትዮጵያዊነት ማዕቀፍ ውስጥ በመደራጀት ለአገራችን ሰላምና ዕድገት መስራት ይኖርብናል።ሁሉም ዲያስፖራ በያለበት አገር የኢትዮጵያ የሰላም አምባሳደሮች መሆን እንደሚኖርባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

የአእላፍ ኔትወርክ የቦርድ ሊቀመንበር ኢንጅነር አሰፋ ወዳጆ በበኩላቸው፣ ዲያስፖራው በኢትዮጵያ ያለው ሁለንተናዊ ተሳትፎ በጥናት የተደገፈ አለመሆኑን አመልክተው፤ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በአንድ ጥላ ስር ተሰባሰበን ለኢትዮጵያ ቀጣይ ልማት፣ሰላምና ዲሞክራሲ መጎልበት በትጋት መስራት ይኖርብናል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## “የትግራይ ሕዝብ ከሌሳው ህዝብ በተሻለ ሁኔታ ሳይ ይገኛል“ የሚለው የአሸባሪው ሕወሓት ፌዝ!

በአሸባሪው ሕወሓት ከፍያለ ግፍና በደል እየደረሰባቸው ካሉ የሀገሪቱ ህዝቦች መካከል የትግራይ ሕዝብ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው። ቡድኑ ምንም እንኳን ከውልደቱ ጀምሮ ለትግራይ ሕዝብ እታገላለሁ እያለ ቢምል ቢገዘትም ለሕዝቡ ግን በተጨባጭ ያመጣለት አንዳች ትሩፋት የለም። ይልቁኑ ለእርሱ የዘረፋና የሴራ ፖለቲካ ብዙ የትግራይ ወጣቶች በከንቱ ሕይወታቸውን እንዲገብሩ አደረገ እንጂ!

ቡድኑ በቀደመው ጊዜ በነጻነት ትግል ስም በታሪካዊ ጠላቶቻችን ጨምሮ በሌሎች ኃይሎች በመታገዝ ለ17 ዓመታት ባካሄደው የትጥቅ ትግል ፤ በጥላቻ ፕሮፓጋንዳ እና በማይጨበጥ የታላቂቷ ትግራይ ቅዥት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ወጣቶችን ለእልቂት ዳርጎ የማዕከላዊ መንግሥት ስልጣን ለመያዝ በቅቷል።

በነዚህ 17 ዓመታት ውስጥም የትግራይን ሕዝብ ከፍ ያሉ ማህበራዊ ምስቅልቅሎች ውስጥ እንዲገባ አድርጓል፤ አርሶ እንዳያመርት፣ አምርቶ እንዳይበላ፣ ልጆቹ እንዳይማሩ ፣ተምረውም ለወላጆቻቸው ተስፋ እንዳይሆኑ በጦርነት ዜማ እና ፉከራ የበረሀ ሲሳይ እንዲሆኑ አድርጓል።

ሕዝቡ የሚበላው የሚቀምሰው አጥቶ በሞትና በህይወት መካከል እያጣጣረ በነበረባቸው አስጨናቂ ክፉ ቀናቶች /የ1970ዎቹ የረሀብ ዓመታት/ ፤ ሕዝቡ ሕይወቱን እንዲያተርፍ ከዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ የተለገሰውን የእርዳታ እህል ከጉሮሮው በመንጠቅ ብዙዎችን ለእልቂት ዳርጓል። ከዚህም አልፎ የእርዳታ እህልን ተዋጊ መመልመያ በማድረግ ለሰብዓዊነት ምንም አይነት ደንታ እንደሌለው በተግባር አሳይቷል።

ቡድኑ ገና ከበረሀ ውልደቱ ጀምሮ በትግራይ ሕዝብ ላይ መዝራት በጀመረው የጥላቻ መርዙም ሕዝቡ የተረጋጋና ሰላማዊ ስነልቦና እንዳይላበስ ፤ በራሱ እና ዙሪያው ባለው እውነታ እንዳይታመን ፤እንዲጠራጠር በዚህም የተረጋጋ ስነልቦና እንዳይኖረው አድርጓል ፤እያደረገም ነው። በዚህም የቡድኑ የጨለሙ ነገዎች ሰለባ እንዲሆን አድርጎታል።

የሽብር ቡድኑ ወደ ማዕከላዊ መንግሥት በመጣ ማግሥትም በትግሉ የተሳተፉና ብዙ ዋጋ የከፈሉ ተጋዮችን ከመካድ አንስቶ ፤ብዙ ሲጮህለት የነበረውን የነጻነትና የዲሞክራሲ ጉዳይ ወደ ጎን በመተው የትግራይን ሕዝብ ቡድኑ ለፈጠረው አምባገነናዊ ስርአት ጋሻ አድርጎ ሲያንቀሳቅሰው ቆይቷል ።

በዚህም ስለ ነጻነትና ዴሞክራሲ ብዙ የተሰበከውና ለዚህም ሲል ዋጋ የከፈለው የትግራይ ሕዝብ ተመልሶ የቡድኑ አምባገነናዊ አስተሳሰብና ከዚህ የሚመነጨው ስርአት ባሪያ ለመሆን ተገድዷል። በተለያዩ አደረጃጀቶችም የራሱን ህይወት መኖር የማይችልበት እስር ቤት ውስጥ ገብቷል።

በቡድኑ አመራሮች ብዙ የተዘመረለት የነጻነት ማግስት ተስፋ ፤ከጥቂት የቡድኑ አመራሮችና ለነሱ ፍቃድ ከተገዙ ግለሰቦችና ቡድኖች በስተቀር የማይጨበጥ የቀን ቅዥት ሆኖ ቀርቷል። የነጻነት ትግሉ የአንድ ቤተሰብ /መንደር / ገዥ መደብ በመፍጠር ተቋጭቷል። ይህ ደግሞ ከማንም በላይ የትግራይን ሕዝብ ልብ የሰበረ ሆኗል።

ቡድኑ በስልጣን ዘመኑም ቢሆን የሀገርን ሀብትና ንብረት ከመዝረፍ ፤ባልተገባ ትምክህትና እብሪት ሀገርና ሕዝብን ዋጋ ከማስከፈል፤ የሃገር አንድነትንና የሕዝቦች ተቻችሎ የመኖር እሴቶችን የሚፈታተኑ ተግባራት ከመፈጸም ባለፈ፤ ሲምል ሲገዘት እንደነበረው ለትግራይ ሕዝብ አዲስ ቀንና ለውጥ አለመጣለትም ፤ የተሻሉ ነገዎችን ሊያመጡ የሚችሉ ማህበራዊ ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መደላደሎችንም አልፈጠረለትም።

ከዚህ ይልቅ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን እና ጎረቤት ሀገራት ሕዝቦች ጋር ተቻችሎና ተፈቃቅሮ እንዳይኖር የሚያደርጉ ሴራዎችን በመግመድ ጥላውን ሳይቀር እንዲጠራጠር በማድረግ የቡድኑ ሴራ ሰለባ እንዲሆን፤ በተለይ ወጣቱን ትውልድ በነገር ሁሉ ተስፋ ቢስ ሆኖ በደሙ የቡድኑ እድሜ ማራዘሚያ እንዲሆን አድርገውታል ።

ቡድኑ በህዝባዊ እምቢተኝነት ከስልጣን ከተወገደ ማግስት ጀምሮ እየታየ ያለውም ይሄው እውነታ ነው። እንደቀደመው ጊዜ ቡድኑ የከዳው የትግራይ ሕዝብ ጉያ በመግባት ፤በሕዝቡ ላይ አዳዲስ የጠላትነት ትርክቶችን በመፍጠር ሕዝቡን ለተጨማሪ ስቃይና መከራ፤ ታዳጊዎችንና ወጣቱንም ለእልቂት እየዳረገ ነው።

ቀደም ሲል ባካሄዳቸው ሁለት የእብሪት ጦርነቶች በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ወጣቶችን ለእልቂት ዳርጓል ፤ ህጻናቱን ሳይቀር የጦር ሜዳ የጥይት ማብረጃ ፤ የትግራይን ሕዝብ ማህበራዊ ህይወት ከማመሰቃቀል አልፎ ስለ ነገዎቹ ተስፋ ቢስ እንዲሆን አድርጎታል ።

እንደቀደመው ዘመን ቡድኑ ለሕዝቡ የቀረቡ የሰብአዊ ድጋፎችን በመዝረፍ ሕዝቡን ለከፋ የረሀብ አደጋ እያጋለጠ፤ ታጣቂ መመልመያ እያደረገ ነው። በዚህ የቡድኑ እኩይ ተግባርም ብዙዎች የሚላስ የሚቀመስ አጥተው አቅራቢያቸው ወደሚገኙ ክልሎች ተሰድደዋል። ሳይወዱ በግድ ጠብመንጃ ይዘው ለቡድኑ እኩይ አላማ ሰለባ እየሆኑ ነው ።

ይህ ሁሉ በአደባባይ እየሆነ ባለበትምሁኔታ በቅርቡ ከቡድኑ አፈትልኮ የወጣው መረጃ “የትግራይ ሕዝብ ከሌሎች የሀገሪቱ ሕዝቦች በተሻለ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙ “በሁኔታ ግምገማው በግልጽ አስፍሮት ተገኝቷል። ይህ የግምገማ ውጤት የቡድኑ አመራሮች ዛሬም የቱን ያህል ለትግራይ ሕዝብ ደንታ ቢስ እንደሆኑና በሕይወቱ እየቆመሩ እንደሆነ በተግባር ያሳየ ነው።

ከዚህ በላይ የቡድኑ አመራሮች ሰብአዊነት የሚባል ነገር እንደሌላቸው፤የታወሩበት የጥፋት ተልዕኮ የቱን ያህል ከሰብዓዊነት እንዳወጣቸው እና እንዳሳወራቸው ያመላከተ ነው ። እንደ ትናንቱ በትግራይ ሕዝብ ስም ከመማልና ከመገዘት ባለፈ ለህዝቡ ምንም አይነት ተቆርቋሪነትም ሆነ ደንታ እንደሌላቸው በተጨባጭ ያሳየ ጭምር ነው!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# አፈትልኮ የወጣው የአሸባሪው ሕወሓት ሰነድና ምንነቱ

ግርማ መንግሥቴ

ሰሞኑን በየማህበራዊ ሚዲያው እየተንከራተተ ያለውን፣ “የማጠቃለያ ምዕራፍ አካሄድና ስትራቴጂ” (ነሐሴ 8፣ 2014 ዓ.ም መቐለ)ን አነበብኩት። ለምን እንደሆነ አላውቅም፣ ምንም አልተሰማኝም። ምናልባት ይህ አይነቱ አገርና ህዝብን ማእከል ያላደረገ ፖለቲካና እንቅስቃሴውን ስለለመድኩት ሊሆን ይችል ይሆናል፤ ምናልባትም “ተጨፈጨፉ”፣ “በጅምላ ተቀበሩ”፣ “ኢትዮጵያን ማፍረስ …” እና ሌሎችንም በሰማሁበት ጆሮዬ ይህችን፣ “የማጠቃለያ ምዕራፍ አካሄድና ስትራቴጂ” ላይ የሰፈረችውን ከምንም ስላልቆጠርኳት ይሆን … ግን አሁንም ምንም አልተሰማኝም። ያ ማለት ግን፣ ቢሰማኝም ባይሰማኝም …. መባል ያለበት መባል የለበትም ማለት አይደለም። በመሆኑም ይህንን ሰነድ ተብዬ ሰነድ አስመልክተን መባል ያለበትን ብለን ታሪካዊ ሀላፊነታችንን እንወጣለን።

ሰነዱ ባለ 12 ገፅ ነው። እኔ የተመለከትኩት በፒዲኤፍ የታሰረውን ነው። በመሆኑም በመከፈቻው ከፍቼ ተመለከትኩት። እውነትም ያው ነው። ድሮም የነበረ ድብቅ አመለካከትና ስሜት የታጨቀበት፤ ድሮም የነበረ ምኞት የተንፀባረቀበት፤ ድሮም የነበረ ህልም የተፈታበት (ከተፈታ) … እንጂ ሌላ ሆኖ አላገኘሁትም። አንድም ቦታ 120 ሚሊዮን ቁጥር ያለውን ህዝብ እንደ አንድ ህዝብ ያላየ ሰነድ ነው።

አንድም ቦታ እንደ አገር አስቦ ለህዝብ ጥቅም ሲንቀሳቀስ ያልታየ ሰነድ ነው። አንድም ቦታ ኢትዮጵያን እንደ አገርና ምድር ቆጥሮ ስሟን ሊጠራ ያልደፈረ ሰነድ ነው። ቅርድብ አዳሪ እንጂ አንድም ቦታ ስትራቲጂክ ሆኖ ሊገኝ ያልቻለ ሰነድ ነው። አንድም ቦታ …..። ባጭሩ፣ ስሜት ሰጪ አሃዶች የጎደሉት ብቻ ሳይሆን ጭራሽም የሌሉት ሰነድ ነው። በመሆኑም “ስትራቴጂ” የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ አይመጥነውም።

ሰነዱ ገና ከርእሱ ጀምሮ፣ “የማጠቃለያ …” ማለቱን ተከትሎ እራሱ በራሱ የራሱን ውድቀት ያወጀ ሰነድ ነው። ሰነዱ የህዝብን ልብ ያገናዘበ ሳይሆን የጠመንጃን አፈሙዝ የተማመነ በመሆኑ ወደ ማንም ልብ ውስጥ ሊዘልቅ የቻለ ሰነድ ሆኖ አይደለም። የማንንም ቀልብ ስቦ የማንንም ልብ ሊያሸፍት የሚችል ሰነድ ሆኖ ሊገኝ አልቻለም። ባጭሩ፣ እዛው፣ ለዛው፣ በዛው … የተዘጋጀ ሰነድ ሆኖ ከማለፍ ሊያመልጥ አልቻለም። የተወሰኑትን ከሰነዱ እየቆነጠርን እንያቸው።

“በጦርነት ሂደት ውስጥ የመረጃ ልዕልና ለማግኘት እና በርካታ ሃይሎችን ከጎንህ ለማሰለፍ ከሚያስችሉ ሁኔታዎች አንዱ፣ ለዓለም አቀፉ ማህብረሰብ ችግሮችን በሰላም ለመፍታት ቁርጠኝነት እንዳለህ አስመስለህ እራስህን ማቅረብ መሆኑ ሊረሳ አይገባም” ከሚለው መረዳት የሚቻለው አንድ አቢይ ጉዳይ ነው፤ በተለይ የዛሬ አመት አካባቢ ኢትዮጵያ በተለይ በምእራቡ ዓለምና አሜሪካ ሚዲያዎች (ቢቢሲ፣ ሲኤንኤን … እኔ ሌሎች በርካቶችም) ምን ያህል በሀሰት ፕሮፓጋንዳ ስትናጥ የነበረ መሆኑን ትንሽ ወደኋላ መለስ ብሎ ማስታወስ ተገቢ መሆኑን ለማየት ይረዳል። ነገሩ እውነትና ንጋት … እንዲሉ ሆኖ እንጂ፤ ምን ያህል የሀሰት ፕሮፓጋንዳ አጥለቅልቋት፤ ጭራሹንም ጠራርጎ ሊወስዳት እንደ ነበረ ለሁላችንም የተሰወረ አይደለም።

“የሕዝባችን ዘላቂ የሰላም ዋስትና የሚረጋገጠው በይምሰል በቀረበው የዐቢይ የሰላም አማራጭ ሳይሆን፣ በክንዳችን ብቻ መሆኑን በፅኑ እናምናለን” የሚለውና አገርና ህዝብን ወደ ድንጋይ ዘመን (ስቶን ኤጅ) የሚመልሰውን ዓረፍተ ነገር ጠቅሱ ከማለፍ ሌላ ስለ እሱ ምንም ማለት አይቻልም እና እንዝለለው።

ሌላው የሰነዱ አስኳል እና የስትራቴጂው ማእከል/ አርቢት “ለትግራይ ሕዝብ ያለው ጭፍን ጥላቻ …፣ ጫፍ የወጣ ጥላቻ …፣ የትግራይ ሕዝብ ጠላት ….” የሚለው ሲሆን፤ ይህም ምናልባት እንደ አንድ የትግል ስልት (መሳሪያ) ቢያገለግል ከሚል የተሰደረ እንጂ መሬት ላይ ያለ እውነታ አይደለም።

ይህ ፀሐፊ እስከሚያውቀው ድረስ ማንም ወገን፣ ክልልም እንበለው ብሔረሰብ በትግራይ ህዝብ ላይ “ጭፍን ጥላቻ …” ቀርቶ ቅያሜ እንኳን የለውም። “ጭፍን ጥላቻ …” ቢኖር ኖሮ እውነት እስካሁን አለን? እንኖርስ ነበር? በእውነት ገና ለገና ወንዝ ለማያሻግር ፖለቲካ ተብሎ የብሽሽቅ ፖለቲካን ህዝባዊ መልክ ለመስጠት መጣር … በእውነት ያስተዛዝናል።

አገርና ህዝብ ይቀጥላል ሲባል እኮ የቃላት ጨዋታ አይደለም። አለመሆኑን ደግሞ የእነ ሩዋንዳ በዛው አለመቅረት፣ የኤርትራና ኢትዮጵያ እዚህና እዚያ መመላለስ …. ወዘተ በሚገባ ያስተምራልና። ለሚያልፍ ቀን የማያልፍ ስህተት ውስጥ መግባቱ ተገቢ አይደለም። እንደ ጥሩ “ስትራቴጂ” ተወስዶም ሊፎከርበት አይገባም።

ሌላው ሰነዱ እንደ ስትራተጂክ ሰነድ ሊወሰድ የማይችልበትና ሊወቀስ የሚገባው ከህፃናት መብቶች አኳያ ሲሆን፤ ለዚህ ማስረጃው ደግሞ በየግንባሩ የሚታዩት፣ ከእነሱ ቁመትና ክብደት የተሸከሙት ክላሽ የሚበልጣቸው ህፃነት መታየታቸው ነው። ከዚህ ሰነድ መረዳት እንደሚቻለው ደግሞ “የትግራይ ወጣቶችን አሁን የሚደረገው ትግል ወደ አዲስ አበባ የመጨረሻ ምዕራፍ ትግላችን እንደሆነ በማሳመን …” የህፃናትና ወጣቶች ወደ ጦር ሜዳ የመሄዱ ጉዳይ የሚቀጥል ይሆናል ማለት ነው። ይህ ደግሞ ሌላውና ትልቁ ስህተት ነውና ለ“የማጠቃለያ ምዕራፍ አካሄድና ስትራቴጂ” መውደቅ አቢይ ምክንያት ነው።

ምናልባት ከዚህ “ስትራቴጂክ” የሚባለው ሰነድ ውስጥ ለግንዛቤ ይረዳል ተብሎ ሊታሰብ የሚችለው “በጠላት ላይ ሽብር፣ ፍርሃትና የስነ ልቦና ጫና መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣ ሽብር የሚያስፋፉ እና በመሀል አገር ያለው ሕዝብ ሳይቀር በመንግሥት አቅም ላይ ያለው እምነት እንዲሸረሽር የሚያደርጉ መረጃዎች በአገር ውስጥና በውጭ ሚዲያዎች በሙሉ ማዳረስ ያስፈልጋል። […] ይሄም በፓርቲያችን የፕሮፖጋንዳ ክፍል በሚቀረፁ መልዕክቶችና ይዘቶች የሚመራና በላይኛው አመራሮች ክትትል የሚደረግበት ይሆናል” የሚለው ሲሆን፣ እዚህ ያለነው ምን ያህል የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ጠራርጎ ሊወስደን እየተዘጋጀ መሆኑን እንገረዳ ዘንድ ማስቻሉ ነው።

ይህንን እድል በመጠቀም መረጃዎችን “ፍሬውን ከገለባው” እንደሚባለው በሚገባ መለየት ይገባናል። “ፋሽስት ዐቢይን ለመበተን፣ ፖለቲካዊ ማህበራዊ ችግሮች ማስቀጠል” የሚለው ንኡስ ርእስም (ርእሱ ብቻ) የሚለው አለና ሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን እንደ አንድ የተደገሰለት ድግስ ወስዶ የውስጥ ሰላሙን መጠበቅ ይኖርበታል።

ሌላውና አሳሳቢው ጉዳይ፣ በሰነዱም ላይ በአፅንኦት እንደ ሰፈረው፣ “የሚጠብቀን ረጅምና መራር ትግል …” ነው የሚለው ነው። ይህ በህዝብና አገር ላይ ረጅም የስቃይና የጦርነት ዘመን ዜና ከማወጅ የተለየ አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ መስማት የሚፈልገው የጦርነቱን ፍፃሜና የሰላም መስፈንን ዜና ነው። ይህም ሰነዱ እንደ አንድ ስትራቴጂክ ሰነድ ለመውሰድ የሚያስቸግር ሁኔታን የሚፈጥር ነው ።

በአጠቃላይ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት ሰላም ነው። ፖለቲካዊ ልፊያም ሆነ ብሽሽቅ፤ ንትርክም ሆነ ያልተገራ ስሜት ለህዝቡ ምንም የሚፈይደው ነገር የለም። ከእስካሁኑም ህፃናትና ወጣቶችን አረገፈ እንጂ ጦርነቱ አንዳችም ያስገኘው ፋይዳ የለም። ስለዚህ ጦርነቱ ቆሞ፣ ሁሉም ፊቱን ወደ ልማት አዞሮ “መጣሁ …”፣ “መጣሁ …” እያለ ከሚያስፈራራን ድርቅ የምናመልጥበት እንዲፈጠርልን እንፈልጋለን።

በዚህ፣ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ጦርነትም ሆነ “… በክንዳችን ብቻ መሆኑን በፅኑ እናምናለን።” የሚለው በአራዶቹ ቋንቋ “የፋራ …” ነውና ወደ ህሊና መመለስ ያስፈልጋል። ከዚህ በመነሳትም “የማጠቃለያ ምዕራፍ አካሄድና ስትራቴጂ” (ነሃሴ 8፣ 2014 ዓ.ም መቐለ) ሰነድ በዚሁ መልክ ሊከለስ እና ሊቃኝ ይገባል ።

# በአገሪቱ በበጎ ፈቃደኞች ከ70ሺህ በላይ የአቅመ ደካማ ቤቶች ታድሰዋል

**ጌትነት ምህረቴ**



አዲስ አበባ፡- በመላ አገሪቱ ከ700 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ከ70 ሺህ በላይ የአቅመ ደካማ ቤቶች በበጎ ፈቃድ አገልግሎት መታደሳቸውን የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ ዶክተር ፍጹም ገለጹ።

ዶክተር ፍጹም 'ፈተና፣ ድል፣ ተስፋ' በሚል ርዕስ የ2014 በጀት ዓመትን ዐበይት የመንግሥት የሥራ ክዋኔዎች የሚዳስስ የአዲስ ወግ የውይይት መርሀ ግብር ትናንት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሲካሄድ እንደገለጹት፤በአዲስ አበባና በክልሎች ከ70ሺህ በላይ የአቅመ ደካሞች ቤቶች በበጎ ፈቃደኞች ታድሰዋል። ይህም በገንዘብ ሲተመን ከ700 ሚሊዮን ብር በላይ ነው።

ዜጎች የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስ፣በፅዳትና በችግኝ ተከላ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የተለያዩ ሥራዎች እየሰሩ ነው ያሉት ዶክተር ፍጹም፤ ይህ የአቅመ ደካሞችን ቤት ማደስ ተግባር የብዙ ሰዎችን አኗኗርና ህይወት መቀየሩን ተናግረዋል።ይህም ሁላችንም ከተባበርን አቅመ ደካሞችን ከችግር ለማውጣት የሚያስችል መልካም ተግባር መሆኑን ተናግረዋል።

የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ሀገራዊ አንድነት፣ እድገትንና የመረዳዳት ባህልን እንደሚያጠናክር ገልጸው፤ሁሉም ዜጋ በሚችለው ሁሉ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠትን ባህል ማድረግ አቅመ ደካሞችን ከመደገፍ ባሻገር ለአገር ዕድገትም ጉልህ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ ትምህርት መዘጋቱን አስመልክተው ባለፈው ሰኔ መጨረሻ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፤ ወጣቱ የእረፍት ጊዜውን በተለያዩ ተግባራት በበጎ ፈቃደኝነት በመሳተፍ ማሳለፍ እንደሚኖርበት ጥሪ ማቅረባቸው ይታወሳል።እሳቸውም የአቅመ ደካሞችን ቤት መገለፃቸውን በየዓመቱ የማደስ እንደሚሰሩ ይታወቃል።

# የሽብር ቡድኑ በተደጋጋሚ የወረራ ሙከራ ቢያደርግም በሽንፈት እንዲመለስ ተደርጓል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት በዞኑ 25 ጊዜ ተደጋጋሚ የወረራ ሙከራዎችን ቢያደርግም በጥምር ጦሩ ጠንካራ ምትና በህዝቡ ደጀንነት ሽንፈትን ተከናንቦ መመለሱን የወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ አሸተ ደምለው ተናገሩ።

አቶ አሸተ ደምለው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሸባሪው ሕወሓት ወረራ ለመፈጸም በተደጋጋሚ ባካሄዳቸው ሙከራዎች ከፍተኛ ኪሳራ ደርሶበት ወደመጣበት ተመልሷል።

የሽብር ቡድኑ ካልጠፋ የኢትዮጵያ ነቀርሳ እስከሆነ ድረስ እፎይታ አይገኝም የሚል እልህና ወኔ በህዝቡ ልቦና በመኖሩ ‹‹እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ›› ሆኖ እየተንቀሳቀሰ ነው ብለዋል።

ህዝቡ የጥምር ጦሩ አስተማማኝ ደጀን ሆኖ እየቀጠለ ነው ያሉት ዋና አስተዳዳሪው፤ በመደበኛ ውጊያ ሲሸነፍ ቄስ ሳይሆን ቄስ በማስመሰል፤ ሸህ ሳይሆን ሸህ መስሎ፣ ሽማግሌ ያልሆነውን ሽማግሌ በማስመሰል፣ በብዙ መልክ እየቀያየሩ ለማስገባት ቢሞክሩም አንድም ሳያመልጥ በቁጥጥር ስር እየዋለ ነው። ይህ የተናበበ ሥራ አሁንም ተጠናክሮ ቀጥሏል ነው ያሉት።

እንደ አቶ አሸተ ገለጻ፤ ትህነግ ወልቃይትን ያዘ ማለት ለታሪካዊ ጠላቶቻችን ምቹ ሁኔታ ስለሚፈጥር አገር አደጋ ውስጥ የሚከት በመሆኑ የመረረ ትግል እየተደረገ ነው። የጀገነ ማህበረሰብ ባለበት ጀግና ሰራዊት አለ። ስለዚህ ህዝቡና ሰራዊቱ እጅና ጓንት ሆኖ እየሰራ ነው። ህወሓት ሴረኛና መሰሪ መሆኑን የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ አካባቢውን በተጠንቀቅ እየጠበቀ ነው።

ዋና አስተዳዳሪው፤ ወልቃይት ጥቅምት 24 /2013 ዓ.ም ነጻ ከወጣ በኋላ አሸባሪው ትህነግ በዞኑ ከ25 ጊዜ በላይ ትንኮሳ ቢያደርግም ከሽፈዋል። በቅርቡ ሶስተኛ ዙር ወረራ ለመፈጸም ሙከራ እያደረገ ቢሆንም እንደለመደው ሽንፈትን ተከናንቦ ተመልሷል። ይህ የሆነበት በየደረጃው ያለው አመራር፣ ህዝቡ የጥምር ጦሩ ተናበው በመስራታቸው ነው። በአስተሳሰብ በተግባር ማህበረሰቡ አሸባሪውን አምርሮ የጠላው ቡድን በመሆኑ የመረረ ትግል እያደረገ ነው ብለዋል።

የትግራይ ህዝብ በአሸባሪ ቡድኑ ላይ እየነቃበት አይደለም ያሉት ዋና አስተዳዳሪው፤ በደሙ እየነገደ ተጠያቂ እንዳይሆን በህዝቡ ጫንቃ ላይ ተጣብቆ ደሙን እየመጠጠ መሆኑን ህዝቡ ሊነቃበት ይገባል ሲሉም ተናግረዋል። የሽብር ቡድኑ የሚያሰልፋቸው ህጻናትና አዛውንቶችን ነው። ይህም አስተሳሰቡ ምን ያህል በደም ሥራቸው ሰርስሮ እንደገባ የሚሳይ ነው። ይህን ነቅሎ መጣል ያለበት የትግራይ ህዝብ መሆኑን ጠቁመዋል።

የትግራይ ህዝብ ዋና ጠላቱ ህወሓት መሆኑን ማወቅና መገንዘብ እስካልቻለ ድረስ ለስልጣኑ ማቆያ ህዝቡን እየማገደ ይኖራል ያሉት አቶ አሸተ፤ ህዝቡ በወልቃት ጠገዴ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ኢትዮጵያ ክፍል ተንቀሳቅሶ የመኖርና የመስራት መብት አለው። ነገር ግን ሽብርተኛው ትህነግ ተወረሃል፤ በወልቃይት መኖር አይቻልም በማለት የተዛባ መረጃ በመስጠት በጅምላ በማሰለፍ እንዲያልቅ እያደረገው ነው። የትግራይ ህዝብ ነቅቶ የ66ቱ የሽማግሌዎች አስተሳሰብ ሊበቃው ይገባል። ለዚህም ህወሓትን አምርሮ መታገል ይገባዋል ብለዋል።

## የሰላም ቀን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አቶ ብናልፍ ፣ የውስጥ ሰላም ካለን ሀገራችን ሰላም የምትሆንበትን ሁኔታ ፈጠርን ማለት ነው። ስለዚህ ሁላችንም ከራሳችን ጋር በመስማማት የውስጥ ሰላማችንን መጠበቅና መልካም አመለካከት እንዲኖረን መጣር ይኖርብናል ብለዋል።

እንደ አቶ ብናልፍ ገለጻ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የቆየ የአብሮነትእሴቶቹን በማዳበር የዘለቄታ ሰላም ግንባታ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት አለበት። ለራሳችን እንዲደረግ የምንፈልገውን ነገር ለሌላ ሰው በማድረግና በኛ ላይ እንዲደረግ የማንፈልገውን በሌሎቹ ላይ ባለማድረግ የሰላም ቀንን ማክበር ይኖርብናል።

ኢትዮጵያ በርካታ ብሄር ብሄረሰቦች ያሏት ሀገር እንደመሆኗ መጠን የቋንቋ ልዩነት፣ የባህል ልዩነት፣ የሃይማኖት ልዩነት ያላት ሀገር ናት። ልዩነቶችን ለማጥፋት የማይታሰብ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ልዩነቶቻችንን በማቻቻል ውስጣችንን ለነዚህ ጉዳዮች በማስገዛት ያለብንን ዋጋ መክፈል ይኖርብናል።

ሀገራችን ብዙ ፈተናዎችን እያሳለፈች ነው የመጣችው ያሉት አቶ ብናልፍ፣ ፈተናው ልንሻገረው የሚገባ ፈተና ነው እንጂ ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም። ምክንያቱም በዛ ውስጥ ሆነን በልማት፣ በሰላምና በሌሎች እያገኘናቸው የመጣነው በርካታ ድሎች የዛ ማሳያ ናቸው።

ፈተናውን ከተሻገርን በኋላ መጪው ጊዜ ያለጥርጥር ወደ ብልጽግና የምናመራበትና የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ በዓል የሚገነባበት እንዲሁም ትልልቅ የልማት ሥራዎችን የሚሠራበትና ሁለንተናዊ የዜጎች ብልጽግና እየተረጋገጠ የሚሄድበት ጊዜ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

እዛ ለመድረስ ግን ማለፍ ያለብን ፈተናዎች ማለፍ አለብን ያሉት አቶ ብናልፍ፣ ሁላችንም ፈተናውን በጽናት ተቋቁመን ማለፍ አለብን። ይህን ለማድረግ ቀዳሚው ነገር የአብሮነት እሴቶቻችንን ማጠናከር ነው ብለዋል። በዘመናት ታሪካችን እንደመጣነው የዛሬውን ፈተና አንድነታችንን በማጠናከር መሻገር ይኖርብናልም ብለዋል።

እንደ አቶ ብናልፍ ገለጻ፣ "ሊነጋ ሲል ይጨልማል" እንደሚባለው ፈተናዎቻችን ለዛሬ ከባድ ቢሆኑም የአንድነት እሴቶቻችንን ለነገ ብርሃንና ተስፋ መሆናቸውን ማወቅ አለብን።

ስለዚህ የሰላም ቀንን ስናከብር ከመቼውም ጊዜ በላይ የአንድነትና የአብሮነት እሴቶቻችንን ጠብቀን ማክበር ይኖርብናል ያሉት አቶ ብናልፍ፣ የጦርነት አባዜ ያለባቸው ከዚህ ድርጊታቸው ራሳቸውን ቆጥበው ነገሮችን በሰላምና በውይይት መፍታት አለባቸው ብለዋል።

ህዝቡም እነዚህን አካላት የሚቃወምና ወደ ሰላም እንዲመጡ ጫና ማድረግ አለበት ። ምክንያቱም "የትኛውም አይነት ጦርነት ጥቅም የለውም፤ የትኛውም አይነት ሰላም ጉዳት የለውም" ለዚህ ጉዳት ለሌለው ነገር ነው መስዋዕት መክፈል ያለብን እንጂ ለጦርነት አይደለም ሲሉ ተናግረዋል።

ስለዚህ በመጪው ዓመት መላው ህዝብ ለሰላም ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራና አሁን ያሉ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ መስራት ይኖርበታል። ይህን ከተደረገ አዲሱ ዓመት ዘመናዊና የተረጋጋ ሀገር የምናይበት፣ ዜጎች በሰላም ወጥተው በሰላም የሚገቡበት እንዲሆን ሁላችንም የበኩላችንን አስተዋጽዖ ማድረግ አለብን ብለዋል።

መጪው ዓመት የሰላምና መረጋጋት ዓመት ከሆነልን የምንመኘው ብልጽግና እንደሚሳካ አልጠራጠርም በማለት ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

## አሸባሪው ሕወሓት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አደረጃጀት የመነጨ መሆኑን የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው ገለጹ፡፡

ረዳት ፕሮፌሰር አበባው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሕወሓትን ያቋቋመው ቡድን ከመጀመሪያውም ጠላት ብሎ የተነሳው የአማራን ሕዝብ ነው፡፡

ቡድኑ ከአርባ ዓመት በፊት ጀምሮ በአማራ ህዝብ ላይ ያለውን ቂምና ጥላቻ በመያዝ ለም የሆኑ የወልቃይትና የሁመራ አካባቢዎችን በቁጥጥሩ ስር በማዋል እና ህብረተሰቡ ከአካባቢው እንዲሰደድ በማድረግ ግፍ ሲፈጽም እንደነበር በርካታ መረጃዎች አሉ፡፡ ይህንን የተመለከተ መጽሐፍን ሰሞኑን ለምረቃ በቅቷል፡፡

ረዳት ፕሮፌሰር አበባው እንዳሉት፤ ቡድኑ ወደስልጣን ለመምጣት የትግራይና የአማራ ህዝብ በታሪክ ጠንካራ ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር አላቸው፡፡ ነገር ግን ሾልኮ በወጣው ሰነድ በአማራና በትግራይ ሕዝብ መካከል የተንጸባረቀው ጥላቻ መጀመሪያ ላይ ሕወሓት እንደፖለቲካ ድርጅት ሲደራጅ ያመጣው መሆኑን መጋለጡን ነው የጠቆሙት፡፡

በኢትዮጵያ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በተግባር በሕዝባዊ ስብሰባዎቹ፣ በየመድረኮቹ፣ በሚዲያው አማራ እንዲጠላ በቡድኑ ታቅዶና ታስቦበት መሰራቱንም ተናግረዋል፡፡

ይህ ሰነድም የቀድሞው የሽብር ቡድኑን አስተሳሰብ መቀጠሉን፣ ከወሰን ጋር ተያይዞም የአማራን ሕዝብ ጠላት የማድረግ አባዜውን የሚያሳይ መሆኑንም ነው የተናገሩት፡፡

የአማራ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ አቋም በመያዝና ኢትዮጵያዊነትን ማቀንቀኑንም ስለማይወደው ይህንን ህዝብ የማዳከም ስልቶች እንደሚንጸባረቁበት ሾልኮ በወጣው ሰነዱ ላይ መቀመጡንም ነው ያነሱት፡፡

አሸባሪ ቡድኑ መጀመሪያ ላይ የአማራ ገዢ መደብ ብሎ ሲያቀነቅን እንደነበር፣ ትግል እያፋፋመና ብሄርን እያጠናከረ ሲሄድ ደግሞ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሌላውም ጠንቀኛ ሆኖ መታየት ያለበት ነው ብሎ በማመን የሃሰት ተረኩን መቀጠሉንም አንስተዋል፡፡

ጌታቸው ረዳም ሆነ በሽብር ቡድኑ አቀነባባሪዎች የሚሰጡ መግለጫዎችና ፕሮፖጋንዳዎች የሕወሓት እኩይ ተግባርን ሕዝብን ለመከፋፈል፣ አንዱን በአንዱ ላይ ለማስነሳትና ውዥንብር ለመፍጠር ያለውን ጽኑ ፍላጎት ማንጸባረቁንም አንስተዋል፡፡

የሚስጢር ሰነዱ ላይ ቡድኑ ወጥ የሆነ ፕሮፖጋንዳ ማራመድ እንዳልቻለ የተጋለጠበት መሆኑን ጠቁመው፤ በአንድ በኩል አማራ ጠላታችን ነው ብሎ ያስባል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከአማራ ሕዝብ ጋር የነበረንን ወዳጅነት እንቀጥላለን፣ አንጎዳውም ይላል፤ እንደሰሞኑ በጨነቀ ሰዓትና ነገሮች አልሆን ሲሉ አማራን ለጊዜውም ቢሆን በፖሮፖጋንዳ በቃል የመሸንገል ሥራ ይሰራል፤ በአጠቃላይ የተምታታበት አካሄድ ነው፡፡

መሬቱን መያዙንና ሲጨፈጭፈውና እንዲጨፈጨፍ ያደረገ ሕዝብ መሆኑን ዘንግቶ ዝብርቅርቅ ንግግሩ የቡድኑን እኩይ ባህሪውን ያሳየበት መሆኑንም ነው የጠቆሙት፡፡

የሽብር ቡድኑ መሪዎች ንግግር አንድም ከድርጅቱ እኩይ ባህሪነት እንደገናም ከግለሰብ ተፈጥሯዊ ባህሪ የመነጨ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡ የሰሞኑ ንግግርም ሕወሓት አማራ ላይ ያለውን አቋም አለመቀየሩን፣ እንደ ሕዝብ ጠላቴ ነው ብሎ የሚፈርጀውን እንደቀጠለበት ማሳያ መሆኑንም አንስተዋል፡፡

ጌታቸው ረዳ ፖለቲከኛ ከመሆኑም በፊት በትምህርት ቤት ሕግ ሲማር ሲያውቁት ቅጥፈትና ሃሰት የተሞላበት እንደነበር፣ ይህ የግል ባህሪው ወደሕወሓት እንዲወሰድ እንዳደረገውም ረዳት ፕሮፌሰሩ ተናግረዋል፡፡

ሕዝብና መንግሥት አንድ ሆነው አቅም እንዳይፈጥሩ ክፍፍል የመፍጠር አካሄድ ለመከተል በሰነዱ ማስቀመጡን ያነሱት ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፤ ሕዝብና መንግሥት መካከል መቃቃርን መፍጠር፣ በሕዝብ መካከልም መቃቃርና መጠራጠር ስሜቶች እንዲፈጠር ለመስራት መነሳቱን በሰነዱ ላይ እንደተቀመጠ ተናግረዋል፡፡

የተሳሳተ የፖለቲካ ትንተናቸውን ያነሱት ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፤ አማራ ክልል ላይ ፋኖ በመታሰሩ በክልሉ መንግሥትና በፋኖ መካከል ክፍተት በመኖሩ ሕዝብን ለማንቀሳቀስ እንደማይመችና ጠንካራ ማጥቃት ቢደረግ የመከላከል አቅም የለም የሚል አስተሳሰብ አለው፡፡

ፋኖን የመኮነንና በሌላ በኩል ደግሞ የክፍተት ምንጭ ማድረግ በፖሮፖጋንዳ የማዳከም ሥራ ቁልጭ ብሎ መቀመጡንም አንስተዋል፡፡ የፖለቲካ ነበልባል የሚያስነሱ ጉዳዮችን ወደራሱ ጥቅም የመቀየርም በታክቲክነት ለመጠቀም የጠነሰሰው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የአካባቢ አስተዳደሮችን እምነት በማሳጣት የማዳከም፣ መንግሥትና ሕዝብ ሆድና ጀርባ ለማድረግ የወጠናቸው አንዳንዶቹ ቡድኑ ቀድሞም ሲሰራበት የነበረ፣ ገሚሶቹ ወቅታዊ ንፋስ አመጣሽ ነጥቦችን በማቀጣጠል መንግሥት በሕዝብ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት የማዳከም ስልት ነው ብለዋል፡፡

ሰሞኑን ከሕወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ሾልኮ የወጣው ሰነድ እንዳመለከተው ቡድኑ በተለይ የአማራ አርሶ አደር እርሻውን እንዳያርስና ያረሰውንም እንዳይሰብስብ በማድረግ ልማን ማደናቀፍ አንዱ ስልቱ አድርጎ የያዘ ሲሆን ከዚህም አልፎ ሰርጎገቦችን በማስገባት ክልሉን ብሎም ሃገርን ማተራመስ የሚል ስልት የያዘ መሆኑ ይታወቃል፡፡

## አገልጋይነት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንዳሉ ጠቅሰው፤ በዋናነት ከአደረጃጀት፣ ከሰው ሀብት ስምሪትና ቅጥር እንዲሁም ዝውውር የሚፈጸምባቸው ህግ ማብራሪያዎች፣ ከመረጃ አያያዝ ጋር ተያይዞ ጡረታን የተመለከተ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ እንዳለ ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመሆን፤ ወደ 30 የሚጠጉ ተቋማት በመሰባሰብ በቴክኖሎጂ የታገዘ "ኢ- ሰርቪስ" የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለተገልጋዮች ተደራሽ የማድረግ ሥራም በዛሬው ዕለት እንደሚከወን ጠቅሰዋል። የጽዳት ዘመቻም ጭምር በማድረግ እንደሚያከብር ጠቁመዋል።

የአገልጋይነት ቀን በዛሬው እለት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች እየተከበረ ሲሆን፤ ዕለቱ መንግስት ለዜጎች አገልጋይነቱን በሥራ የሚያሳይበት፤ ዜጎች ያለምንም እንግልት የመንግሥትን አገልግሎት እንዲያገኙ የሚደረግበት፤ ማገልገልን በተግባር ለዜጎች ለማሳየት ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

# ወቅታዊ

# «ሰላም ማለት ግጭትን ማስወገድ ብቻ አይደለም፤ ከእያንዳንዱ ዜጋ የአስተሳሰብና የባህሪ ለውጥ የሚጀምር ነው»

**- አቶ ብናልፍ አንዷለም**
**የሰላም ሚኒስትር**




አስመረት ብስራት

**በአገራችን የለውጥ እንቅስቃሴ ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ የሰላም መደፍረስ በየአቅጣጫው ታይቷል። በተለይ ሕወሓት በህዝቦች ያልተቋረጠ ተቃውሞ ከስልጣኑ ተገፍትሮ ወደ መቀሌ ከመሸገ ጀምሮ ደግም የስልጣን ጥሙን በኃይል ለማስመለስ ያሳሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ከአገር ውስጥና ከውጪ የሽብር ቡድኖች ጋር በመተባበር የአገርን ሰላም የማወክ ሴራውን በአደባባይ ጦርነት በመክፈት እንዲሁም በስውር ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ግጭት ሲጠነስስና ሲጠምቅ ቆይቷል። ይህም አልበቃ ብሎት በመንግስት በተለያዩ ጊዜያት የተዘረጉ የሰላም እጆችን ረግጧል። አሁንም የሰላም መንገዱን ወደ ጎን አድርጎ ለሶስተኛ ጊዜ ጦርነት ከፍቷል። ሆኖም መንግስት ዛሬም የሰላም በሩን አልዘጋም። የሰላም ሚንስትሩ አቶ ብናልፍ አንዷለም በሰላም ምንነትና አስፈላጊነት፣ የሰላም እሴት ግንባታ፤ ለሰላም የተደረጉ ጥረቶችና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አዘጋጅተነዋል።**

**አዲስ ዘመን፡- የሰላም እሴት ግንባታን ማጎልበትና ህዝቡን የሰላም ባለቤት ለማድረግ አልፎ አልፎ የሚታዩ ግጭቶችን ለመፍታት የሚሰሩ ስራዎችን ቢገልፁልን?**

**አቶ ብናልፍ፡-** ሰላም ስንል ምን ማለት ነው የሚለውን ሀሳብ ከማብራራት እንነሳ። የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት የሰላምን ትርጉም የሰው የውስጥ ሰላም በማለት ይተረጉሙታል። ይህ ማለት ሰላም የሚጀምረው ከእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ነው ማለት ነው። የአእምሮ ሰላም፣ የውስጥ ሰላም፣ የውስጥ መረጋጋት ከእያንዳንዱ ዜጋ ይጀምራል። ማንም ሰው ውስጡ ሰላም ከሆነ ከራሱም፣ ከጎረቤት ከቤተሰብ ከሁሉም ጋር በሰላም መኖር ይችላል። እንዲህ አይነቱን ሰላም መገንባት የሚቻለው ከአስተሳሰብና ከባህሪ ለውጥ ነው። ይሄንን ሰላም መገንባት የቻለ ማህበረሰብ ቀጣዩን የሰላም ትርጓሜ ለመቀበል ማንም አያስገድደውም። ይህ የምናገኘው ደግሞ በማስተማር በተለያዩ አነቃቂ የሆኑ ቀና አስተሳሰቦችን ህዝቡ ውስጥ በማስረፅ ነው። እዚህ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ለዘላቂ ሰላም ውጤት አለው።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ይሄንን በደንብ አጠናክሮ ለመስራት አቅዶ እየተንቀሳቀሰ ነው። ይህ ሲባል በሚቀጥሉት ዓመታት የሠላም ትምህርት በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካትቶ ለዜጎች የሚሰጥበትን ሁኔታ እየተመቻቸ ነው። የሠላም ትምህርት በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካትቶ ለዜጎች የሚሰጥበትን ሁኔታ በማመቻቸት የሠላም ትምህርት በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ መካተቱ የሰለጠነ የግጭት አፈታት መንገድን ዜጎች ከትምህርት ቤት ጀምሮ እንዲለማመዱትና ባህል እንዲያደርጉት የሚያስችል ነው።

የሠላም ትምህርት የዜጎችን አስተሳሰብና ባህሪ ለመቀየርና እያንዳንዱን ሰው የህሊና ሠላም ለመጠበቅ የሚያስችል ነው ። ይህን ለማድረግ የሠላም ሚኒስቴር ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተዘጋጅቶ በቅርቡም ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የፊርማ ሥነ-ሥርዓት ይኖራል። በመግባቢያ ሰነድ ውስጥ ተማሪዎች የሠላም ክበባትን ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ እንደሚቋቋምና ሌሎችም ጉዳዮች በማካተት በሰላም የተቀረፀ ትውልድ እንዲኖር ይደረጋል።

ሌላኛው የሰላም ትርጓሜ ሲሰጥ ብዙ ጊዜ የተለመደው የጦርነት ያለመኖር ወይም ግጭት ያለመኖር የሚል ነው። ይህ ትርጓሜ ለረጅም ዓመታት ሲሰማ የኖረ የሰላም ትርጉም ነው። በኛ አገር ብዙ ግጭቶች ነበሩ በዚህ በሶስት በአራት ዓመታት ብቻ ሳይሆን ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በየአካባቢው በተለያዩ ምክንያቶች ግጭቶች ነበሩ። ግጭቶች እንዳይከሰቱ አስቀድሞ የግጭት መነሻ የሆኑ ጉዳዮችን የመከላከል ስራ መሰራት አለበት። ያም ሆኖ ግን የማህበረሰብ እሴቶችን አልፎ በተለያዩ ምክንያቶች ግጭቶች ሲከሰቱ የከፋ ጉዳት ሳይከሰት የመቆጣጠር ስራ ሊሰራ ይገባል።

በአገራችን ብዙ ግጭቶች መፈናቀሎች ነበሩ። በአሰቃቂ ሁኔታ ዜጎች በጅምላ የተጎዱበት ሁኔታ ነበር። በአጠቃላይ የደረሰው ውድመትና ያስከተለው ችግር ቀላል አልነበረም። ያንን ውድመት ወደ ነበረበት ለመመለስ መንግስት ርብርብ ያደረገባቸው፣ ሚኒስትሩም በርካታ ስራዎችን ሲሰራ መቆየቱን ለመናገር እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- የአገር በቀል የግጭት መፍቻ ስልቶቻችንን በመጠቀም አገርን በማረጋጋት የእርስ በእርስ ግጭትን ወደ ሰላም ለማምጣት አይነተኛ መፍትሄ ሲሆኑ ስለሚችሉ እነዚህን ከመጠቀም አንፃር ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ብናልፍ፡-** ኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ክልሎች እጅግ ወርቃማ የሆኑ የግጭት አፈታት ዘዴዎች አሉ። አንዳንዶቹ በጥናት የተደገፉ ሲሆን ገና ብዙ መጠናት ያለባቸውም አሉ። ህብረተሰቡም ሆነ የተቀረው የማህበረሰብ ክፍል እንዲያውቃቸው የሚያስፈልጉ በጣም ትልልቅ እሴቶች በየትኛውም ክልል ውስጥ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶች አሉ። እነዚህንም በደንብ ልንጠቀምባቸው ይገባል።

ዜጎች እንዲያውቃቸውና ከትውልድ ወደ ትውልድ በተገቢው መልኩ እንዲተላለፉ ሰፊ ስራን ይጠይቃል። በዚህም ላይ የተጀመሩ በርካታ ስራዎች አሉ። በማህበረሰቡ እሴቶች በርካታ ግጭቶች ከመቀስቀሳቸው በፊት ባጭር የቀሩ ብሎም ከተቀሰቀሱ በኋላ ሳይሰፉ እንዲቀሩ የተደረጉ አሉ። የሰላም ሰራዎች ስለማይታዩ አልተነገረላቸውም እንጂ ስራዎቹ እየተሰሩ ነው። በርካታ በባህላዊ እሴቶች የተፈቱ አሉ። እነዚህን ወደ ፊት በጥናት እየደገፉ ጥቅም ላይ ለመዋል የሚጠበቁ ስራዎች ስለሚኖሩ አጠናክረን እንቀጥላለን።

**አዲስ ዘመን፡- አገሪቱ አሁን የገጠማትን ግጭቶችን ለማከም እና ሰላምን ለመመለስ ከማን ምን ይጠበቃል?**

**አቶ ብናልፍ፡-** በአገሪቱ የግጭት ምክንያት ነው ብዬ የማስበው በዋናነት የፖለቲካ ባህላችን ያለበት ችግር ነው። ሌሎች ሰዎች ቢጠየቁ ብዙ ችግሮችን ሊዘረዝሩ ቢችሉም ለእኔ ግን ዋነኛው ምክንያት ዋናውና ትልቁ የፖለቲካ ባህላችን ላይ ያለ ችግር ነው።

ወደ ኋላ መልስ ብለን የአገሪቱን ታሪክ ብንመለከት የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ የሚፈልጉ አካላት በሰለጠነ መንገድ ስልጣን ከመያዝ ይልቅ በመጠፋፋት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ባህል ይዘን የቆየን መሆኑን ያሳያል። በንጉሱ ዘመን ስልጣን የሚያዘው በዘር ሐረግ ሲሆን አንዱን ወደ ስልጣን ለማምጣት አንዱ ሌላውን ማስወገድ የነበረበት ነው።

ከዛ በኋላም የፖለቲካ ፓርቲዎች ተፈጥረው በነበረበት ወቅት ለስልጣን የሚያደርጉት ፉክክር በመጠፋፋት ላይ የተመሰረተ ነበር። በስልሳዎቹ የተፈጠሩት ፓርቲዎች ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር ደረጃ የሚያራምዱት ርእዮተ ዓለም ሶሻሊዝም ነበር። ሁሉም አንድ አይነት ርእዮተ አለም እያረመዱ እርስ በእርስ ነበር የተጨራረሱት። ለምሳሌ ደርግና ኢህአፓ፣ ኢህአፓና ሜኤሶን ሌሎቹም ፓርቲዎች እርስ በእርሳቸው የተጠፋፉበት ሁኔታ ትውልድን እንድናጣ ያደረገን ነው። ይሄ ልንደብቀው የማንችለው የሁላችንም ታሪክ ነው። በዚህም የትውልድ ክፍተት እንዲፈጠር አድርጓል።

ከዛ በኋላም ደርግን ለመጣል የተደረገው እንቅስቃሴም በጦርነት ላይ የተመሰረተ ነበር። በትጥቅ ትግልም የደርግ ስርአትን ለማስወገድ ችለዋል። በአጠቃላይ በጦርነትና እርስ በእርስ የመገዳደል ባህልን የያዘ ታሪክ ነው ያለን። ባለፉት ሰላሳና አርባ ዓመታት የፖለቲካ ባህሉ በዘር ላይ የተመሰረተ ልዩነት ላይ የተመሰረተ ሆነ። አንድ የሚያደርጉንን ለብዙ ሺ ዓመታት ይዘናቸው የመጣናቸውን እሴቶች እንድንጥልና እርስ በእርስ በጥርጣሬ እንድንተያይ ሆነናል።

ይሄ የህብረተሰቡን ግንኙነት ከፉኛ የጎዳ ከመዋደድ ከመቻቻል ይልቅ እርስ በእርስ እንድንጠፋፋ አድርጎናል። ልማትን ከማስቀደም ይልቅ በግጭቶች እንድንታመስ የሆነውም በዚህ ምክንያት ነው። ቀደምት በርካታ የስልጣኔ ታሪክ ያለን ህዝቦች ነን። ጦርነት ተገደን ብቻ የምንገባበት ነው። ብዙ ወረራዎች ቢፈፀሙብንም ሁሉንም መክተን የጥቁር ህዝቦች ተምሳሌት እስከንሆን ደርሰን የነበርን ህዝቦች አሁን ግን በጣም ያነሰ የወረደ ተግባር በመፈፀም በድህነትና በጉስቁልና እንድንኖር ሆነናል። ስለዚህ የፖለቲካ አመለካከታችን ማጥራት አለብን።

ለዚህም የመጀመሪያው መፍትሄ ብሄራዊ መግባባትን መፍጠር ነው። የምንለያይባቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ልዩነቶቻችንን እንዴት መፍታት አለብን የሚለውን ነገር በሰከነ አእምሮ ማሰብ አለብን። ከባለፈው ጥፋታችን ተምረን ለውጥ የምናመጣበት ትክክለኛ ጊዜ አሁን ነው። ቁጭ ብለን በሰለጠነ መልኩ በመወያየት የአመለካከት ልዩነታችንን እያስታረቅን፤ አገራችንን እናሳድጋለን። የማንግባባበትን ሂደት ከፈታው ፈታው ካለበለዚያ ግን ለህዝቡ በመተው ሰላምን ማስቀደም አለብን።

ይህንን አገራዊ መግባባት ለመፍጠር የማንም ተፅእኖ የማይኖርበት ማህበረሰቡን ወደ ተረጋጋ ሰላም የሚያመጣ ኮሚሽን ተቋቁሞ ወደ ስራ መግባቱ በጉጉት እየተጠበቀ ነው። ለውጥ ያመጣል ብለንም እናምናለን።

**አዲስ ዘመን፡- መንግስት በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ያለውን ችግር በሰላም ለመፍታት እስከ ምን ድረስ ሄዷል?**

**አቶ ብናልፍ፡-** በአሁን ወቅት በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተከሰተው ግጭት መነሻው ለውጥን ባለመቀበል ወይም ለማደናቀፍ ባለው ፍላጎት የተነሳ ነው። ከአራት ዓመት በፊት በነበሩ ብዙ ችግሮች ተወግደው የተሻለ ፍትህና ዲሞክራሲ የሚከበርበት አገር እንዲሆን ህዝቡ ታግሎ ለውጥ አምጥቷል። ያ የለውጥ እንቅስቃሴን ጥቅማቸውን የነካባቸው ኃይሎች አምርረው ለውጥን ሲቃወሙ ነበር። እናም ይሄንን ለውጥ ለመቀልበስ ያላደረጉት ሙከራ አልነበረም።

በአሁኑ ወቅት በሰሜኑ የአገራችን ክፍል እየተከሰተ ያለው ግጭት ዋነኛው ምክንያት ለውጥን ለማደናቀፍና ላለመቀበል ካለ ጽኑ ፍላጎት ነው። በአንጻሩ በኢትዮጵያ የተሻለ ዴሞክራሲ፣ የተሻለ ፍትህ፣ የተሻለ ልማት ያለባትና የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት የተከበረባት አገር እንድትሆን በመንግሥት በኩል በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል። መንግሥትም ይህን እውን ለማድረግ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሲሰራ ቆይቷል። ይህንን እውን ለማድረግ የተጀመረው ሰላማዊ እንቅስቃሴ ጥቅማችንን ጎድቶታል ብለው የሚያስቡ ኃይሎች አምርረው ለውጡን ይቃወሙ ጀመር። ከእነዚህም ውስጥ ግንባር ቀደሙ ትህነግ ነው ብለዋል። የትህነግ እንቅስቃሴ ለውጡን ብቻ መቃወም አይደለም፤ አገር በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ከአፍሪካ አገራት ብሎም ካደጉት አገራት ተርታ እንዳትሰለፍ የማድረግ ሥራ ነው። ይህ ሙከራው እንዳልተሳካለት ባወቀ ጊዜ ትግራይ ክልል በመሄድ በየቀኑ የጦርነት አዋጅና ትርኢቶች ሲያደርግ ቆይቷል። መንግሥት ይህ እንቅስቃሴ አዝማሚያው ጥሩ አይደለም፤ አገሪቱን ወደ ጦርነት ይከታታል፤ ካለፈው የጦርነት ጊዜያት መማርና ማረም አለብን፣ አለበለዚያ ከበፊቱ የባሰ አገሪቱን ወደ ቀውስ ይከታታል በሚል ሕወሓት ከዚህ እንቅስቃሴ እንዲቆጠብ ተደጋጋሚ የሠላም ጥሪ አቅርቧል።

መንግሥት በተደጋጋሚ ይሄን ጉዳይ በሠላም እንዲፈታ ጥረት ሲያደርግ የነበረ ቢሆንም ይህ ጥረት በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በአገር ሽማግሌዎች፣ በኃይማኖት አባቶች፣ በእናቶችና ከኢትዮጵያ ውጪ በሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጭምር ወደ ጦርነት ሳይገባ ችግሩን በሠላም እንፍታ የሚል ጥያቄ ቀርቧል። ምክንያቱም በሠላም የማይፈታ ጉዳይ ምንም ነገር የለም። ይህም በጥሪ ብቻ አልነበረም በአካል መቀሌ ድረስ ተሂዶ ተሞክሮ ምላሹ ግን የፈለገ ነገር ይምጣ፣ ወደ ጦርነት እንገባለን የሚል ነበር። በዚህም ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ቡድኑ በሰሜን እዝ ላይ ጥቃት ፈጽሟል። ይህ ደግሞ ግልጽ የሆነ የአገር ሉአላዊነት መዳፈር ነው። ምክንያቱም መከላከያ ማለት የአገር ሉአላዊነት የመጨረሻው ምሽግ ነው። በውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጪም የአገሪቱ ሉአላዊነት የሚዳፈር አካልን ዋጋ የሚሰጠው መከላከያ ሰራዊት ነው።

በዚህም መንግሥት የህግ ማስከበር ዘመቻ አድርጓል። የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች ጦርነቱን እንደ ምክንያት ተጠቅመው የተለያዩ የማጥቃት እንቅስቃሴዎች

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ሲያደርጉ ቆይተዋል። ነገር ግን በኢትዮጵያውያን በተባበረ ክንድ ይህን እንቅስቃሴ ማቆም ተችሏል። ከዚህም ለሰላም ተጨማሪ እድል ለመስጠት እና የትግራይ ህዝብ የግብርና ሥራውን ተረጋግቶ እንዲሰራ መቀሌ የገቡ ወታደሮችን አስወጥቶ፤ ሰብዓዊ ድጋፍ ለሚያደርጉ አካላትም መንገዱን ክፍት አድርጓል። ሆኖም በመንግሥት በኩል ጦርነቱን ለማስቆም እና ሰላማዊ እልባት ለመፈለግ የተደረጉ ጥረቶች በሕወሓት በኩል ተቀባይነት ያገኝ አልበረም።

ከዛም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የመሩት ጦርነት ተደርጎ ትርጉም ያለው ውጤት ሲገኝ ከዚህ በኋላ ወደ ትግራይ ገብቶ ላለመዋተት ቃል ገብቶ ጥሪ አቀረበ። በዓለም ላይ የተካሄዱ ጦርነቶች አሸናፊና ተሸናፊ ያልነበራቸው ውጤታቸውም ውድመት፣ ኪሳራና፣ በአገራት ላይ ከፍተኛ ቀውስ ያስከተለ ስለሆነ የኢትዮጵያ መንግስት ተኩስ አቁም አደረገ።

ነገር ግን የአሸባሪው ትህነግ እራሱን ለሶስተኛ ዙር ጦርነት እስኪያዘጋጅ ቆይቶ የተሰጠውን ተደጋጋሚ የሰላም እድል ያመከነበት ሁኔታ ነው፤ መንግሥት ለሠላም ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ ሕወሓት ወደ ጦርነት እንዳይገባ እና ችግሮችም በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ በርካታ ሙከራዎችን አድርጓል። የኃይማኖት አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች ስለሠላም ቡድኑ ያለበት ሄደው የሠላም ጥሪ እንዲያቀርቡ ተደርጓል። ከዚህም በተጨማሪ በርካታ የሰላም ጥሪዎች ቀርበውለታል። ቡድኑ ይህን አልቀበል ሲል ደግሞ ከመንግሥትና ከሌሎች ኃይሎች ገለልተኛ የሆነ የምክክር ኮሚሽን እንዲቋቋም ተደርጎ ችግሩን በሰላም ለመፍታት ብዙ ርቀት ተሂዷል።

መንግሥት የሰላም ውይይቱን በአስቸኳይ ለመጀመር የሚያስችል የሰላም ምክረ- ሃሳብን፣ የያዘ ሰነድ ማዘጋጀቱን ይፋ ቢያደርግም፣ ሕወሓት በተቃራኒው፣ የተኩስ አቁም ስምምነቱን ማፍረሱ በግልጽ "ኃይል ብቸኛ አማራጩ" እንደሆነ ያሳያል። ግጭቱ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ መንግሥት ለሰላም ዕድል ለመስጠት ተደጋጋሚ ሙከራዎችን ቢደረግም የሰላም አማራጩን በዘላቂነት እውን ለማድረግና በሰሜኑ የትግራይ፣ የአፋርና የአማራ ክልል አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎችን ከገጠማቸው ችግር ለማላቀቅ የሕወሓት ታጣቂ ቡድን ጠብ አጫሪነቱን ሊገታ ይገባል።

የአሸባሪው ትህነግ የጦርነት ጥሪ ትውልድን የማጥፋት ዘመቻ መሆኑ ግልጽ ነው። ጦርነትን እንደ ጀብድ ለሚያዩና ህዝብን ለማስጨረስ ጦርነትን ለሚጎስሙ የቡድኑ መሪዎች ወደ ልቦናቸው ተመልሰው ቆም ብለው ሊያስቡ ይገባል። እንደ ሀገር ችግሮችን በውይይት መፍታት የሚያስችሉ መድረኮች እየተዘጋጁ ባሉበት በአሁኑ ወቅት ጦርነትን እንደተሻለ አማራጭ ለመጠቀም መሞከር ህዝብን የሚጎዳና ኃላፊነት የጎደለው አካሄድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈንና አገራዊ መግባባት ለመፍጠር የተቀየሱ ስልቶችና እስትራቴጂዎች ምን ይመስላሉ ?**

**አቶ ብናልፍ፡-** በኢትዮጵያ የሰላም ጉዳይ በተለይ የዛሬ አራት አመት ገደማ የለውጥ እንቅስቃሴ ከተጀመረበትና ለውጥ በዚህ አገር እውን ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ዋነኛ የለውጡ ማእከል ከተደረጉ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የሰላም ጉዳይ ነው። ያኔ በለውጡ ዋዜማ አካባቢ አገሪቱ የነበረችበት ሁኔታ እጅግ በጣም ውጥረት የበዛበት፤ ከፍተኛ ትርምስ፤ ያለመረጋጋት የነበረበት ነው። የአገሪቱ የመጨረሻ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል የሚለው በብዙ ዜጎች ዘንድ ከፍተኛ ስጋትን ፈጥሮ ስለነበረ አጠቃላይ በአገር ደረጃ ሪፎርም ማድረግ አለብን ተብሎ ለውጡ በሪፎርም እንዲመራ ተወስኗል።

ከዛ በኋላ የተለያዩ የሪፎርም አጀንዳዎች ተቀርፀዋል። የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካ፤ የህግና ሌሎች ሪፎርሞች ተቀርፀው ነበር። የሰላም ጉዳይና ህግ የማስከበር ጉዳይ የመሳሰሉትን ያካተተ ትልቅ ሪፎርም ነው በወቅቱ የተጀመረው። በዛ ወቅት በአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት እንዲመጣ ብዙ ትልልቅ እርምጃዎች ተወስደዋል። ለ20 ዓመታት ቆይቶ የነበረው በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የነበረው ውጥረት በሰላም ለመፍታት የተወሰደው እርምጃ በትልቁ የሚጠቀስ ነው። ከጎረቤት አገሮቻችን ጋር በሰላምና በወዳጅነት በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንዲኖረን በውጭ ይኖሩ የነበሩ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ አገር ቤት እንዲመጡ ተደርጓል። የትጥቅ ትግል አውጀው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የተለያዩ አካላት በሰላማዊ መንገድ ጥያቄያቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ። ስለዚህ በጠላትነት ከመተያየት ወጥተን ሰላም የሰፈነባት አገር መሆን እንችላለን በሚል ጥሪ ተደርጎላቸው ወደ አገር የገቡበትም ጊዜ ነበር። በብዙ የአረብ አገራት እስር ላይ የነበሩ ዜጎች ተፈተው አገራቸው እንዲገቡና የመሳሰሉት በጣም ትልልቅ እርምጃዎች ተወስደዋል።



ከሁሉ በላይ ደግሞ የውስጥ ሰላማችንን ማስጠበቅና ህዝቡ ወደተረጋጋ ሁኔታ መጥቶ ያሉ የፖለቲካ ልዩነቶች በሰላማዊ መንገድ በሰለጠነ አካሄድ እንዲፈቱ ማድረግ ይቻላል በሚል ሪፎርሙ ማእከል አድርጎ ነበር። ህግ የማስከበር አቅማችን እንዲያድግ ሎው ኢንፎርስመንት ኤጀንሲስ የሚባሉትን ገለልተኛ ሆነው ከማንኛውም ፖለቲካ ወገንተኝነት በፀዳ መልኩ ህግንና ህግን ብቻ መሰረት አድርገው እንዲሰሩ የማድረግ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። እነዚህ በሪፎርሙ የተገኙ ውጤቶች ነበሩ።

በአገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰላም ሚኒስቴር በሚኒስትር ደረጃ ተቋማዊ በሆነ መልክ እንዲመራ የተቋቋመው በለውጡ ነው። በእነዚህ ጥረቶችና ውጤቶች ዓለም ሁሉ የተደመመበት ተግባር ተከናውኖ ነበር። በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታም የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሰላም ኖቬል ተሸላሚ እስኪሆኑ ድረስ ያደረገ ጥረትና ውጤት ነበር የተደረገው።

ምንም እንኳን ከዛ በኋላ ለወጡን በመቃወም እና ለወጡን ለማደናቀፍ አቅደው የሚሰሩ የፖለቲካ ኃይሎች ሁሉም የአገሪቷ አካባቢ ግጭት እንዲቀሰቀስ ሆኗል። በዜጎች ላይ ጥቃት እንዲፈፀም፤ አገሪቱ እንዳትረጋጋና የተጀመረው ለውጥ እንዲቀለበስ ለማድረግ ከውስጥም ከውጭም የተቀነባበሩ ሴራዎች ስለነበሩ የተከፈለው ዋጋ ትልቅ ነበር።

በክልሎች መካከል የሚኖረው ግንኙነት ጤናማ እንዲሆን በክልሎች ውስጥ የሚነሱ ግጭቶች ካሉ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ለማድረግ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች በማህበረሰብ ደረጃ የሰላም ውይይቶች እንዲካሄዱ ለማድረግ የተጀማመሩ ስራዎች አሉ። በውይይቱ የተነሳም የተለያዩ ችግሮች በአካባቢው እንዲቀሩ ተድርጓል። በአጠቃላይ የሰላም ግንባታ ስራ ረጅም ጊዜን የሚወስድ ስራ እንደመሆኑ ያንን ለማሻገር እየተሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንደ ስሙ ለሰላም ያደረጋቸውን ጥረቶች ዘርዘር አድርገው ቢገልፁልን?**

**አቶ ብናልፍ፡-** መስሪያ ቤቱ የመንግስት አንድ አስፈፃሚ መስሪያ ቤት ነው። መንግስት በሰላም ጉዳይ ላይ የሚሰራቸውን ጉዳዮች የሚያስፈፅም በአዋጅ የተቋቋመ መስሪያ ቤት ነው። ዋናውና ትልቁ ነገር በአገሪቱ የተረጋጋ ሰላም እንዲኖር አወንታዊ ሰላምን ለማስፈን እየሰራ ነው። ሰላም ማለት ግጭትን ማስወገድ ብቻ አይደለም፤ ጦርነትን ማስቀረት ብቻ አይደለም። ሰላም ማለት ከእያንዳንዱ ዜጋ የአስተሳሰብና የባህሪ ለውጥ የሚጀምር ነው። ስለዚህ ዘለቄታዊና አስተማማኝ ሰላምን ለማስፈን ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ ነው።

ሰላም የሚፈለገው መሰረታዊ ለሆኑ ጉዳዮች ነው። አንደኛው ጉዳይ የህልውና ጉዳይ ስለሆነ ነው። ዜጎች ያለሰላም መኖር አይችሉም። የሰላም ጥያቄ የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ ነው። ጦርነት ሲቀሰቀስ ወጥቶ መግባት ያዳግታል፤ እናቶች ልጆቻቸውን ማሳደግ አይችሉም፤ ህፃናት ተምረው እራሳቸውንም ሆነ አገርን መለወጥ አይችሉም። ለህልውና የግድ ሰላም ያስፈልጋል። ሁለተኛው ሰላምን የምንፈልግበት ምክንያት የእድገትና የብልፅግና መንገድ ስለሆነ ነው። ያለሰላም እድገትና ብልፅግና ሊረጋገጥ አይችልም። ብጥብጥ ካለ ዲሞክራሲ፤ ልማት፤ እድገት የሚባል ነገር የለም። አዲስ እድገት ማምጣት ይቅርና ዜጎች ለረጅም ዓመታት ለፍተው ደክመው ያፈሩት ሀብትና ንብረት ይጠፋል። ለዚህ ሌላ ምሳሌ አያስፈልገንም በአይናችን አይተናል። ስለዚህ ለልማት ለእድገት ሰላም ያስፈልገናል። በሶስተኛ ደረጃ ሰላም የመጨረሻ የሆነ የዜጎች እሴት ነው። ዜጎች ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጡት እሴት ነው። ስለዚህ ይሄንን ማረጋገጥ ያስፈልገናል።

ስለዚህ የግጭት ስጋቶችን ባሉበት ማምከን ተቋሙ ትኩረት አድርጎ የሚሰራበት ጉዳይ ነው። ክልሎች ከክልሎች ጋር ጤናማ ግንኙነት እንዲኖራቸው፤ ከሌሎች ከፌደራል መንግስት ጋር ያለው ግንኙነትን ጤናማ ለማድረግ ሰላም ሚኒስቴር በርካታ ስራዎችን እየሰራ ነው። ግጭቶችም ቢፈጠሩ በአግባቡ በመመልከት የተፈጠረውን ግጭት ወደ ሰላም ለማምጣት ይሰራል። ይህን ሁሉ አልፈው ወንጀል የሚፈፅሙ አካላት በህግ እንዲጠየቁና በአገሪቱ የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ይሰራል።

**አዲስ ዘመን፡-ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሕወሓት ወደ ሰላማዊ መንገድ እንዲመጣ የሚጠበቅበትን ነገር አድርጓል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ብናልፍ፡-** በመንግስት በኩል ያለው ፍላጎት የሰላም ፍላጎት ነው። መንግስት በሰላም በኩል አንድም ቀን በሩን የዘጋበት ጊዜ አልበረም። ምንም እንኳን መንግስት የጦርነት ፍላጎት ባይኖረውም ትህነግ ግን በግድ ለመከላከል ወደ ጦርነት እንድንገባ አድርጎናል። ችግሮች በሰላም እንፍታው በሚል መንግስት ተደጋጋሚ ጥሪዎች አቅርቧል። ይሄንንም ለዓለም አቀፍ ማህበረሰቡ በተደጋጋሚ አሳውቋል። ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡ የሰላም ጥረቱን እያወቀ በጅምላ ጦርነት አቁሙ ከማለት በስተቀር ጦርነቱን የቀሰቀሰውን አካል ለይተው አያወግዙም። ትህነግ ሶስት ጊዜ በተከታታይ ጦርነት እየቀሰቀሰ ይህም እየታወቀ ነጥለው አያወግዙትም። ነጥለው ይሄንን አካል ቢያወግዙ ደጋፊዎችም እጃቸውን በመሰብሰብ ትህነግ ወደ ሰላም የሚመጣበትን እድል ያሰፋታል።

ዜጎችን ለመከላከል ጥረት የሚያደርገውን መንግስት ከማውገዝም በላይ የተለያዩ ማእቀቦችን እየጣሉ የሰላምን መንገድ ከማጥበብ ባሻገር ሁሉንም ወደ ማስማማት የሚያመጣ ሀሳብ እየመጣ አይደለም። መንግስት ብዙ ጊዜ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለሰላም የሚሆን ጥረት ያድርግ በማለት ጥሪ ሲያስተላለፍ ቆይቷል።

አሁንም ቢሆን ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የሰላም ጥረቱ ላይ መሳተፍ ይገባዋል። መንግስት ዛሬም ቢሆን የሰላም ጥረቱን አላቆመም ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ቆም ብሎ ግጭት የሚፈጥረውን አካል ተፅእኖ ቢያደርግበት ለውጥ ይመጣል። ከመጋረጃው ጀርባ ሆነውም ድጋፍ የሚያደርጉ ኃይሎች እጃቸውን እንዲሰበስቡ የዓለም አቀፍ ማህበረሰቡ ተፅእኖ ቢያደርግ ለሰላም መፍትሄ ይመጣል ብዬ አስባለሁ።

የሽብር ቡድኑን በተለያየ መንገድ የሚደግፉ አንዳንድ የምዕራባውያን አገራትም ከተሳሳተ መንገዳቸው በመውጣት የሽብር ቡድኑን ጸብ አጫሪነት ሊያወግዙ ይገባል። በጠረጴዛ ዙሪያ ተነጋግሮ ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ ጦርነትን የመረጠው አሸባሪው ትህነግ ለሦስተኛ ዙር ጦርነት የትግራይን ህዝብ ከህጻን እስከ አዋቂ መመልመሉ ተገቢነት የሌለውና ሰብዓዊነት የጎደለው ተግባር ነው። የአሸባሪው ሕወሓት ትንኮሳ ቢኖርም መንግሥት እየተከተለ ያለውን የሰላም አማራጭ እንዳጣናከረ መንግሥት ከሰጠው ተደጋጋሚ የሰላም እድል ለመጠቀም የትግራይ ህዝብ አሸባሪውን ትህነግ ከድርጊቱ ሊያስቆመው ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡-የአገሪቱ ሰላም ለቀጠናው ብሎም ለአፍሪካ ካለው ፋይዳ አንፃር የምእራባዊያን ጫና እንዴት ይገለፃል?**

**አቶ ብናልፍ፡-**ለኢትዮጵያ ሰላም ዋነኛ ተጠቃሚዎች ኢትዮጵያዊያን ናቸው። በጦርነቱ ከፍተኛ ተጎጂዎችም የዚህች አገር ህዝቦች ስለሆኑ ማለት ነው። ዋነኞቹ ተጠቃሚዎች ኢትዮጵያዊያን ቢሆኑም ዳፋው ለቀጠናው አገራት ይተርፋቸዋል። የኢትዮጵያ ሰላም መሆን ለአፍሪካ ቀንድ ቀጠና አገራት ጥቅም አለው። አገሪቱ ሰላም ስትሆን ከራሷ አልፋ የተለያዩ ጊዜ የሰላም ማስከበር ስራዎችን በመስራት ከጎረቤቶቿም አልፋ ለሌሎችም ትተርፋለች።

ይህች አገር ሰላም እንድትሆን ከተደረገ ሁሉም ሰላም ይሆናሉ፤ አሁን በቅርቡ እንደምናየው በጎረቤት አገሮች ያሉ ችግሮች እንዳይባባሱ በመልካም ጉርብትና ስለሰላም ስትሰራ ቆይታለች። አገሪቱ በጦርነት ስትታመስ ከቀጠናው ውጪ መላው አፍሪካ ብሎም ዓለም በአንድም በሌላም ሊጎዱ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ሰላም ለዓለም ሰላም ፋይዳ ያለው መሆኑን በመረዳት ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ትኩረት አድርጎ መስራት የሚገባው ሰላም ላይ መሆኑን ላሳስብ እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ዛሬ ጦርነት ላይ ብንሆንም መጨረሻው ሰላም እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን፤ ከጦርነቱ ማብቃት በኋላ አገሪቱ ሰላሟን አስጠብቃ እንድትኖር ከሌሎች አገራት ተሞክሮ በመነሳት ምን መሰራት ይኖርበታል ?**

**አቶ ብናልፍ፡-** አገራት ወደ ጦርነት የሚገቡት አንድም ወደው በሌላ በኩል ደግሞ ተገደው ነው። ምንም ይሁን ግን ጦርነት የመጨረሻ መፍትሄ ሲሆን ታይቶ አይታወቅም። ምናልባትም መፍትሄ አምጥቶ ከሆነ እጅግ በጣም ጥቂት ሊሆን ይችላል። በዓለም ላይ የተካሄዱ ትልልቆቹ የዓለም ጦርነቶች ላይ በርካታ ህዝብ አልቆ እንኳን መጨረሻ ላይ ዓለም ወደ ተረጋጋ ነገር እንዲመጣ ቁጭ ብለው ተነጋግረዋል። የተረጋጋ አገር እንዲፈጠር ቁጭ ብለው በመነጋገር አሁን የምናያትን አውሮፓንም፤ ሌሎቹንም አህጉራት ሊፈጥሩ ችለዋል።

አውሮፓውያን በጦርነቶቹ ተጎጂ እንኳን ብትሆን ከጥፋቱ በኋላ እንዴት ማገግም እንደሚችሉ ዳግም ወደጦርነት እንዳይገቡ በመስማማታቸው ሰላም ማምጣት ችለዋል። በጣም ዘግናኝ የዘር ማጥፋት የተደረገበት ርዋንዳም ካለፈው ትምህርት ወስደው በመስማማት ወደሰላም መጥተዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ አሁንም ሰላም ሊያመጣ የሚችለው ብቸኛው መንገድ ሰላም ብቻ ነው። አሸናፊና ተሸናፊ በማለት ድጋሚ እያገረሸ ችግሮችን ከመፍጠር የበለጠ መፍትሄ የለም። አሁንም ከጦርነቶቹ በኋላ የሰላም አማራጮችን እያዩ የማስፋት አማራጭ አለ።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻም ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልእክት ካለ ዕድሉን ልስጦት?**

**አቶ ብናልፍ፡-** ለህዝቡ ማስተላለፍ የምፈልገው የመጀመሪያው ነገር ሰላምን ከውጭ መፈለግ የለብንም የሚል ነው። ሰላምን ከእራሳችን ጀምሮ መጠበቅ ይኖርብናል። ሁላችንም የውስጥ ሰላም ካለን አገራችን ሰላም የምትሆንበትን ነገር ፈጠርን ማለት ነው። ቀና አስተሳሰብ በማስፈን፤ ልዩነትን በመቻቻል፤ እንዲደረግብን የማንፈልገው ነገር ሌሎች ላይ ባለማድረግ፤ የአብሮነት እሴታችንን አስጠብቀን ለማቆየት የሁላችንንም ጥረት ይጠይቃል። ሁላችንም ኢትዮጵያዊያን ለሌሎች መተው የሌለብን ነገር የሰላም ስራን ነው።

በእኔ እምነት መጪው ጊዜ ብሩህ ነው፤ አሁን ግን እየተፈተንን ነው። በዚህ ውስጥ እያስመዘገብን ያለናቸው ትልልቅ ድሎች አሉ። አሁንም ፈተና ውስጥ ነን። ይሄንን ፈተና ከተሻገርን ግን መጪው ጊዜ ያለጥርጥር ወደ ብልፅግና በመጓዝ ሰላምን እናሰፍናለን። ፈተናውን ግን ሁላችንም በአንድነትና በፅናት መሻገር አለብን።

መንግስት መቼውንም ቢሆን ቅድሚያ የሚሰጠው ለሰላም ነው። ጦርነት ስንገደድ የምንገባበት ብቻ ነው። ከጦርነት ምንም አይነት ጥቅም አይገኝም። የጦርነት አባዜ የተጠናወታቸው ወገኖችም ሰለማዊ እይታን ቢያሳድጉ መልካም ነው። ሰላም የማይፈልጉ አካላት ሰላምን ምርጫቸው ቢያደርጉ ህዝቡም ሰላም ለሚያመጣ ነገር በሙሉ ዋጋ በመክፈል ሰላም በአገራችን እንዲሰፍን ጥሪዬን አቀርባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ውድ ጊዜዎን ሰውተው ሀሳቦትን ስላካፈሉን እናመሰግናለን።**

**አቶ ብናልፍ፡- እኔም አመሰግናለሁ**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የሕወሓት ሴራና ቅዠት በምስጢራዊው የ“ማጠቃለያ ምዕራፍ አካሄድና ስትራቴጂ”

**ማሙሻ ከአቡርሻ**

የጠላትነት ስዕል ፈጥሮና ይሄንኑ በሰነድ አስደግፎ ሕዝብን በተዛባ ትርክት እየሸነገሉ ለማሳመንና ከጎኑ አሰልፎ ጋሻ ለማድረግ የመስራት የግማሽ ምዕተዓመት ልምድ ያለው አሸባሪው ሕወሓት፤ ዘንድሮም እንደ ደደቢት ጥንስሱ የጥፋትና የጠላትነት ትርክትን የከተበ ምስጢራዊ ሰነድ አዘጋጅቶ “የማጠቃለያ ምዕራፍ አካሄድና ስትራቴጂ” በሚል የዳቦ ስም ሰጥቶ የአገር ክህደት ጉዞውን መቋጫ ለመስጠት ማቀዱን መረዳት ተችሏል። ሰነዱን የጥፋት ቡድኑ ዋና ዋና የፖለቲካና የጦር መሪዎች ያዘጋጁት ሲሆን፤ ይሄንኑ ሰነድ በምስጢር ይዞና በዚሁ ተመርቶ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን ለመበታተን የሚያስችላቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች በማባባስ፤ ብሎም ከአጋር የሽብር ኃይሎች ጋር ተቀናጅቶ በመስራት የተባባሰውን ችግር በሽብር አቀጣጥሎ ሥርዓቱን በመነቅነቅ አገር የማፍረስ ከፍ ያለ ሕልም መሰነቃቸውን ያሳያል። መቐለ ላይ ቁጭ ብለው ያዘጋጁት እና ነሃሴ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ወደስራ እንዲገባ የወሰኑትን ይሄን ምስጢራዊ ሰነድ በወፍ በረር ለመመልከት እንሞክር።

### ነገረ ሕወሓት _ ሰላም ጠል ጉዞው

የሽብር ቡድኑ ሲሻው ፋሽስት፣ ሲፈልግ ደግሞ አሃዳዊው መንግሥት ብሎ የሚጠራው በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የሚመራውን መንግስት የወሰደውን የተናጠል ተኩስ አቁምና የሰላም አማራጭ ተስፋ የሌለውና በቡድኑ ተቀባይነት እንዳልነበረው በሚያረጋግጥ ነው ጽሑፉ የሚጀምረው። በመግቢያው ክፍል “መንግስት ያዘጋጀው የሰላም አማራጭ ከመጀመሪያውም የማይሆንና የትግራይን ሕዝብ ጥያቄ ፈፅሞ የማይፈታ መሆኑ ቀደም ብሎም የታመነበት ነው፤” በማለት ነው ቡድኑ ፈጽሞ ሊቀበለው እንደማይችል ያውቀው እንደነበር ያረጋገጠው። ከዚህም ባለፈ በአፍሪካ ሕብረት አደራዳሪነት ላይ እምነት እንደሌላቸው በሰነዱ በግልጽ ያስቀመጡ ሲሆን፤ ችግሮች በሰላም ሳይሆን በጦርነት ብቻ እንደሚፈቱ የሚያስበው ይህ ቡድን “ለሁለንተናዊ የመጨረሻ ምዕራፍ ዘመቻ ልንዘጋጅ ግድ ይላል” ሲል ለዓላማው ተከታዮች ያሳስባል።

በአደራዳሪነት የተመረጡት የአፍሪካ ህብረት ልዩ መልዕክተኛ ኦሊሴንጎን ኦባሳንጆ፣ ምንም እንኳን ባካበቱት ልምድና በገነቡት ስም የምናከብራቸው ቢሆንም፤ ... የሕዝባችን ዘላቂ የሰላም ዋስትና የሚረጋገጠው በዐቢይ የሰላም አማራጭ ሳይሆን፣ በክንዳችን ብቻ መሆኑን በፅኑ እናምናለን። የትግራይ ሕዝብ የሚበጀውም ጦርነቱ የጠየቀውን ያክል የሕይወት መስዋእትነት ከፍለን አዲስ አበባ የሚገኘውን ፋሺስቱን ዐቢይ መንጥረን ሕዝባዊ መንግሥት ማቋቋም ስንችል ብቻ ነው።

በዚህ ሂደትም ዓለማቀፉን ማህበረሰብ በማስመሰል የፕሮፖጋንዳ አሰራራቸው መሰረት ከጎናቸው ማሰለፍ እንደሚገባቸው በአግባቡ በሰነዱ ያስቀመጡ ሲሆን፤ ይሄንኑም “በጦርነት ሂደት ውስጥ የመረጃ ልዕልና ለማግኘት እና በርካታ ኃይሎችን ከጎንህ ለማሰለፍ ከሚያስችሉ ሁኔታዎች አንዱ፣ ለዓለም አቀፉ ማህብረሰብ ችግሮችን በሰላም ለመፍታት ቁርጠኝነት እንዳለህ አስመስለህ እራስህን ማቅረብ መሆኑ ሊረሳ አይገባም፤” በሚል በግልጽ አስፍረውታል።

ለዚህ ደግሞ የራሳችንና የአጋሮቻችን ዝግጁነት ከመቼውም ጊዜ በላይ በተሻለ ሁኔታ ይገኛል። የውስጥ ትግላችን በማገዝ የሚንቀሳቀሱ እንደ ኦነግ የመሳሰሉ አጋሮቻችን እንዲሁም በተለያዩ የዓለም መአዘናት የሚገኙ የትግራይ ዲያስፖራና ዓለም አቀፍ አጋዦቻችን በዚህ ጊዜ የተሳካ ጥምረት በማድረግ ወደ አዲስ አበባ በምናደርገው እንቅስቃሴ ከጎናችን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑን የክልላችን ዋና ስራ አስፈፃሚ በዝግ ባደረገው ውይይት አረጋግጧል። ስለሆነም ይሄ ፅሁፍ ከአጋሮቻችን ጋር የምንከተለውን ስትራቴጂ አስመልክቶ በየደረጃው ለሚገኝ አመራር ግብአት እንዲሆን የቀረበ ነው” ሲል ወደ ዋና ጉዳዩ ያንደረድራል።

### የሕወሓት ስልታዊ “መንታ ገጽ”ነት

አሸባሪው ሕወሓት የአማራ ሕዝብን በጠላትነት ፈርጆ ትግል ከመጀመሩም በላይ፣ በ27 ዓመታት የስልጣን ዘመኑ አማራ ጠልነቱን በተግባር ያሳየ ኃይል ነው። በዚህም በርከት ያሉ አማራ ጠል ተረኮችን ከማዘጋጀትና ከማኖር ባለፈ፤ በልዩ ሁኔታ የአማራው ሕዝብ ተረጋግቶና ራሱን አደራጅቶ እንዳይኖር አድርጎት ቆይቷል። በኋላም ከስልጣን ተወግዶ መቐሌ ከመሸገና በአገር መከላከያ ሰራዊት ላይ ጥቃት ፈጽሞ የአገር አፍራሽነት ተልዕኮውን ባረጋገጠ ማግስት፤ በአማራ ሕዝብ ላይ ሂሳብ አወራርዳለሁ ብሎ በፈጸመው ወረራ እልፍ አማራዎችን በጅምላ ጨፍጭፏል፤ ሃብት ንብረታቸውን ዘርፏል፣ አቃጥሏል፤ አውድሟል፤ ለማይሽር የአካልና ሥነልቦና ጉዳትም ዳርጓል። በተመሳሳይ ይሄንኑ የእርኩሰት ተግባር በአፋር ሕዝብ ላይ ፈጽሟል።

ሕወሓት በተለይ በአማራ ህዝብ ላይ ያለው የማይወላውል የጥላቻና የጠላትነት ስዕል እንዳለ ቢሆንም፤ እንደ ጊዜና ሁኔታው የአማራን ሕዝብ የጠላትነት ደረጃና ወሰን ከፍና ዝቅ እያደረገ፣ አንዳንዴ ልሒቁን ከአርሷደሩ ለመነጠል፤ ሌላ ጊዜ የጥምር ኃይሉን ከሕዝቡ ለመነጠል፤ አንዳንዴም ሙሉ ሕዝቡን ወዳጅ አድርጎ የመሳል፤ ከፍ ሲልም የታጠቀውን ጥምር ኃይል ሳይቀር በፌዴራል መንግስቱ ተታልሎ የገባበት እንጂ የአማራ ሕዝብ ሕዝባችን ነው፤ ከእነሱ ጋር ጠብ አንፈልግም፤... ሲል መደመጡ የተለመደ ሆኗል። በዚሁ ሰነድም እንደቀደሙት ሁሉ ተመሳሳይ የሆነ የአስልቶ አራጅነት ስልታዊ የጠላትነት ገጽ መፍጠር የታየበት ነው።

በዚህ ረገድ በሰነዱ እንዲህ አስፍረውታል፡- የአማራ ተስፋፊ ሃይል ከፋሽስት ዐቢይ በሚሰጠው ትዕዛዝ መነሻ እና በቆየ የትምክህት ታሪኩ፣ ተስፋፊነቱና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመጫን የሚያደርገው እንቅስቃሴ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ...በአማራ ክልል ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ሃይሎች ጦርነቱ በፈጠረላቸው አጋጣሚ ተጠቅመው በርካታ ገንዘብ ያገኙ ሲሆን፤ ይህም ራሳቸውን በትጥቅ ያደራጁ ፅንፈኛ ተስፋፊ የአማራ ሃይሎች እንዲፈለፈሉ አድርጓል። ይሄ ሁኔታ የተፈጠረው በሌሎች ክልሎች ቢሆን ኖሮ ለትግላችን ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነበር። ነገር ግን ይሄ ሁኔታ የተፈጠረው በአማራ ክልል መሆኑ... ከዚህ ቡድን ጋር ወዳጅነት ሊኖረን አይችልም፤ ይልቁንም ከሁኔታው በመነሳት ቡድኑን በጠላትነት እንፈርጀዋለን።

ይሄ ፅንፈኛ የአማራ ተስፋፊ ሃይል... በክልሉ ያገኘውን ሕዝባዊ ተቀባይነት ሽፋን በማድረግ እና ጠንካራ ቅንጅት በመፍጠር ከአማራ ክልል መንግሥት የሚስተካከል አቅም መፍጠር በመጀመሩ እና ይሄ ሃይል ራሱን “ፋኖ” ብሎ በመጥራቱ የዐቢይ አስተዳደር በወሰደው ርምጃ በተወሰነ መልኩ መዳከም ታይቶበታል። ...ይሄ ሁኔታ የትግራይ ሰራዊት እንደ ጥሩ አጋጣሚ ሊጠቀምበት የሚገባ ሲሆን፤ ... ይህንን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ስራ በመስራት የተፈጠረውን መሻከርና ክፍተት የበለጠ እንዲከር ማድረግ ይገባል።...

በአማራ ክልል በተወሰነ መልኩም ቢሆን ፊቱን ወደ ልማት ያዞረ ገበሬ እየታየ ነው። ...ይህ ሃይል የእርሻ ውጤቱን ወደ ቤቱ እንዲያስገባ ልንፈቅድለት አይገባም። ...ለጦርነት ባልተዘጋጁበትና በዐቢይ የሰላም ጥሪ በተዘናጋበት ጊዜ አስፈላጊ የሚባል ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። ...ከወታደራዊ ዘመቻዎቻችን ጎን ለጎን የቅማንት የወሰንና ማንነት ጉዳዮችን በሚመለከት እዛ አካባቢ ከፍተኛ ሕዝባዊ ጥያቄ እንዲነሳና አካባቢውን ወደማያባራ ፖለቲካዊ ማህበራዊ ችግር ሊለውጥ የሚያስችሉ ስራዎች መስራት አስፈላጊ ነው።

### ተደማሪ የጠላትነትና አጋርነት ትንተናዎች

የሽብር ቡድኑ በአማራ ሕዝብ ላይ ከያዘው የጠላትነትና የስልታዊ የለውጥ ጉዞው ባሻገር፤ የአፋር፣ የሶማሌ እንዲሁም ኦሮሚያ አካባቢ አሉብኝ የሚላቸውን ሥጋቶች፤ አሉኝ የሚላቸውን እድሎችና አጋሮች በሰፊው ተመልክቷል፤ በምስጢራዊ ሰነዱም በግልጽ አስፍሯል። ለምሳሌ፣ በአፋር ያለውን ስጋትና ተስፋ ሲያስቀምጥ፤ “የዓፋር መንግሥት... ከዐቢይ አስተዳደር በሚሰጠው አድናቆትና ቁጥር የሌለው የትጥቅ እገዛ አይኑ የታወረ፣ ጆሮው የተደፈነ በመሆኑ፣ ትግላችን በሚያግዙ የዓፋር የነፃነት ታጋዮችና ቤተሰቦቻቸው አፈናና ግድያ እየፈፀመባቸው ይገኛል” በማለት ነው። በተመሳሳይ፤ “በሱማሌ ክልል ያለው የሙስጠፌ ዑመር አምባገነን አስተዳደር... የአሸባሪውን አልሸባብ እንቅስቃሴ ለመግታት በሚል ምክንያት በርከት ያለ ወታደራዊ ትጥቆች የታጠቀ እና ዝግጅት ያለው ሲሆን፣ የዐቢይ ሰራዊት በትግራይ ሰራዊት ላይ ባደረጋቸው ዘመቻዎች በንቃት የሚሳተፍ የትግራይ ሕዝብ ጠላት በመሆኑ፣ በክልሉ ከሚንቀሳቀሱ እና የጋራ ጠላታችንን ከሚታገሉ የአልሸባብ ሴሎችና ከኦጋዴን ታጋዮች ጋር የመረጃ ልውውጥ እገዛ እና ስትራቴጂ ሥራዎቻችን ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል” ሲል አስቀምጧል።

ከዚህ በተጨማሪ በኦሮሚያ ክልል ስለሚንቀሳቀሰው እና ቀደም ብለው “ያልተቀደሰውን ጋብቻ” ለሽብር አብሮ የመስራት ትብብራቸውን ይፋ ባደረጉት ሸኔ ላይ ያለውን ተስፋ እና ተስፋውን እውን በማድረግ ሂደት እያጋጠሙ ያሉ ፈተናዎቹን ከመፍትሄዎቻቸው ጋር አሰናስሎ ያቀረበበት ሃቲት ተጠቃሽ ነው። ሃቲቱም በሰነዱ በሚከተለው መልኩ ተቀምጦ ይገኛል፡- በኦሮሚያ ክልል የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት የትግላችን አጋር መሆኑን በግልጽ ማሳወቃችንን ተከትሎ እንዲሁም በክልሉ ያለው ይዞት እየሰፋ በመምጣቱ የተነሳ ፋሺስቱ ዐቢይ ከሰሜን ግንባር በማያንስ የተጠናከረ ኦፕሬሽን እያካሄደ እንደሚገኝ የፋሺስቱ የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን እየተቀባበሉት ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ ግንባር ላይ የሚገኙ የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት አመራሮች እንደሚነግሩን ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው እንዳለና የትግል ስልት መቀየር ግዴታ እንደሆነባቸው ማየት ተችሏል። ...ይሁን እንጂ መንግስትን በማዳከም ወደ አዲስ አበባ የሚደረገው የመጨረሻ የትግል ምዕራፍ ላይ የቅርብ አጋዦች እነዚህ የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት በመሆናቸው ሊስተካከሉ የሚገባቸው እና ባለፈው ግምገማ የታዩ ክፍተቶች ታርመው ወደ መጨረሻው ምዕራፍ እንዲዘጋጁ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

### ለማጠቃለያው ምዕራፍ ራስን ማዘጋጀት

የሕወሓት የሽብር ቡድን ጦርነትን እንደ ሕልውና ማስቀጠያ አድርጎ እንደመያዙ፣ ለዚህ ጦርነት የሚውለውን የሰው ሃይልም ሆነ ሎጀስቲክስ ማሰባሰብ ትልቁ የቤት ሥራው ነው። ለዚህ ሥራው ደግሞ ቢችል ቀድሞ በፈጠረው የጠላትነት ሥዕል ታግዞ ፍላጎቱን ማሟላት፤ ሳይችል ደግሞ በሰብዓዊ ርዳታ መያዣነት የሰው ሃይሉን ማጠናከር፤ ካልሆነም በቅርቡ ሲያደርግ እንደነበረው ከጎኑ ያልተሰለፈ ቦታ እንደሌለው አስፈራርቶ በመንገር የሕዝብ ማዕበል መፍጠር ስትራቴጂካዊ መንገዶቹ ናቸው። የሎጀስቲክስ ጉዳዩም ቢሆን፣ ምግብን ከሰብዓዊ ድርጅቶች በመዝረፍና ሕዝቡን በማስገደድ፤ ትጥቁንም በመንግስትነት ዘመኑ ደብቆ ካከማቸውና ከዘረፈው፣ እንዲሁም ከታሪካዊ የኢትዮጵያ ጠላቶች በሚያገኘው የሚያሰባስበው ነው። ይሄው እውነት በተለያዩ ጊዜያት ሲገለጽ የቆየ ሲሆን፤ በዚህ ምስጢራዊ ሰነድ የተመላከተውም ይሄው ሃቅ ነው።

በሰነዱ ባሰፈሩት መሰረትም፤ እስከ ቀበሌ ያሉ አደረጃጀቶችን ተጠቅመው ባካሄዱት ስራ ባለፉት ወራት ብቻ በርከት ያሉ ወጣቶች ወደ ታጣቂ ቡድኑ እንዲገቡ በማድረግ የተሳካ ስራ ሰርተዋል። ለዚህም የትግራይ ወጣቶችን አሁን የሚደረገው ትግል ወደ አዲስ አበባ የመግባት የመጨረሻ ምዕራፍ ትግላቸው እንደሆነ በማሳመን የሕወሓት አመራር ካለፈው ዘመቻ ራሱን ገምግሞ የነበሩበትን ክፍተቶች በሙሉ በመዝጋት ለመንቀሳቀስ ቆርጦ መነሳቱና ድል አይቀሬ መሆኑን መላው የትግራይ ወጣትና ሕዝቡን ለማሳመን የሚያስችል የሚዲያ ሥራ እየተሰራ ይገኛል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ “የመሳሪያና ትጥቅ አቅም አለማጠናከር ባለፉት ዘመቻዎቻችን የነበረብን ክፍተት እንደሆነ ተገምግሟል። ይህንን ግምገማ በማየት በውጭ ያሉ አጋዦቻችን በአስቸጋሪ እና አጣብቂኝ ጊዜ ውስጥም ቢሆን ችግሩን አልፈው ዘመናዊ ትጥቆች እንድንታጠቅ አድርገውናል። ይህም ሆኖ የዚህ ዘመቻ ምዕራፍ መራርና በርካታ መስዋእትነት የሚጠይቅ በመሆኑ አሁንም ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ዘመናዊ ትጥቅ ለመከላከያ ሃይላችን እንዲያቀርቡልን የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ከውስጥና ከውጪ ተባባሪዎቻችን ጋር ያለንን ስራ አጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል፤” ሲል ያስቀምጣል።

የስንቅ አቅርቦቱን አስመልክቶም፤ “የታጋዮቻችን ትጥቅና ስንቅ የሚሟላት ስራ በዋናነት በነፃነቱ የማይደራደረው ሕዝባችን ተግባር ይሆናል፤ በትግራይ የሚገኙ የዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች ሰብአዊ ድጋፍ ማከማቻ መጋዘኖች ፋሽስቱን ለማስወገድ በምናደርገው ትግል የስንቅ አቅርቦት እንዳይጓደል በቁጥጥራችን ስር ልናደርጋቸው ይገባል። ይሄም ከዓለም አቀፍ የእርዳታ አስተባባሪዎች አወንታዊ የሆነ ግንኙነቶች በማጠናከር ረሃብና ተረጅነት ከሕዝባችን ትከሻ ላይ ለማውረድ ለምናደርገው ትግል ደጋፊ እንዲሆኑና ከጎናችን እንዲቆሙ ልናደርግ ይገባል፤” በማለት ነበር ከጫካ ጀምሮ የኖረበትን አሰራር ዛሬም አለመልቀቁን ያረጋገጠበትን እውነት ያሰፈረው።

### የመረጃ ልውውጥና ፕሮፖጋንዳ ስልት

ቡድኑ በውስጥም በውጪም ካሉ ተባባሪ ሃይሎች የመረጃ ቴክኖሎጂዎችን የማግኘትም ሆነ የሃሰት ፕሮፖጋንዳዎችን ተቀናጅቶ የማሰራጨት ልምዱ ቀደም ባሉት የአገር ማፍረስ ስምሪቶቹ ተስተውሏል። አሁንም በዚህ ምስጢራዊ ሰነዱ ይሄው እውነት እንዲህ ተሰድሮ ይገኛል፡- አንዱና ዋነኛው የውስጣችን ጥንካሬ መገለጫ ውስጣዊ አቅማችንና የአሸናፊነት ስነልቦና በመሆኑ ይሄን ከፍ የሚያደርጉና የሚያነቃቁ ስልጠናዎችና የዶክመንተሪ ስራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። ከሠራዊታችን በተጨማሪ፣ መላው የትግራይ ሕዝብና በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያም ውጪ ለሚገኙ የትግል አጋሮቻችን ድላችን እንደማይቀር እያበሰርን እስከ መጨረሻ መዳረሻችን አብረውን እንዲጓዙ የሚያስችል ስራዎች፣ ስልጠናዎች፣ የመረጃ ልውውጥና ፕሮፖጋንዳ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል።

በተመሳሳይ በጠላት ላይ ሽብር፣ ፍርሃትና የስነ ልቦና ጫና መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣ ሽብር የሚያስፋፉ እና በመሀል አገር ያለው ሕዝብ ሳይቀር በመንግሥት አቅም ላይ ያለው እምነት እንዲሸረሸር የሚያደርጉ መረጃዎች በአገር ውስጥና በውጪ ሚዲያዎች በሙሉ ማዳረስ ያስፈልጋል። ...ከአገር ውጪ የሚገኙ የኦሮሞ ፖለቲከኞችና የሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ልሂቃን የሚመሯቸው በውጪ አገር ያሉ ሚዲያዎች፣ የጋዜጠኛ ቴዎድሮስ ፀጋይ ርእዮት ሚዲያ፣ የጋዜጠኛ ኤርሚያስ ለገሰ ኢትዮ 360 እና ሌሎች በትግራይ ተወላጆች የሚመሩ ሚዲያዎች ተከታታይነት ያላቸውና በዋነኝነት ፋሺስት ዐቢይ ላይ ያነጣጠሩ የማዳከምና የመበተን ስራዎች ሊሰሩ ይገባል። ይሄም በፓርቲያችን የፕሮፖጋንዳ ክፍል በሚቀረፁ መልዕክቶችና ይዘቶች የሚመራና በላይኛው አመራሮች ክትትል የሚደረግበት ይሆናል።

ከዚህ በተጨማሪ ወደ አማራ ክልል በተፈናቃይና በተጓዥ ስም የሚገባ ሃይል ሊዘጋጅና ሥራውም በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊፈፀም ይገባል። ይህ ወደ ክልሉ የሚገባ ሃይል በተቻለው መጠን የትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቅሞ ወደ አዲስ አበባ ዙሪያም ሊጠጋ ይገባል። አስርገን የምናስገባው ሃይል በየደረሰበት አካባቢዎች መረጃና ሁኔታ የሚጠቁምዋቸው አመራሮች ይኖራሉ። ይህ ስራ ከዚህ በፊት እንዳጋጠመን ታጋያችን ለተልዕኮ ዝቅተኛ ትኩረት በመስጠት በማያስፈልግ የምዝበራና ዘረፋ ተግባር እንዳይሳተፍ ከፍተኛ የሆነ የዲስፕሊን አቅጣጫ ይሰጣል።

### ሕዝብን እረፍት የመንሳት ሴራ

የሽብር ቡድኑ አንዱና የሚታወቅበት ሴራ፣ ሕዝብ በአንድ ሃሳብ ሆኖ በአንድነት እንዳይቆም የተለያዩ አጀንዳዎችን በማቀበል ረፍት እንዳያገኝ በማድረግ ከመንግስት ጋርም ሆነ እርስ በእርሱ እንዳይናበብ ማድረግ ነው። ይሄ የህዝብ አለመናበብና በተለያዩ ጉዳዮች ተጠምዶ አንድነቱን እንዲያጣ የማድረግ ሴራው ደግሞ ሕብረት በሌለው ሕዝብና መንግስት ውስጥ በቀላሉ ሰርጎ ለመግባትና የሚፈልጉትን ነገር ማግኘት ይቻላል የሚል እምነት በማሳደራቸው ነው። በርግጥ ይሄ ሕልማቸው የሚሳካ ባይሆንም፤ ይሄን አካሄዳቸውን ግብ በሚከተለው መልኩ ነው ነድፈው ያኖሩት፡-

በግንባር ላይ ከሚገኘው ድል ባልተናነሰ፣ የጦርነት ነጋሪት በመጎሰምና የተሳካ የፕሮፖጋንዳ ስራ መስራት ብቻውን የሚያደርሰው ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች ጠላትን ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍሉታል። ስለሆነም ፋሺስት የዐቢይ መንግሥት በችግር ጊዜ አሳክቼዋለሁ የሚላቸው የእርሻ ዘርፍም ሆነ የኢኮኖሚ ልእልና በማደናቀፍ ወደ ኋላ መመለስ ከተቻለ በስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ማድረስ ይቻላል። ...የእርሻ ዘርፉ እንዲደናቀፍ በየአካባቢው ግጭት በመቀስቀስ እና ግጭት ለመቀስቀስ የሚያስችሉንን ሃይሎች በማገዝ እረፍት በመንሳት፣ የልማት ስራዎችን ትቶ እሳት ማጥፋት ላይ እንዲጠመድ ማድረግ በረዥም ጊዜ የዐቢይ መንግሥትን ለማዳከም የሚያግዝ ሲሆን፤ ባጭር ጊዜም ደግሞ ለሚካሄደው ወታደራዊ ዘመቻ የጠላት አቅም እንዲዳከም ትልቅ ጥቅም አለው።

ፖለቲካዊ አጀንዳዎች በተለይም የማንነት ጥያቄዎች በጥንቃቄ ሊፈቱ የሚችሉበት እድል ከተፈጠረ የዐቢይ አገዛዝ ጎልቶ የሚወጣበት እድል እንደሚኖረው ቀደም ብሎ ከተፈቱ የማንነት ጥያቄዎች ማየት ይቻላል። ስለሆነም፣ ማንኛውንም አይነት ማህበራዊና ፖለቲካዊ አጀንዳዎችን ሳንንቅ ወደ አደባባይ እንዲመጡ በማድረግ፣ ጥያቄዎቹ ሕዝባዊ ቁመና እንዲላበሱ ማድረግ አስፈላጊ ነው። እነዚህ ጉዳዮች ተገቢ ትኩረት እንዲያገኙ ሚዲያዎች፣ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች አጀንዳውን የማቀጣጠል ሚናቸውን በሚገባ እንዲወጡ በማገዝ የፋሺስት ዐቢይን ውድቀት ሊያፋጥኑ ይገባል። ለዚህም አሃዳዊውን የዐቢይ አገዛዝ ከሚቃወሙ ፌደራሊስት ሃይሎች ጋር በተጠናከረ መንገድ ግንኙነታችንን በማደስ፣ በደቡብ ክልል እየታየ ያለውን የክልልነት ጥያቄ በደንብ እንዲጠናከር በማድረግ እንዲሁም ተመሳሳይ የክልልነት ጥያቄዎች በተጠናና በተናበበ መልኩ በሌሎች አከባቢዎች እንዲነሱ ማድረግ ይገባል።

በሌላ በኩል፤ ኢትዮጵያዊያን በተለይም የከተማ ነዋሪዎች፣ መንግሥትን የሚቃወሙት በተለያየ የፖለቲካ አጀንዳዎች አይደለም፣ ከፖለቲካ አጀንዳዎች ይልቅ በቀጥታ ከዕለት ኑሯቸው ጋር የተያያዘው የኑሮ ውድነት ዋና መንግሥትን የሚቃወሙበት አጀንዳ መሆኑ ግልፅ ነው። በርከት ያሉ ዜጎች የኑሮ ውድነቱን መቻል አቅቷቸዋል። ከባድ ፈተና ውስጥ እንዳሉ ብዙ ማሳያዎች አሉ። ስለሆነም የኑሮ ውድነቱን የሚያባብሱ ኢኮኖሚያዊ አሻጥሮችን በተቀናጀ መንገድ መፈጸም አስፈላጊ ነው። ...ስለሆነም የተመረጡ አምራች ድርጅቶችንና መጋዝናቸውን ማጥቃትና ማፍረስ፣ ከእርሻ እስከ ገበያ ባለው ሂደት የዕለት አስቤዛ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እንዲኖረው ማድረግ፣ ከውጪ የሚገቡ ሸቀጦች እና ነዳጅ እንዲስተጓጎል ዋና ዋና የማስገቢያ ኮሪደሮች በመቆጣጠርና ሌሎች እርምጃዎችን በመውሰድ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ችግር እንዲፈጠር እና እንዲባባስ ማድረግ ዋናው ትኩረታችን እናደርገዋለን።

# ጎሜ

# የጠላቴ ጠላት ወዳጄ

**ምሕረት ሞገስ**

ተሰማ መንግስቴ፣ ዘውዴ መታፈሪያ እና ገብረየስ ገብረአምላክ ዛሬ ከወትሮ በተለየ መልኩ እንቅፋት ሲሉ በሚጠሯት ግሮሰሪ በጊዜ ተገናኝተዋል። በፊት በራሱም ይሁን በሌሎች ምክንያቶች ተገንጥሎ የሚቀመጠው ገብረየስ ‹‹ጉግ ማንጉግ›› የሚል ቅጽል ስም ወጥቶለት ነበር። ብቻውን ይበላል፤ ብቻውን ይጠጣል፤ ብቻውን ይቀመጣል፤ ደግሞም ብቻውን ያወራል። እና ይሄ ቅጽል ቢወጣለት ይደንቃል። ዛሬ ግን ምን ገጥሞት ይሆን መቀመጫውን ከዘውዴ እና ከተሰማ አጠገብ አድርጓል። አብሮ እየጠጣ ሊጫወት ዳር ዳር ማለት ቀጥሏል።

በአንድ ጠረጴዛ ሊጋራ የፈለገው ብርጭቆ ማስቀመጫውን ብቻ አይደለም፤ ሀሳቡን ጭምር ነው። ደግሞ እንኳን አሁንና ሌላም ጊዜ ቢሆን የሚወሩ ወሬዎች ሞልተዋል። የኑሮ ውድነት የወሬ ማዳወሪያው ነው። ይሔንን የኑሮ ውድነት እንደ ሸማኔ መወርወሪያ ከወዲያ ወዲህ የሚያነሳ የሚጥለው ሞልቷል፤ ብዙዎች ባይተዋወቁ እንኳን እንደወሬ መግቢያ እንደ መግባቢያ ይጠቀሙበታል። የጋራ ጉዳይም አይደል። ሁሉን አንድ አድርጎ ያግባባል።

በየገበያው በየሱቁ ከሴቶቹ የተሰሙ ምሬቶች ታክለውበት ብዙ እውነት በትንሽ የውሸት ቅመም ጣፍጦ ጭምር የፖለቲካ አካል ሆኖ ወንዶቹም ያሽሞነሙኑታል። እውነቱ ግን እውነት ነው፤ የእያንዳንዱ ሸቀጥ በፊት ከምናውቀው በሁለትና በሶስት እጥፍ ዋጋው ጨምሯል። ይሄን ያላዩ ውድነት የሁሉንም ቤት የሚያንኳኳ በመሆኑ በጨዋታው አልሳተፍም የሚል አይኖሩም፤ ከወንበር ማዶ ያሉትም ቢሆኑ ሀሳብ ባይሰጡ እንኳን በማዳመጡ ይሳተፋሉ።

በአቀማመጡ ሲርቃቸው የቆየው የመጠጥ አጋራቸውም ገብረየስ ገብረአምላክ ይሄ የሰሞኑ ጨዋታ ቢስበው ብሶቱም ቢጨምር መሰለኝ ዛሬ ከጎናቸው መዶሉን በደንብ አምኖበት መርጧቸው ተቀላቅሏቸዋል። እነርሱም ግን አልከፉቸውም። አስጠግተውት ብሶቱን ሲነግራቸው እያባበሉ ያፅናኑታል። ለስጋ ብቻ ሳይሆን ለመንፈስም መደጋገፍ ጉልበት ይሆናልና የልብ ልብ እየተሰማው ከሰዎች ጋር መጠጋቱን እጅግ ወዶታል። ነፃ ሆኖ መወያየት ማውራት አንዳንዴም መከራከሩን ቀጥሎታል።

ዘውዴ መታፈሪያ ስለኑሮ ውድነት ሲወራ በሆዱም ቢሆን ያጉረመርማል። ምን የኑሮ ውድነት ብቻ ኑሮ የሚኖረው እኮ ሰላም ሲኖር ነው፤ መጀመሪያ እነዛ ጉደኞች በሰሜን የጀመሩትን ጦርነት አስቁሞ ሰላም ማስፈን ያስፈልጋል። ኑሮ ረከሰም ተወደደም መብላት መጠጣት የሚያቻለው ሰላም ሲኖር ነው። መዘመር ያለበት ከምንም በላይ ስለ ሰላም ነው እያለ ያንጎራጉራል።

‹‹ልክ ነው! አሁን በአገራችን ሰላም የጠፋበት ጊዜ ነው፤ እንደውም ከኑሮ ውድነቱ በላይ ሊያሳስበን የሚገባው የሰላሙ ጉዳይ ነው›› ብሎ የዘውዴን ውስጣዊ እንጉርጉሮ የሰማ ይመስል ገብረየስም ወሬውን ተቀላቀለው።

ዘውዴ በድጋሚ፤ ‹‹በሰሜኑ አካባቢ ያለው የሰላም መደፍረስ ደግሞም በዚህ በኦሮሚያ አካባቢ ያለው የሸኔ ጉዳይ ተወርቶ የሚያልቅ አይደለም።›› አለ። ተሰማ በበኩሉ ‹‹ጉድ እኮ ነው! ጉድ ነው የገጠመን የእናት ጡት ነካሽ ሁላ›› አለ። ገብረየስ ደግሞ የሚያሳዝነው ንፁሃኑ የትግራይ ህዝብ ነው። ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሲያለቅስ ይኖራል እንደሚባለው ሆኖበት ህዝቡ ከሕወሓት ሲፈጠር ጀምሮ የሰላም አየር ተንፍሶ አያውቅም። ሁሌ በጦርነት፤ ሁሌ ልጁን ለጥይት፤ ሁሌ አገሩን ለረሀብ ህዝቡን ለተረጂነት... ብሎ ምርር ብሎ ተናገረ ።

ዘውዴ መታፈሪያ የሌላውን ሰው ውስጥ የሚያነብ ይመስላል፤ ‹‹የሕወሓትን የሴራ ፖለቲካ መለስ ብዬ ሳወጣና ሳወርድ መልካም ነገር ልጣ›› አለ። ግንባሩን ጨምድዶ ፊታ ካደረገ በኋላ፤ በውስጡ ሀሳብ እንደሚያብላላ የፊቱ ገጽታ ላይ በሚያሳብቅ መልኩ ዘውዴ በድጋሚ ንግግሩን ቀጠለ። አይ ሕወሓት እንዲህ በሚሊየኖች ላይ ይቀልድ? አለ በድጋሚ።

> ሽፍታው አንድ ቀን አንድ ነገር ከማድረጉ በፊት ‹‹እወድሃለሁ›› እንድትለው ፈለገ። እወድሃለሁ በይኝ አላት። ሴቲቱ እንደገመታት ‹‹እወድሃለሁ›› አላለችውም። አልወድህም አለችው። ‹‹ለምን ?›› አላት። ‹‹በድለኸኛል። እንድወድህ ሳታደርግ አግብተኸኛል፤ ያየኸኝ እንዳንተ እንደሰው ሳይሆን እንደምትፈልገው ዕቃ በመሆኑ እኔ ልወድህ አልችልም›› አለችው

የተጨነቀ ሰው ብሶቱን፣ ጭንቀቱን፣ ህመሙን የሚያስተነፍሰው በንግግሩ ነው። ቀጠለ ዘውዴ ዛሬ መረር ያለው ይመስላል። ‹‹የከፋቱ ክፋት ከሌላው ብሔር ጋር ተጋብቶ ተጋምዶ የኖረውን ህዝብ ሊያባላ መነሳቱን ሳስብ ያንገፈግፈኛል፤ ስንቱ የጎንደር ሰው ከትግራይ ህዝብ ጋር እንደተጋባ ሳስብ ይብስብኛል።›› አለ ።

ገብረየስ በበኩሉ ‹‹በእርግጥ ይህን ካላደረገ ከዚህ በኋላ በስልጣን ዘመኑ የረሳቸው የትግራይ ሰዎች ከፌዴራል እንደወጣው ከክልልም እንዲወጣ ያደርጉታል። ያለጦርነት መኖር አይችልም። በዛ ላይ ውስጣዊ ባህሪውም አይፈቅድለትም።›› ብሎ ዘውዴን መልከት አደረገው።

ገብረየስ ‹‹ሕወሓት ይህን ካላደረገ እንደበፊቱ በየት በኩል ይዘርፋል፤ በየት በኩል በሩቁ የሚቋምጠውን ስልጣን ያገኛል፤ እንዲህ ካልሆነ በሕይወት አለሁ ማለት ይችላል? አይችልም። በሴራ መንገዱ ትክክል ነው ይሄን ማድረግ አለበት። አሁን እኮ ገብቶትም እንዳልገባው እየሆነ ቢሆንም በትግራይ ህዝብ እየተጠላ ነው። አላመነም እንጂ በብዙዎቹ ዘንድ አክ እንትፍ ተብሏል። እናቶች እንቢ ልጆቻችንን ለጥይት ገብረን ቀባሪ አናጣም በቃን! እያሉ ነው። የወሰዳችኋቸው ወጣቶች የት ደረሱ? ብለው እየጠየቁ ነው፤ ግን መልስ የለም ማስፈራራት ዛቻ ብቻ ሆኗል። ያልደገፈን ከደገፈን እኩል መብቱ አይከበርለትም ብለው በሰብዓዊ እርዳታ በማስፈራራት ላይ ነው። ይሔ ደግሞ ብዙ አያቆየውም›› አለ።

ተሰማ መንግስቴ በበኩሉ መንግስት ደግሞ ደጋግሞ ሲዘረጋው የነበረውን የሰላም እጅ የረገጠው ሕወሓት አሁን ደግሞ ጦርነት መክፈቱ ያስገርማል ብሎ ሰሞኑን ጌታቸው ረዳ ሸንፈት ሲከናነብ የሚፖተልከው እና ቀደም ሲል ከአማራ ጋር ሂሳብ እናወራርዳለን ምናምን... ምናምን... ሲል የነበረውን አስታወሰ። የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ አይደል ነገሩ። ‹‹ደግሞ እንዴት እንዳበጠ? ብሎ ተሰማ ተሳለቀ።

ዘውዴ በበኩሉ ‹‹እርሱንማ ተወው ሽንፈት አሳብዶት ነው። ለነገሩ በእኛ በኩል ያለው ተዋጊ ጥበቡ ያስገርማል። ሕወሓት ህዝባዊ ማዕበል በሚል በገፍ ከኋላ እየተገፋ ሲመጣ የመንግስትን የመከላከል ጥበብ ብታይ እና ሳይንሱ ቢገባህ እጅግ ትደነቅ ነበር።›› አለ የውትድርናውን ሳይንስ የሚገልጽበት መንገድ በቦታው ሆኖ በውጊያው ተሳትፎ ያየ ሁሉ እስኪመስል አቀነባብሮና አጣፍጦ ነው። አዋጊም ሚስጢር አዋቂም እርሱ ይመስላል። ትንሽ ነገር አንብቦ ይሆን ወይስ ቀደም ሲል የውትድርናዋን ትምህርት ቀስሞ ብቻ እንጃ በእኔ ውስጥ የተመላለሰ ሀሳብ ብጤ ነው። ከተሳሳትኩ አፉ በሉኝ።

ጥቃት ከምንም በላይ ያማልና አንዳንዴ ሶስቱም ተጠቅቻለሁ የሚል ስሜት ይታይባቸዋል። የዘር ሀረጋቸውን እየመዘዙ ይሆን እንጃ ብቻ ስሜታቸው ይደበላለቃል። የዛኔ አንዱ ሌላውን ታግሶ የሚያልፍ አይመስልም። ነገር ግን በተደጋጋሚ በትዕግስት ይተላለፋሉ።

የዛሬው ተጠቅቻለሁ ባይ ዘውዴ ነው። ትንሽ ንግግራቸው ከረር ብሏል። በተለይ ዘውዴ አልፎ አልፎ ከገብረየስ ጋር የሚከራከሩት የሀሰት ትርክት ደግሞ አወቅኩ ባይነታቸው ለነገ እንገናኛለን የሚያስብል አይደለም። ዘውዴ ያዘዘውን ቢራ በቀኝ እጁ ሁለት ጣቶች መሀል አንስቶ እየተጎነጨ ‹‹የአንዱ ችግር ላይ መውደቅ ለእያንዳንዱ ሰው ጥሩ ስሜት አይሰጠውም፤ የአንዱ ቤት መቃጠል ለሌላው ጫካ ተቃጥሎ ከሰል እንደሚገኝ ተራ ነገር ይቆጥረዋል፤ የእኛ ቤት ሲቃጠል ለማጥፋት ብትረባረቡ አሁን ዞሮ ይሔ ሁሉ ነገር አይመጣም ነበር።›› አለ።

ዘውዴ ለወሬው ማድመቂያ አንድ ተረት ልንገራችሁ አለ። በአንድ አካባቢ አንድ ተፈሪ ሽፍታ ነበር። የፈለገውን እየዘረፈ፤ የፈለጋትን እያገባ ያልፈለጋትን እየፈታ ኖሯል። ሽፍታው በድንገት አንድ ጎረምሳ አብዝቶ የሚወዳትን ልጃገረድ እርሷን እና ቤተሰቧን አስገድዶ አገባት። ያቺ ሴት ሽፍታውን ሳይሆን የምትወደው ያንን ጎረምሳ ቢሆንም ለሽፍታው መልካም ሴት ሆነችለት። እርሱ ከሌላ ሴት የተለየች አድርጎ እንዲወዳት ማድረግ ቻለች።

ታታሪ በመሆኗ ሁልጊዜም ሲመጣ የሚበላ ሰርታ ቤቱን አሰናድታ ሁሉን አሰውባ ታቀርብለታለች። ታጥባ ታጥና ትቆየዋለች። በጊዜ ሒደት አብዝቶ ወደዳት፤ የዘረፈውን ዋነኛ ንብረቴ የሚለውን ሁሉ የሚያስቀምጠው በእርሷ ቤት ሆነ። ወዶታልና አመናት። እንደወደዳት ስታረጋግጥ ጥያቄዎችን ማቅረብ ጀመረች። ከልቡ የወደዳት ሽፍታ ሴቲቱ የምትጠይቀውን ሁሉ ይሰጣት ቀጠለ። ነገር ግን አንድም ቀን ለአንድ ጊዜም ቢሆን እንደምትወደው ጠይቋት አያውቅም ነበር። እርሷም ‹‹እወድሃለሁ›› ብላው አታውቅም።

ሽፍታው አንድ ቀን አንድ ነገር ከማድረጉ በፊት ‹‹እወድሃለሁ›› እንድትለው ፈለገ። እወድሃለሁ በይኝ አላት። ሴቲቱ እንደገመታት ‹‹እወድሃለሁ›› አላለችውም። አልወድህም አለችው። ‹‹ለምን ? ›› አላት። ‹‹ በድለኸኛል። እንድወድህ ሳታደርግ አግብተኸኛል፤ ያየኸኝ እንዳንተ እንደሰው ሳይሆን እንደምትፈልገው ዕቃ በመሆኑ እኔ ልወድህ አልችልም ›› አለችው። በጥልቅ ፍቅር ውስጥ የነበረው ሽፍታ ከበደሉ በኋላ ማባበል ተቀባይነት እንደሌለው ተገንዝቦ መውደዱ ከልቡ መሆኑን ማሳየት ፈለገ።

‹‹መውደዴ ከልቤ ነው ምን ላድርግልሽ›› አላት። መልሷ ከወደድከኝ ከዛሬ ጀምሮ ፍታኝ አለችው። በማለት ተረቱን የጨረሰው ዘውዴ ሕወሓት በምንም መልኩ ለትግራይ ነጻነት እቆማለሁ፤ ለትግራይ ህዝብ ያለሁት እኔ ነኝ፤ ከትግራይ ህዝብ በላይ ለትግራይ ህዝብ አውቅለታለሁ ቢልም ህዝቡንም ክልሉንም ጠቅሞ አያውቅም። ከመፈጠሩ ጀምሮ ሲጎዳው ኖሯል። አሁን ላይ የትግራይ ህዝብ የሕወሓት ቡድን የሚወደን ከሆነ እንፋታ እያለ ነው። እወድሃለሁ የሚል ቡድን አልወድህም አልፈልግህም ከሚለው አካል ፍቅርን ማግኘት አይችልም። መውደዱን የሚያረጋግጠው ሲፋታው ብቻ ነው ብሎ ዘውዴ ተረቱን በቁም ነገር አስታኮ ሁሉንም አስደመመ።

ገብረየስ ለዘውዴ ‹‹ይህን ማለትህ ትክክል ነህ። አንድ ነገር ሲፈፀም አንዱ በትዕግስት ቢያልፍም ሌላው ሊነሳ ስለሚችል ምንጊዜም ቢሆን ስህተት ላለመስራት ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። ለነገሩ የሕወሓት ስራ ከስህተትም በላይ ሴራ ነው። በተደጋጋሚ የትግራይን ልጅ ለጦርነት ዳርጓል። አንዴ ከደርግ ሌላ ጊዜ ከኤርትራ አሁን ደግሞ ይኸው አንዴ ከአፋር ሌላ ጊዜ ከአማራ ብቻ ከሁሉም ጋር እያናከሰን ነው። ትክክል ብለሃል አንድ ሰው ግዴለሽ ከሆነ ወይም ጥንቃቄ ከሌለው በተለይ ለብልጣ ብልጦች መቀለጃ ከመሆን አያመልጥም። የትግራይ ሕዝብ የሕወሓት መቀለጃ ሆኗል። በሰዎች መካከል መቀራረብ፣ መስማማት፣ መዋደድና መተሳሰብ ሲኖር ሰላም እና ፍቅር ስለሚኖር የበለጠ ተጠቃሚ መሆን ሲቻል። ሕወሓት ግን ጥላቻ ውስጥ እየከተተን በቀጣይም ከማንም ጋር እንዳንኖር እየዳረገን መሆኑ በእርግጥ ያሳዝናል። በትክክልም ማስቆም አለብን ነገር ግን ውሉ የጠፋን እንዴት ብለን የሚለው ነው።›› አለ።

ተሰማ በበኩሉ ለገብረየስ መልስ መስጠት ፈለገ ‹‹አንዳንድ ጊዜ ያልታሰበ የተወሳሰበ ችግር ያጋጥማል፤ የገደለው ባልሽ የሞተው ወንድምሽ ሃዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽ አልወጣ እንደሚባለው አሁን እየሆነ ያለው ይኸው ነው። ነገር ግን መረዳት ያለባችሁ አሁን ሕወሓት የአንድ የብልፅግና ወይም የመንግስት ጠላት ብቻ አይደለም። የትግራይም ጠላት ነው። ከነቃችሁ ጠላቴን የሚያጠቃልኝን እንደወዳጄ እቆጥረዋለሁ ብላችሁ ከመንግስት ጎን ቁሙ። እንደእባብ ዱካ ሆናችሁ የሕወሓትን ሴራ የውሃ ሽታ አድርጉት ይህንን ለማድረግ ከቆረጣችሁ የሁላችንንም ጠላት ሕወሓትን ማጥፋት ይቻላል። ሕወሓት ጠላቴ ነው የጠላቴ ጠላት ደግሞ ወዳጄ ነው። አቦ ለዛሬው ይብቃን እንውጣ።›› ብሎ ከኪሱ ብር አውጥቶ ጠረጴዛ ላይ እያስቀመጠ ከመቀመጫው ተነሳ።

# ኪነ ጥበብ እና ሰላም

ዋሰልኝ አዩስ

ኪነ ጥበብ የሰውን ልጅ አስተሳሰብ ይዘውራል፤ ሲፈልግ ያለማል፤ ሲፈልግ ያጠፋል። ለሰላም ይውላል፤ ለጦርነት ይውላል። በጦርነት ጊዜ አዝማሪ ለምን አስፈለገ? የውስጥ ወኔን ስለሚያነቃቃ!

በአገር ቤት በባህላዊ የሰርግ ስነ ሥርዓት ላይ ለአዝማሪ ሽልማት የሚሰጠው ለምንድነው? ወኔን ስለሚያነቃቃ፤ ‹‹የዳቦ አጣሁ!›› ብሎ ለሚለምን ከአንድ ብር በላይ ሰጥተን አናውቅም፤ መድረክ ላይ ድንቅ አጨፋፈር ወይም አተዋወን ላሳየ ሰው ግን ሃምሳ እና መቶ ብር እንሰጣለን፤ ይህ ለምን ሆነ? ኪነ ጥበብ ስሜትን ስለሚዘውር!

የትኛውም የኪነ ጥበብ ሥራ የገሃዱ ዓለም ነጸብራቅ ነው። ጥያቄው ‹‹የገሃዱ ዓለም ምንድነው?›› የሚለው ነው። የገሃዱ ዓለም ፍቅር ነው፣ ማህበራዊ ጉዳይ ነው፤ ፖለቲካ ነው። ከእነዚህ ጉዳዮች ውስጥ ፖለቲካ ተደጋግሞ ይነሳል፤ ምናልባትም ከአገር ምንነት ጋር በቅርብ የሚቆራኝ ስለሆነ ይሆናል። ምናልባትም በመሪነት ደረጃ ያሉት ብቻ ሳይሆኑ ህዝቡም ፖለቲካ ይወዳል(እርግጥ ነው ፖለቲካና ኤሌክትሪክን በሩቅ የሚለው ብሂልም አለ)። ይሄ በራሱ ግን ፖለቲካ ነው። እንዲያውም የህዝቡም ፖለቲካን መውደድ እንጂ እውነት ፖለቲካ ከሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች እና ከኢኮኖሚ በላይ ለአንዲት አገር ወሳኝ ሆኖ ነው? መልስ ሊሆነን የሚችለው ሁሉም ነገሮች በፖለቲካው ውስጥ ያልፋሉ የሚለው ነው።

ወደ አገራችን ኪነ ጥበብ እንግባ። ስንገባም ኪነ ጥበብን ከፖለቲካና ሰላም ጋር አገናኝተን ነው። ኪነ ጥበብ በአገሪቱ ነባራዊ እሴቶች ላይ ስለሚሰራ ከፖለቲካ ገለልተኛ ነው የሚለው ክርክር ለዚህ ጽሑፍ አያስኬድም፤ ኪነ ጥበብ ከፖለቲካ ውጭ ነው የሚለው እምነትም በጣም የጥቂቶች ብቻ ነው።

ኪነ ጥበብ በፖለቲከኞች አለመግባባት የሚፈጠረውን ግጭት ወደ ሰላም የሚያመጣ መሆን አለበት። ምክንያቱም ከያኒዎች ‹‹ሀብታችን ሕዝብ ነው›› ሲሉ እንሰማለን። ስለዚህ ለሀብታቸው ሰላምና ደህንነት ሊሰሩ ይገባል።

> ኪነ ጥበብ የጋራ ማንነትን ይፈጥራል። ማህበራዊ ማንነት ‹‹ጄኔቲካዊ›› ሳይሆን ማህበራዊ ስሪት ነው። ባህልና ኪነ ጥበብ ነው የሚቀርጸው። አገር የሚሰራው በትርክት ነው። ኃያላን የሚባሉትን አገራት የምናውቃቸው በትርክት ነው። ይህን ደግሞ የሚያደርገው ኪነ ጥበብ ነው

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ወደ ሥልጣን እንደመጡ ከኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ጋር በጽሕፈት ቤታቸው ተወያይተዋል። በዚያው ዓመት ውስጥ የሰላም ሚኒስቴር የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን ጠርቶ ውይይት አካሂዶ ነበር። በዝግጅቱ ላይ ታድሜ ስለነበር እስኪ በዛሬው የሰላም ቀን የማስታውሳቸውን ላንሳ።

የሰላም ሚኒስቴር በወቅቱ በነበሩት ሚኒስትር ሙፈሪያት ካሚል አማካኝነት የሰላምን ነገር ሲያሳብ ከኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ጋር መወያየት አለብኝ አለ። የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች የህዝብን ስሜት እንደሚዘውሩ አመነ። አምኖም መድረክ አዘጋጀ። የሰላም ሚኒስትሯ ወይዘሮ ሙፈሪያት ከሚል መድረኩ ላይ ተገኙ፤ በራሳቸው በሚኒስትሯ አወያይነት ሀሳቦች ተንሸራሸሩ። ከያኒ ከፖለቲከኛ በላይ ሃይል እንዳለው፣ ፖለቲከኛ በህዝብና በህዝብ መካከል ያጠረውን አጥር ከያኒ ማፈራረስ እንደሚችል ተናገሩ። ‹‹ከያኒ ድንበር የለውም›› አሉ የሰላም ሚኒስትሯ።

ምሳሌም አነሱ። የኦሮሚያና የሶማሌ ፖለቲከኛ ድንበር ቢያበጅ፣ ቢኳረፍ፤ የኦሮሚያና የሶማሌ አርቲስት ግን ይህን ድንበር ነው ማፍረስ ያለበት። የኦሮሚያና የሶማሌ ከያኒ ከተኳረፈ ያኔ ነው ኪነ ጥበብ አድርባይ ሆነች የሚባለው።

በወቅቱ የውይይት መነሻ ጽሑፍ ያቀረቡት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ተስፋዬ እሸቱ፤ ‹‹ኪነ ጥበብ ለሰላም ይጠቅማል የሚለው ቃል አገላለጽ የኪነጥበብና የሰላምን ግንኙነት የሚያሳንስ ነው›› ይላሉ። መምህር ተስፋዬ ማለት የፈለጉት፤ ኪነ ጥበብና ሰላም ፍጹማዊ አንድ ሆነው ‹‹ኪነ ጥበብ ለሰላም ይጠቅማል›› መባሉ ግን ጥብቅ ቁርኝት ያልነበራቸው ያስመስለዋል ነው። መንግስትም፣ መገናኛ ብዙኃንም ይህንን ነው የሚደጋግሙ፤ ‹‹ኪነ ጥበብ ለሰላም ፋይዳ አለው›› ቢሉም ማንም የተረዳው ግን የለም። በጣም ግልጽ የሆነውን ነገር ልክ በሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር እንደ አዲስ የተገኘ ይመስል ‹‹ኪነ ጥበብ ለሰላም ይጠቅማል›› ማለት ምን ያህል ትኩረት እንዳልተሰጠውም ያሳያል።

መምህሩ አዝማሪዎችን ምሳሌ ያነሳሉ። የአዝማሪዎች ጨዋታ የማህበረሰቡ ነጸብራቅ ነው። በማህበረሰቡ ውስጥ አዝማሪ ብዙ ነገር ነው። ኢኮኖሚ ነው፣ ፖለቲካ ነው፣ ፍቅር ነው፣ ማህበራዊ ግንኙነት ነው። በማህበረሰቡ ውስጥ ይሄ ሆኖ ግን አሁን አሁን ለአዝማሪ የሚሰጠውን ዋጋ እናውቃለን፤ መሰደቢያ ሁሉ ይመስለናል። ይሄ የመንግስትም የመገናኛ ብዙኃኑም ችግር ነው፤ አልሰሩበትም። ከጥንት ጀምሮ የነበረው ታሪካዊ ዳራው አልታወቀለትም። ያ ታውቆ ቢሆን ኖሮ ኪነ ጥበብና ሰላም ድንበር የለሽ ህዝባዊ ትስስር መሆናቸው ግልጽ ይሆን ነበር።

በኪነ ጥበብ ላይ ፈላስፎች ክርክር ነበራቸው። ፕሌቶ የተባለው ፈላስፋ ኪነ ጥበብ አፍራሽ ነው ብሎ ያምን ነበር፤ ምክንያቱ ደግሞ ዓለምን አይወክልም ነው፤ ከእውነታው ይርቃል፣ ይጋነናል ነው።

ሌላው ፈላስፋ አርስቶትል ደግሞ የፕሌቶን ሀሳብ ውድቅ ያደርጋል። ኪነ ጥበብ የስሜትና የእውነታ ውህደት እንደሆነ ያምናል። ይሄ ማለት ስሜታችን የሚጦዘው የሆነ ውስጣችን ያለውን ነገር(የነበረውን እውነታ) ሲነካው ነው ማለት ነው። ለምሳሌ ለቅሶ እንደ መዳኛ ይቆጠራል፤ ‹‹አልቅሶ ይውጣለት›› ይባላል። ለቅሶ የስሜትና የእውነታ ውህደት ነው። ይሄ እፎይታ ነው። ስለዚህ ያ ስሜት እፎይታ አስገኘ ማለት ነው። ሌላው አርስቶትል የሚለው ነገር ኪነ ጥበብ ደስታን እንደሚፈጥር ነው። ደስታ ደግሞ ለሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ጤንነት ነው። እንዲያውም ኪነ ጥበብ የሳይንሳዊ ግኝቶች መነሻ እንደሆነም ይታመናል።

ኪነ ጥበብ መንገድ አይሰራም፤ ሕንጻ አይሰራም፤ ይህን የሚሰሩትን ሰዎች ግን ይሰራል። ለዚህም ነው እነዚህ ሰዎች ‹‹ጥበበኞች›› የሚባሉት። ይሄ ሲሆን ኪነ ጥበብ የጋራ መግባቢያ ሆነ ማለት ነው። የአንድ አገር ሰዎች የጋራ መግባቢያ ሲኖራቸው ነው እርስ በእርስ የሚተዋወቁትና የሚግባቡት። ለዚህ ደግሞ ኪነ ጥበብ ጥሩ ማሳያ ነው። በጋራ ያግባባል፤ በጋራ ያኖራል፤ ያስተዋውቃል። ፖለቲካ ድንበር አለው፤ ሃይማኖት ድንበር አለው፤ ኪነ ጥበብ ግን ድንበር የለውም ይላሉ ባለሙያዎቹ።

‹‹ኪነ ጥበብ ማንነትን ይገነባል›› ይላል የመምህር ተስፋዬ ጽሑፍ። ኪነ ጥበብ የጋራ ማንነትን ይፈጥራል። ማህበራዊ ማንነት ‹‹ጄኔቲካዊ›› ሳይሆን ማህበራዊ ስሪት ነው። ባህልና ኪነ ጥበብ ነው የሚቀርጸው። አገር የሚሰራው በትርክት ነው። ኃያላን የሚባሉትን አገራት የምናውቃቸው በትርክት ነው። ይህን ደግሞ የሚያደርገው ኪነ ጥበብ ነው።

በአገራችን ‹‹እንዴት እየተሰራበት ነው?›› ለሚለው፤ መምህር ተስፋዬ መንግስትንና የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን ተጠያቂ ያደርጋሉ። ቀዳሚውም መንግስት ነው። ይሄ ማለት ወርዶ ድራማ ይስራ ማለት አይደለም፤ ከመንግስት የሚጠበቀው ኪነ ጥበብን ተቋማዊ ማድረግ ነው። በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የኪነ ጥበብ ትምህርት ያስፈልጋል፤ ይህ የሚሆነው አገሩን በሙሉ አርቲስት ለማድረግ አይደለም፤ ይልቁንም ሰው እንዲሆኑ ነው። ኪነ ጥበብ ሰብዓዊነት ነውና! ሐኪሙም፣ የህግ ባለሙያውም፣ መሃንዲሱም ጥበበኛ መሆን አለባቸውና! የመንግስት ቀዳሚው ሥራው ይሄ ነው።

መንግስት በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ አልሰራም፤ ተማሪዎች አገራቸውን አያውቁም፤ ‹‹አፋር ውስጥ ያለ የሰባተኛ ክፍል ተማሪ የአማራ ወንድሙን አያውቅም፤ ትግራይ ውስጥ ያለው የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ሶማሌን አያውቅም፤ ታዲያ ላይጣሉ ነው እንዴ!›› ይላሉ መምህር ተስፋዬ። ይህ ሲሆን ነው ኪነ ጥበብ ሰላም ላይ ሚሰራው።

ወላጆች ላይም ችግር አለ ነው የሚሉት መምህሩ። ልጆቹ ከሰብዓዊነት ውጭ ሆነው እያደጉ ነው። ከሰዋዊ ነገሮች ይልቅ ቁሳዊ ነገር ነው የሚዘጋጅላቸው። አሻንጉሊት ነው የሚገዛላቸው፤ የውጭ ፊልምና ‹‹ጌም›› ነው የሚጫንላቸው። አካባቢያቸውን እንዲያውቁ አልተደረገም። ባህላቸውንና ታሪካቸውን ቢያውቁ ሰብዓዊነት ይገነባቸው ነበር። አርቲስቶች እዚህ ላይ ነበር መሥራት ያለባቸው።

ከኪነ ጥበብ ባለሙያው የሚጠበቀውንም መምህር ተስፋዬ በወቅቱ ተናግረው ነበር። የኪነ ጥበብ ሰው መሪ ነው መሆን ያለበት። መንግስት ልማት ሲል አብሮ ልማት የሚል ከሆነ፣ መንግስት ውሃ ማቆር ሲል አብሮ ውሃ ማቆር የሚል ከሆነ ኪነ ጥበብ ዋጋ አይኖረውም። ኪያኒ ማነሳሳት ነው ያለበት። ቢቢሲ የሰራው አንድ ዘጋቢ ፊልም ላይ በመሬት የሚሄድና በሰማይ የሚበር አውሮፕላን ‹‹እንዴት ሰራኸው?›› ተብሎ ‹‹ፊልም ላይ አይቼ›› ነው ያለው። ከያኒ እንዲህ ነው፤ ነገሮችን ፈጣሪ! ከመንደር ያለፈ ሥራ መሥራት አለበት። ዝም ብሎ ‹‹ተጋቡ ተፋቱ›› የሚል ሥራ ብቻ ነው እየተሰራ ያለው። እንኳን በምናብ ፈጥሮ ማስተማር መሬት ላይ ያለው እውነታ እንኳን አልተሰራበትም። ወሎ ውስጥ ለጥምቀት በዓል ሙስሊም ከበሮ እየመታ ይከበራል፤ ይሄን ማንም አያውቀውም፤ ከያኒ ግን ያልታየውን ማሳየት ነበር ሥራው።

ኪነ ጥበብ ከመንግስት ኃይል በላይ ነው። ግጭት ቢነሳ መንግስት ግጭቱን ማስቆም ነው የሚችለው፤ ኪነ ጥበብ ግን እንዳይነሳ ማድረግ ይችላል። መንግስት በኃይል ነው የሚያስቆመው፤ ኪነ ጥበብ ግን በአስተሳሰብ ለውጥ ነው የሚያስቆመው፤ በፍቅር ነው የሚያስቆመው። የተጋጩት ወገኖች ኃይል ፈርተው ሳይሆን ፍቅር አሸንፏቸው ነው የሚያቆሙት።

‹‹አርቲስት ልቡ የሸበተ ነው›› ይባላል። ሽማግሌ ነው ለማለት ነው፤ አስታራቂ ነው ማለት ነው። ጸጉራቸው የሸበተ ሽማግሌዎች ለሰላም ያላቸውን አስተዋጽኦ እናውቃለን። አርቲስት ደግሞ ዕድሜው ወጣት ቢሆን እንኳን ልቡ እንደ ሽማግሌ መሆን አለበት። ከዚያና ከዚህ ያለውን የሚያግባባ መሆን አለበት። አንድ የኪነ ጥበብ ሥራ ከብዙ መድረኮችና ስብሰባዎች በላይ ያስተምራል።

የወቅቱ የሰላም ሚኒስትር ሙፍሪያት ካሚል የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን በሰበሰቡበት መድረክ እንዲህ ብለው ነበር። ‹‹እኛ ፖለቲከኞች ልንቀያየር እንችላለን፤ እናንተ ግን የማትቀያየሩ መሆን አለባችሁ!››

አዎ! ሥርዓት ይመጣል ሥርዓት ይሄዳል፤ ባለሥልጣን ይቀየራል። የጥበብ ባለሙያ ግን በሕዝቡ ውስጥ ያለውን እውነታ ይዞ መቀጠል አለበት። ፖለቲከኛ በየመንደሩ ያጠረውን አጥር ማፍረስ የሚችለው ኪነ ጥበብ ነው። ጥበብ የጋራ ቋንቋ ያለው ነው።

ሙዚቃን መውሰድ እንችላለን፤ በጎጃምኛ ሙዚቃ የሚንቀጠቀጠው ኦሮሞው ጉራጌው ትግሬው ነው፤ በትግርኛ ሙዚቃ የሚሽከረከረው አማራው፣ ኦሮሞው ሶማሌው ነው። ኪነ ጥበብ አንድ ያደርጋል። የጋራ ቋንቋ ነው ማለት ይህ ነው።

የኪነ ጥበብ ሥራ ከፖለቲከኛ በላይ ነው፤ ዘመን ተሻጋሪ ጉልበት አለው። ዛሬ ‹‹ባህላችን፣ ታሪካችን›› እያልን እንድንኮራ ያረጉን ዘመን አይሽሬ የኪነ ጥበብ ሥራዎች ናቸው።

‹‹አርቲስት ድንበር የለውም›› ሲባል በአገሪቱ ውስጥ ያለ ባህልና ታሪክ ሁሉ የራሴ ነው ብሎ መሥራት አለበት ማለት ነው። ብዙሃነት ውበት መሆኑን ማወቅ አለበት። ብዝሃነት ተፈጥሮ ነው። ፈጣሪ ሁሉንም አንድ አይነት ማድረግ ቢፈልግ ኖሮ ማድረግ አቅቶት አልነበረም፤ ሁሉንም አንድ አይነት ቀለም አድርጎ መፍጠር ይችል ነበር። ይህን የፈጣሪ ውበት ማስጠበቅ የሚችለው ኪነ ጥበብ ነው፤ ከያኒ ራሱ ፈጣሪ ሆነ ማለት ነው።

ኪነ ጥበብ ይህን ሁሉ ጉልበት እያለው ዳሩ ግን ያየነው እና የሰማነው አይነት ጥፋቶች ደርሰዋል። ሰዎች በአገራቸው ‹‹አገራችሁ አይደለም›› ተብለዋል፤ በአገራቸው ባዕድ ሆነዋል፤ በአገራቸው መፈናቀል ደርሶባቸዋል።

‹‹ቅኝ ያልተገዛች አገር ነፃ አገር ›› የሚለው ስሙ ብቻ ተርፏቸዋል፤ በአገራቸው ነፃነትን ሲያጡ ‹‹ቅኝ አለመገዛት ማለት ምን ማለት ይሆን?›› ያሰኛቸዋል። ‹‹ቅኝ ገዥዎችስ ከዚህ በላይ ምን ያደርጉናል?›› ብለው ነበር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በመስቀል አደባባይ ለድጋፍ ሰልፍ ባደረጉት ንግግር። ‹‹ድንበር የለውም›› የተባለው አርቲስት ግን ራሱም ድንበር ፈጥሮ ሲከፋፈል ታይቷል።

የአንዲት አገር ዋነኛ መለያ ሰላም ነው። ሁሉም የሚመጣው ሰላም ሲሆን ነው። ሰላም በሌለበት ስለምንም ነገር ማውራት አይቻልም፤ ስለዚህ መንግሥትም ሆነ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ቀኑን ከማክበር ባለፈ ሰላም ላይ ሕዝባዊ ሥራ ሊሰሩ ይገባል!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ዋናው ነገር ሰላም

**ሰላማዊት ውቤ**

ሰላም በሦስት ፊደል ብቻ ይገለጽ እንጂ ሁሉም ነገር ነው። የተለያዩ የአማርኛ ቃላት መፍቻ መዝገቦች ሰላምን ጸጥታ፣ ዕረፍት፣ እርጋታ፣ እርካታ እንዲሁም የእርስ በእርስ ስምምነት በአንድነት አብሮ መኖር መቻልና የዕረፍት ስሜት ሲሉ ትርጉም ይሰጡታል። በአጠቃላይ ሰላም ከሰው ልጆች መሰረታዊ ፍላጎቶች አንዱና ዋነኛው ነው።

ሆኖም ይህ መሰረታዊ ፍላጎት በተለያዩ አላላት ሲደፈርስ ይታያል። ከሰላም ይልቅ ከጦርነት በሚያተርፉ አካላት አማካኝነት ግጭት፤ ሁከትና ብጥብጥ በአለማችን ላይ ነግሶ ይታያል። የእኛዋም ኢትዮጵያ የዚሁ ሰለባ ከሆነች ሰነባበተች። በጥባጭ ካለ መች ደህና ይጠጣል እንደሚባል ኢትዮጵያውያን በአሸባሪው ሕወሓትና በግብረ አበሮቹ ምክንያት ሰላማቸውን ካጡ ሰነባብተዋል።

ለዚህ አባባል ደግሞ አሁን ለሦስተኛ ጊዜ በአገራችን ላይ በሕወሓት ቡድን የተከፈተው ጦርነት በራሱ አንዱና ትልቁ መገለጫ ይሆናል። የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ሰላምን በመሻት እየተወጉም ጭምር ለሰላም በርካታ መንገድ ተጉዘዋል። ከታዋቂ ሰዎች ጀምሮ እስከ ኃይማኖት አባቶች ጭምር የሕወሓት አሸባሪ ቡድን ከጦርነት በሃሪው እንዲወጣና ሰላም እንዲያሰፍን በብዙ ቢለፉም ቡድኑ ጦርነት አምላኪ በመሆኑ የተደረጉት ጥረቶች ሁሉ መክነው ቀርተዋል።

እንደ መንግስት በአገር ደረጃ የሰላም ሚኒስቴርን ከማቋቋም ጀምሮ ግጭቶችን በሰላም ለመፍታት ጽኑ አቋም ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ይሄንን ጽኑ የመንግስት አቋም አዲስ አበባ በተካሄደው በ35ኛው የአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ጉባኤ መክፈቻ ላይ"በአገራችን ሰላም ለማስፈን የማንፈነቅለው ድንጋይ አይኖርም" ሲሉ የተናገሩትን ማስታወሱም ማሳያ ይሆናል። በሌሎች አገራዊ መድረኮች ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰላም ውይይቱን የሚያካሂድ ኮሚቴም በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን የሚመራ ኮሚቴ በብልጽግና ሥራ አስፈፃሚ መሰየሙን ሲናገሩ ማድመጣችንም ቢሆን የመንግስትን ሰላም ፈላጊነት ያመላክታል።

በመንግስት የሚመራውና ሰላምን በባለቤትነት ይዞ እንደ አገር የተቋቋመው የሰላም ሚኒስቴርም በየአካባቢው የሚነሱ ግጭቶችን ጨምሮ በሕ›ወ.ሓ.ት የተከፈተውን ጦርነት ጭምር በሰላም ለመፍታት ዘወትር ጥረት እያደረገ ይገኛል። የኢትዮጵያ መንግስት በጦርነትም ውስጥ ሆኖ የሰላም አማራጮችን የሚያስቀድም መንግስት ነው።

ይህንኑ ታሳቢ በማድረግም መንግስት የዛሬዋን ዕለት ጭምር ለሰላም በማዋል ጳጉሜን ሦስት የሰላም ቀን ብሎ እስከመሰየም ደርሷል። ኢትዮጵያውያን በየትኛውም ዕለት ለሰላም ይተጋሉ፤ በዛሬዋ ቀን ደግሞ ድምጻቸውን በአንድነት ያሰማሉ። ሰላሟ የተረጋገጠ፤ ዜጓቿ በሰላም ወጥተው የሚገቡባት አገር እንድትኖራቸው ይጸልያሉ። በርካታ ወጣቶች ሴቶች በግልና በጋራ ጦርነትን፤ ሁከትንና ብጥብጥን አንሻም በማለት በጋራ ይቆማሉ፤ በአሸባሪ ቡድኑ አማካኝነት በተለያዩ አካባቢዎች የሚታዩ የጦርነት ድርጊቶችን ያወግዛሉ።

ብዙዎችም ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለዓለም ያሰማሉ። ሴቶች ደግሞ ለዚህ ግንባር ቀደም ሚናውን ወስደዋል። ከነዚህ አንዷ በኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን የተመዘገበችው አገር በቀል ድርጅት ትምራን ናት። ትምራን ሴቶች በፖለቲካዊ እና አመራርነት ዘርፎች በጉልህ የሚሳተፉባት ኢትዮጵያን ለማየት እየሰራች የምትገኝ ማህበር ናት።

ወይዘሮ እየሩስዓለም ሰለሞን የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ናቸው።

ትምራን ከተመሰረተች ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ በሰላም ዙርያ ስትሰራ መቆየቷንም አውስተዋል። እኛ ሴቶች ሰላምን ነው የምንሻው። ጦርነትን አጥብቀን እንቃወመዋለን። ኢትዮጵያ ልጆቻችን በሰላም እንዲያድጉ፤ እንዲማሩ፤ እኛም በሰላም ሰርተን የምንኖርባት እንድትሆን እንፈልጋለን ይላሉ። በየዓመቱ የሰላም ቀን ተብሎ የተሰየመውንና ዛሬ




እየተከበረ ያለውን ጷጉሜን ሦስትን በዚሁ መልኩ አክብሮ ለመዋልና ለማሰብ የሚያስችልና ከሴቶች አደባባይ ተነስቶ እስከ መስቀል አደባባይ የሚዘልቅ ታላቅ የእግር ጉዞ መዘጋጀቱንም ይናገራሉ።

ትምራን ጦርነትንና ሁከትን የሚቀሰቅሱ ማናቸውም ኃይሎች ሆኑ ሕ.ወ.ሓ.ት ወደ ሰላም ፊታቸውን እንዲመልሱ ሳታሰልስ ትሰራለች ያሉት ሥራ አስኪያጇ ከመንግስትና ከየትኛውም ሰላም ፈላጊ ጋር የምትሰራ መሆኗንም አውስተዋል። ሕ.ወ.ሓ.ትም ሆነ የትኛውም ቡድን ለሰላም እንዲቆምና ለሰላም መቆም ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም ብለዋል። በሰሜን ኢትዮጵያ የሚካሄደው ጦርነት ሰላማዊ መፍትሔ እንዲያገኝ መንግስት ሳያሰልስ ሲሰራ መቆየቱንና እየሰራ መሆኑን የጠቆሙት ወይዘሮ እየሩስ አለም ከዚህ ጦርነት ማንም እንደማያተርፍና ከሁለቱም ጎን የሚያለማ ወጣት እየረገፈና የአገሪቱም ሀብት እየወደመ መሆኑን ተረድቶ ወደ ሰላም መፍትሄ መምጣት አስፈላጊ እንደሆነም አስምረውበታል።

ስራ አስኪያጇ እንደሚሉት አሁን ላይ "ሴቷ ሰላምን ትምራ" በሚል መሪ ቃል ሰላምን በአገራችን የማስፈን ምኞትን ያነገበ የሴቶች የእግር ጉዞን ከኢትዮጵያ ሴት ማህበራት ቅንጅት ጋር በጋራ በመተባበር ያዘጋጀችው ሰላምን ለማስፈን ነው፡፡ ሰላም ማጣት ከማንም በላይ ዋጋ ከሚያስከፍላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ሴቶችና ህፃናት ዋነኞቹ ናቸው ። ምንም እንኳን ሰላም የሁሉም ነገር መሰረት እና ለሁሉም እኩል አስፈላጊ ቢሆንም፤ ሰላም በማጣት ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ለጥቃት ተጋላጭ የሚሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች ሴቶች እና ህፃናት መሆናቸው በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተፈጠረው ጦርነት ዋነኛ ማሳያ ነው።

ይህንንም ታሳቢ በማድረግ እና የጉዳዩን ወቅታዊነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሴቶች እራሳቸው ሰላምን እንዲሰብኩ፣ እንዲገነቡ እና የሰላም መሪዎች እንዲሆኑ እንዲሁም በአዲሱ ዓመት በኢትዮጵያ ዳግም እያንሰራራ ያለው የግጭት እና የጦርነት ሃሳብ ከምንጩ እንዲደርቅ በመመኘት "ሴቷ ሰላምን ትምራ" የሚል መፈክር በማንገብ ጳግሜ 03/2014 ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት ጀምሮ ከሴቶች አደባባይ በመነሳት መዳረሻውን መስቀል አደባባይ ያደረገ የሰላም የእግር ጉዞ ከ ኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (NEWA) ጋር በመተባበር ማካሄድም አስፈልጓል፡፡

በእግር ጉዞው በርካታ ሴቶች፣ የሴት አደረጃጀቶች፣ የሴት መብት ተሟጋቾች እና ማህበራዊ አንቂዎች ይሳተፉበታል። እንዲሁም መርሀ ግብሩ ለዘለቄታዊ ሰላም ሴቶች ያሉዋቸውን ሀሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት በማቅረብ፤ በሌሎች አካባቢዎች የተነሱ ሀሳቦች የተሻለ የማስፈፀሚያ ዘዴ በማመላከት እና የዓመቱ የሰላም እንቅስቃሴ በሴቶች ጉልህ ተሳትፎ እንዲመራ አቅጣጫ በመስጠት ይጠናቀቃል ብለዋል። በጉዞው ላይ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲሁም የሰላም ሚኒስትር የሴቶች ተሳትፎ እንዲረጋገጥ መልዕክት ያስተላልፋሉ።

በአጠቃላይ የሰላም ቀንን በመጠቀም ሕወሓትና መሰሎቹ የአገራችንን ሰላም ከማወክ እንዲቆጠቡ እና ከጦርነት ውድመት እንጂ ሌላ ትርፍ እንደማይገኝ መልዕክት ይተላለፍበታል። የጦርነት ቅድሚያ ተጎጂ የሆኑት ሴቶችም በአገራችን ሁለንተናዊ ሰላም እንዲሰፍን የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ አቋም የሚወስዱበት ይሆናል ሲሉ መልዕክታቸውን ቋጭተዋል።

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ ምዕራባውያን ቃል የገቡትን "የሎጂስቲክስ ማዕቀብ" አላነሱም ስትል ወቀሰች

ሩሲያ እህል እና ማዳበሪያ ለዓለም ገበያ እንድታቀርብ ምዕራባውያኑ የገቡትን ቃል አላከበሩም ሲሉ የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌይ ላቭሮቭ ወቀሱ።

ምዕራባውያን ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ላይ የተጋረጠውን የምግብ እህል አቅርቦት ቀውስ ለማቃለል በተመድ እና ቱርክ አደራዳሪነት የዩክሬን የእህል ምርት በጥቁር ባሕር በኩል ለዓለም አቀፉ ገበያ እንዲቀርብ ስምምነት ላይ ደርሰው ነበር።

ከዚህ ጋር ተያይዞም ሩሲያ እህል እና ማዳበሪያ ለዓለም አቀፉ ገበያ ያለ ገደብ እንድታደርስ ስምምነት ቢደርሱም ይህን አላከበሩም ሲሉ ነው ሚኒስትሩ የወቀሱት።

በቱርክ ኢስታንቡል የተደረሰው ሥምምነት የጥቁር ባሕር ወደብ እንዲከፈት እና ከዩክሬን በወጪ ንግድ የሚላከው የምግብ እህል አቅርቦት እንዲቀጥል ነበር።

ምዕራባውያኑ ግን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሃፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ በኩል የገቡትን ቃል አላካበሩም ሲሉ የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቤቱታ አቅርበዋል።

የሩሲያ እህል እና ማዳበሪያ ወደ ዓለም ገበያ እንዳይገባ የሚከለክለውን የ"ሎጂስቲክስ ማዕቀብ" አላነሱምም ነው ያሉት ሰርጌይ ላቭሮቭ።

ሚኒስትሩ ከታይላንድ አቻቸው ዶን ፕራሙድዊናይ ጋር በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ተመድ ኢስታንቡል ላይ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ግዴታውን እንዲወጣ መጠየቃቸውን አር ቲ መዘገቡን ኤፍቢሲ ዘግቧል።

## አዲሷ የዩናይትድ ኪንግደም ጠቅላይ ሚኒስትር ወዳጆቻቸውን በቁልፍ የካቢኔ ቦታዎች ላይ ሾሙ



ቦሪስ ጆንሰንን ተከተው የዩናይትድ ኪንግደም ጠቅላይ ሚኒስትርነት መንበሩን የተረከቡት ሊዝ ትረስ ባደረጉት ከፍተኛ የካቢኔ ሹመት ለቅርብ አጋሮቻቸው ቁልፍ ቦታዎችን ሰጡ። ክዋሲ ክዋርቴንግ ቻንስለር ሆነው ሲሾሙ፣ ጀምስ ክሌቨርሊ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነዋል። ሱዌላ ብሬቨርማን ደግሞ ፕሪቲ ፓቴልን ተከተው የአገር ውስጥ ሚኒስትርነቱን ቦታ ተረክበዋል።

ከትረስ የቅርብ ጓደኞች አንዷ የሆኑት ቴሬዝ ኮፊ የጤና ሚኒስትር እና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሰይመዋል። አዲሱ ካቢኔያቸው ትረስ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ሥልጣኑን ከተረከቡ በኋላ የመጀመሪያቸው ከሚሆነው የጥያቄና መልስ ጊዜያቸው በፊት ይሰበሰባል ተብሏል።

ካቢኔው በውድድሩ የተሸነፉትን ተቀናቃኛቸውን ሪሺ ሱናክን ከደገፉት መካከል አንዳቸውም እንዲቀጥሉ አልተደረገም። ዶሚኒክ ራብ፣ ግራንት ሻፕስ፣ ጆርጅ ኤስቲስ እና ስቲቭ ባርክሌይ ወደ ቀድሞ ቦታቸው ተመልሰዋል።

የትረስ ቃል አቀባይ ለውጦቹ የወግ አጥባቂውን ፓርቲ "አንድ እንደሚያደርገው" ተናግረዋል። ለአምስት የተቀናቃኛቸው አመራሮችም ሹመት ሰጥተዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ ከአራቱ ከፍተኛ "የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የኃላፊነት ቦታዎች" ከሚባሉት የጠቅላይ ሚኒስትር፣ የቻንስለር፣ የአገር ውስጥ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ቦታዎች አንዳቸውም በነጮች ወንዶች አልተያዙም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አዲሷ ጠቅላይ ሚኒስትር ከአገር መሪ ጋር የመጀመሪያ ስልክ ልውውጣቸውን ከዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮሎዲሚር ዜሌንስኪ ጋር አድርገዋል። በዚህም አገራቸው ለዩክሬን ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እንደምትሰጥ ቃል ገብተዋል። ትረስ ዩክሬንን እንዲጎበኙ የቀረበላቸውን ግብዣም በመቀበል ደስተኛ መሆናቸው ተገልጿል።

ኋላም የአሜሪካውን ፕሬዚዳንት ጆ ባይደንን አነጋግረዋል። ዩናይትድ ኪንግደም ከአውሮፓ ኅብረት ጋር በሰሜን አየርላንድ የድኅረ-ብሬግዚት የንግድ ሕጎች ላይ ከስምምነት መድረሳቸው ስላለው አስፈላጊነት ተወያይተዋል።

ባለፉት ዓመታት የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው ሲያገለግሉ የቆዩት ሊዝ ትረስ፤ የወግ አጥባቂ መሪ ለመሆን ከቀድሞ የገንዘብ ሚኒስትር ሪሺ ሱናክ ብርቱ ፉክክር ገጥሟቸው ነበር። ይሁን እንጂ የኋላ ኋላ ሊዝ ትረስ በሰፊ የድምጽ ብልጫ ሪሺ ሱናክን በመብለጥ የወግ አጥባቂ ፓርቲ መሪ እንዲሆኑ በፓርቲው አባላት ተመርጠዋል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

ሐሙስ
አዲስ ዘመን
# ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ስፖርት እና ሰላም

**ብርሃን ፈይሳ**

የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው፤ ስፖርትና ሰላም። ስፖርት ያለ ሰላም ሊከወን አይችልም፤ ሰላምም በስፖርት አውድ ይሰበካል። ከማዝናናት፣ አካላዊና አእምሯዊ ጤንነትን ከመጠበቅ ባለፈ ከተፈጥሮ እና ከሰላም ጋር ባለው ጥብቅ ቁርኝት ምክንያት የተለያዩ መልእክቶችን ለማስተላለፍ ጭምር እጅግ ተመራጭ ዘርፍ ነው። ለዚህም ነው ከአሸናፊነት ፉክክሩ ተመጣጣኝ የሆነ ዋንጫ (ሽልማት) ለስፖርታዊ ጨዋነት የሚበረከተው። ይኸውም ተደጋጋሚ ጥፋት ላላደረሰ፣ ተፎካካሪውን በወዳጅነት ስሜት ለሚያስተናግድ እንዲሁም ሰላማዊ ስፖርትን ለሚተገብር ስፖርተኛ ወይም ቡድን እውቅና የሚሰጥ ነው።

ስፖርት ዓለምን የመለወጥ ኃይል አለው፤ ማህበረሰባዊነትን በማጠናከር እና አብሮነትን በማጎልበት ሰላምን ለማስፈን ይተጋል። ለዚህም ነው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እአአ በ2013 ባካሄደው ጠቅላላ ጉባኤው፤ ዓለም አቀፍ የስፖርት ቀን ለሰላም ግንባታ በሚል እንዲከበር የወሰነው። ዘመናዊው ኦሊምፒክ ለመጀመሪያ ጊዜ እአአ በ1896 በሚያዝያ ወር መጀመሩን ተንተርሶም የስፖርት ለሰላም ግንባታ ዕለት በመላው ዓለም ታስቦ ይውላል። ይህም ብቻም ሳይሆን ተቋሙ ሰላምን ለማስፈንና ለመስበክ ከሚጠቀማቸው መሳሪያዎች መካከል አንዱ ስፖርት ነው። በመገባደድ ላይ ባለው ዓመትም ስፖርት በአካባቢያዊ የአየር ለውጥ ላይ ያለውን በጎ ሚና በማመላከት ተከብሯል።

ዓለም አቀፉ የኦሊምፒክ ኮሚቴ ከመርሆዎቹ ሁሉ አንኳር የሆነው ሃሳቡ ሰላም ሲሆን፤ ሰላምን ባላከበሩና በሰው ልጆች ሕይወት ላይ ያነጣጠሩና አደገኛ ትኩሳቶች ያሉባቸውን አገራት እስከማገድና ከአባልነትም እስከማሰናበት ይደርሳል። ከዚህ ባለፈ ኮሚቴው በተለያዩ ሰው ሰራሽ ምክንያቶች አገራቸውን ጥለው ለስደት የተዳረጉ ሰዎችን በራሱ ባንዲራ በመወከል በታላቁ የውድድር መድረክ ላይ አገራቸውን እንደወከሉት ሌሎች ስፖርተኞች ሁሉ እንዲወዳደሩ በማድረግም አስመስጋኝ ተግባርን ይከውናል።

የዓለም ቋንቋ የሚል ስያሜ የተሰጠው እግር ኳስም ከትኩረት አቅጣጫዎቹ መካከል አንዱ ሰላማዊ የውድድር መድረክ ነው። የእግር ኳስ ጨዋታ ከመጀመሩ አስቀድሞ ተጋጣሚዎቹ ቡድኖች እርስ በእርሳቸው የሚያደርጉት ሰላምታ እንዲሁም አስቀድሞ ሰላማዊነትን የሚያንጸባርቁ ማስታወቂያዎችን ይዞ መገኘትም የስፖርቱን ዓላማ በግልጽ የሚያመላክት ነው። ኢትዮጵያን ጨምሮ በተለያዩ አገራት በሚደረጉ የእግር ኳስ ውድድሮች የጸባይ ዋንጫን ማበርከትም የተለመደ ነው። ስፖርቱን በበላይነት የሚመራው ፊፋም ሰላማዊነትን በወርቃማ ደንቦቹ ላይ በግልጽ አመላክቷል።

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተቀመጠውን አቅጣጫ እአአ ከ2016 ጀምሮ በመተግበር እንዲሁም ብሄራዊ ፌዴሬሽኖችን፣ ክለቦችንና ተጫዋቾችንም በማስተባበር ይታወቃል። በቀድሞ የእግር ኳስ ተጫዋቾች የተመሰረተና ለትርፍ ያልተቋቋመው እግር ኳስ ለሰላም የሚል ድርጅትም ከፊፋ ጋር በጋራ ይሰራል። ይህ ተቋም እግር ኳስ ለዲፕሎማሲ መሳሪያ እንዲሁም መግባቢያ እንዲሆንም ይሰራል። የሰላም ዋንጫ የሚል ስያሜ የያዘው ሌላኛው ተቋምም በየሁለት ዓመት የወዳጅነት ጨዋታን መሰረት ያደረገ የእግር ኳስ ውድድርም እአአ እስከ 2012 ሲደረግ ቆይቷል።

በአንጻራዊነት ሰላማዊና ከንክኪ የጸዳ እንደሆነ የሚነገርለት የአትሌቲክስ ስፖርትም መተሳሰብና አንድነትን ከአሸናፊነትም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። በውድድሮች ላይ ከራሳቸው አሸናፊነት ይልቅ ለተፎካካሪያቸው መልካምነትን ያሳዩና የአንድነትን ዋጋ ያንጸባረቁ ምስጉን አትሌቶችም በየጊዜው ታይተዋል። ዓለም አቀፉ ተቋም ሰላምን በሚመለከቱ ጉዳዮች ከሌሎች አካላት ጋር ከመስራት ባለፈ ለሰላም መስፈን ከፍተኛ ሚና ያላቸው ውድድሮችንም በመደገፍ ይታወቃል። ተፈጥሮን በመንከባከብ እንዲሁም ማህበራዊነትን ማስፋፋት ላይም ይሰራል።

የስፖርት ማህበራትና ሌሎች ተቋማትም ሰላምን ቅድሚያ የሚሰጡት ጉዳይ ሲሆን፤ መቀመጫውን በሞናኮ ያደረገ «ስፖርትና ሰላም» የሚልና አላማውም እንደመጠሪያው የሆነ ተቋምም ዓመታትን በስራ ላይ አስቆጥሯል። የዓለም ዋንጫ እየተካሄደ በነበረበት ወቅት ከቡድን አጋሮቹ ጋር በመሆን በአገሩ ለዓመታት የነበረውን የእርስ በእርስ ግጭት እንዲቆም በመማጸን ሰላም እንዲሰፍን በማድረግ ስሙ ከታሪካዊ የእግር ኳስ ከዋክብት መካከል የሰፈረው ኮትዲቯራዊው ዲድየር ድሮግባ ደግሞ ተቋሙን በምክትል ፕሬዚዳንትነት ያገለግላል።

ተቋሙ በየአገራቱ ዓላማውን ለማስረጽ የሚሰራ ሲሆን፤ ስፖርተኞችንም ይሸልማል። እንደሚታወቀው ተገዳዳሪ በሆኑ አካላት መካከል የበላይነትን አሊያም አሸናፊነትን ለመቀዳጀት ሲባል በሚካሄድ ፍልሚያ ለሚሰሩ ጥፋቶች ቢጫ እና ቀይ ካርዶች መመዘዛቸው አይቀሬ ነው። ይሁንና ነጭ ካርድም የስፖርትን ሰላማዊነት የሚያንጸባርቅ እንዲሆን አስተዋውቋል።

የኢትዮጵያን የሰላም ሁኔታ ለመመለስ መንግስት የተለያዩ ስልቶችን እየተከተለ የሚገኝ ቢሆንም ፤ የሰላም ማዕከል በሆነው የስፖርት ዘርፍ ግን ብዙ አልተሰራበትም። በኢትዮጵያ እየገነነ የመጣው የዘውግ ፖለቲካ ክልሎች በጎሪጥ እንዲተያዩ፤ የኔ ብሔር፣ ያንተ ጎሳ በሚል የጠበበ አስተሳሰብ መገፋፋቱ እየጎላ ሄዷል። ይህን ለአገር ጠንቅ የሆነ እንቅፋት ለመቅረፍ የኢፌዴሪ ሰላም ሚኒስቴር የተለያዩ የሰላም መድረኮችን በማዘጋጀት ጥረት ማድረጉ ይታወቃል። የሚኒስቴሩ ጥረት የስፖርቱን ዘርፍን በተለየ መልኩ መሰረት ማድረግ በጥራትና በፍጥነት ፍሬያማ ማድረግ ላይ ግን የማይካዱ ውስንነቶች አሉ።

በተለይ ደግሞ በአገሪቱ ህዝቦች መካከል መቻቻልን፣ አንድነትን፣ ወንድማማችነትን...የሚሰብኩ የውድድር መድረኮችን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ቀርጾ ወደ ተግባር በመግባት ረገድ የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክረው አልቀጠሉም። ለምሳሌ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ለ«ኢትዮጵያችን እንሩጥ» የሚል ሀሳብ የያዘ ውድድር አዘጋጅቶ፤ አንድነት፣ ወንድማማችነት፣ ብሄራዊ ስሜት፣ ባጠቃላይ ኢትዮጵያዊነት የሚያንጸባረቁባቸውን መልዕክቶች በማስተላለፍ የልዩነቱን ግንብ የመናድ አጋጣሚ መፍጠር ይቻላል። እንደ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሁሉ በሌሎች የስፖርት አይነቶችም አንድነትን፣ ሰላምን የሚያጎሉ ስፖርታዊ ክንውኖች ማዘጋጀት ቢቻል ትርፉ የጎላ እንደሚሆን ይታመናል። ምክንያቱም ስፖርት ሰላምን ለማስፈን ያለውን አቅምና ውጤታማነት በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች ለመመልከት ተችሏልና። የዘርፉ የሰላም አለኝታነት ደግሞ በትላልቅ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጭምር ቅቡልነቱ ያለው መሆኑን በዛሬው የሰላም ቀን ማስታወስ ተገቢ ይሆናል።

POPULATION MEDIA CENTER
Acting for Change

## ከፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር ጋር በመተባበር በየወሩ የሚታተም

# ኮካንቴ እና ጓደኞችዋ

ኮካንቴ ዳንሳ ትባላለች። በደቡብ ክልል በሃላባ ዞን አቶቲ ኡሉ ወረዳ ነዋሪ ነች። የ 18 አመት ወጣት እና የ 12ኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ኮካንቴ በወረዳዋ በፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር ከተሰሙት የሬዲዮ አድማጭ ቡድኖች መካከል አንዱን ትመራለች።

“የሴት ልጅ ግርዛትም ሆነ በታዳጊነት የሚፈጸም ጋብቻ በአካባቢያችን በብዛት ይፈጸም እንደነበር አውቃለሁ። ግርዛት እንደውም በእኔም ላይ ተፈጽሞአል። ገና የ 8 አመት ህጻን እና ስለ ግርዛትም ጎጂነት አላውቅም ነበር። ዛሬ ላይ መገረዜ በጣም ይቆጨኛል፤ ጉዳቱንም ተገንዝቤያለሁ እና ታናናሽዎቼ እንዳይገረዙ ታግያለሁ ተሳክቶልኝም እህቶቼን ከግርዛት አስጥያለሁ” በማለት ታሪክዋን መናገር የጀመረችው ኮካንቴ “በታዳጊነት የሚፈጸም ጋብቻ ግን በእኔ ላይ እንዲፈጽም አልፈቀድኩም።” በማለት የቅርብ አመታት ትውስታዋን እንዲህ በማለት መናገሯን ቀጠለች።

“አባቴ ኡስታዝ ነው። ገና 15 አመት እንከዋን ሳይሞላኝ ነበር ማግባት እንዳለብኝ የነገረኝ። እኔ መማር እንደምፈልግ እና እድሜዬም ለጋብቻ እንዳልደረሰ የምታውቀው እናቴ ኃላፊነቱን ወስዳ ከአባቴ ጋር ተጋፈጠች እና ከጎኔ ቆመች። «ትማራለች መድረስ የሚገባት ቦታም ትደርሳለች» በማለት ከውሳኔ ጋር ቆመችና ትምህርቴን መቀጠል ቻልኩ።



ወደፊትም ቢሆን አላማዬን ሳላሳካ ያለፍላጎቴ አላገባም።” በማለት ጠንካራ አቋምዋን የምትናገረው ኮካንቴ አሁን ላይ እያከናወነች ሰላለችውም ተግባር ትናገራለች

“ ዛሬ ላይ የሴት ልጅ ግርዛትንም ሆነ በታዳጊነት የሚፈጸም ጋብቻን ጎጂነት ለሌሎች እያስተማርኩ ነው። ከፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር በስልጠናም ሆነ በሬዲዮ ይህንን ጎጂ ድርጊት በተመለከተ ያገኘሁት መረጃ ደግሞ ከጓደኞቼ ጋር ሆኜ ለሌሎቻችን እንዳስተምር ጠቅሞኛል” በማለት ገልጻለች። ከኮካንቴ ጋር በጋራ እያስተማሩ ያሉትስ ምን ይላሉ?

“ያሲን ዳውድ እባላለሁ። የ 11ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። በተለይ በፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር አማካኝነት ስልጠና ከወሰድኩ በኋላ እኔ እና ጓደኞቼ ተመልሰን በየትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች እውቀታችንን አካፍለናል። በዚህም በወረዳችን ባሉ ትምህርት ቤቶች በመዞር ጉባ ሸረሮ ትምህርት ቤት ለ 400 ሴት ተማሪዎች እና ለ 288 ወንዶች፣ ጉሮራ ቡቾ ለ 360 ሴቶች እና ለ 400 ወንዶች፣ ሽዕዋኮ አሊባ ለ 250 ሴቶች እና ለ 350 ወንዶች፣ ደበሴት ለ 400 ሴቶች እና ለ 320 ወንዶች፣ ዩዬሽዕዋኮ ለ 288 ሴቶች እና ለ 269 ወንዶች በእረፍት ሰአታቸው በመገኘት ለ 15 ደቂቃ ያገኘነውን ግንዛቤ አካፍለናል” በማለት መዝግቦ የያዘውን የቁጥር መረጃ ምንጭ በማድረግ ያስረዳል።

“በታዳጊነት የሚፈጸም ጋብቻ በሴቶች ላይ ብቻ አይደለም፤ እኛም ወንዶቹ ትምህርታችንን አቋርጠን ለጋብቻም ዝግጁ ሳንሆን እንድናገባ በቤተሰብ የምንገድድበት ጊዜ አለ። እኔ ለምሳሌ ገና የ 8ኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ አባቴ ከአንድ ቤተሰብ ጋር ዝምድና ፈልጎ እንዳገባ ጠይቆኝ ነበር። እንቢ ብዬ ነው ትምህርቴን የቀጠልኩት” በማለት የራሱንም ገጠመኝ ይናገራል።

“ዙልፋ ጡኒሳ እባላለሁ” በማለት ራስዋን በማስተዋወቅ የጀመረችው ደግሞ ሌላዋ የኮካንቴ ጓደኛ ነች። “ግርዛት ጥቅሙ እና ጉዳቱ በማይገባኝ ጊዜ በ 9 ዓመቴ ተፈጸሞብኛል። ዛሬ ላይ ግን በታናናሽዎቼ እንዳይፈፀም እየታገልኩ ነው።

እስካሁን አልተፍጸመባቸውም፤ ወደፊትም እኔ እያለሁ አይፈጸምባቸውም” በማለት በቆራጥነት የምትናግረወ ዙልፋ፤ እንደ ጓደኞችዋ ሁሉ እስዋም ራስዋን በታዳጊነት ከሚፈጸም ጋብቻ እንዳስመለጠች ትናገራለች።